# ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ

(ሚዛናዊ እና ምክንያታዊ ፖለቲካ)

## የአቋም መግለጫዎች

ነእፓ ህዝብ ግንኙነት

ታህሳስ 2015፣ አዲስ አበባ

## *መግቢያ*

የአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ከሚያከናውናቸው መደበኛ ስራዎች መካከል አንዱ በተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ የፓርቲውን አቋም የሚገልጹ የአቋም መግለጫዎች ማዘጋጀት ነው፡፡ የአቋም መግለጫዎች የፓርቲው አባላት እና ደጋፊዎች እንዲሁም አጠቃላይ ማህበረሰቡ በወቅታዊ ጉዳዮች ዙርያ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖረው እና ፓርቲው በተለያዩ አጀንዳዎች ዙሪያ የሚከተለው አቅጣጫ እንዲታወቅ ከማድረግ ባሻገር የተሳሳቱ አስተሳሰቦች እንዲታረሙ ጉልህ አስተዋጾ ያደርጋል፡፡ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ (ነእፓ)** በህዝብ ግንኙነት የስራ ዘርፍ ከሚሰራቸው ስራዎች አንዱ በተለያዩ ወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የሚያዘጋጃቸው የአቋም መግለጫዎች ሲሆኑ፣ ፓርቲው በሀገራችን ፖለቲካ ተጨባጭ ተጽእኖ ለመፍጠር እንዲሁም የፓርቲውን ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ለማስተማር ዓላማ አድርገው የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ በነእፓ የሚዘጋጁ የአቋም መግለጫዎች የፓርቲውን ፖሊሲ እና ፕሮግራሞች ታሳቢ በማድረግ የፓርቲውን የፖለቲካ ፍልስፍና፣ ዓላማና ግቦች፣ እንዲሁም የስራ እንቅስቃሴዎች ለዜጎች ለማድረስ ትልቅ አስተዋጾ አላቸው፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ባለፉት ሶስት አመታት በማህበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ዓለም አቀፍ፣ ጉዳዮች ዙሪያ በርካታ የአቋም መግለጫዎችን አውጥቷል፡፡ በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች የሚከሰቱ ግጭቶች እና በዜጎች ላይ የሚደርሱ ጉዳቶች፣ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ለሁለት አመታት የተካሄደው የእርስ በርስ ጦርነት፣ የሀገራችን የሰብአዊ መብት አያያዝ፣ እየተባባሰ የመጣው የመልካም አስተዳደር ችግር፣ የውጭ ግንኙነት፣ የህዳሴ ግድብን ጨምሮ ብሄራዊ ጥቅማችንን የሚመለከቱ ጉዳዮች፣ 6ኛው ጠቅላላ ምርጫ፣ ብሄራዊ መግባባት፣ በአምልኮ ተቋማት ላይ የደረሱ ጥቃቶች፣ ሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ አደጋዎች፣ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ዜጎች፣ የዜጎች ራስን በራስ የማስተዳደር እና የክልልነት ጥያቄ፣ የነእፓ ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ የሀገራችን የፍትህ ስርአት ችግሮች ወዘተ ባለፉት ሶስት አመታት በነእፓ የአቋም መግለጫዎች የተዳሰሱ አንኳር ጉዳዮች ናቸው፡፡

ፓርቲው የሚያወጣቸው የአቋም መግለጫዎች ውጤታማ እና ተጽእኖ ፈጣሪ ይሆኑ ዘንድ ግልጽ መርሆች ላይ የተመሰረቱ እና በከፍተኛ ጥንቃቄ የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ ፓርቲው በሚያወጣቸው የአቋም መግለጫዎች ከሚከተላቸው መርሆች መካከል በፓርቲው ፕሮግራም እና ፖሊሲ የተቃኙ፣ የነእፓን መሰረታዊ የፖለቲካ ፍልስፍና እና የትግል ስልቶችን ታሳቢ ማድረግ፣ ከስሜት እና ወገንተኝነት መራቅ፣ ሚዛናዊነት እና ምክንያታዊነት፣ በበቂ መረጃ ላይ የተመሰረተ (ስለ ጉዳዩ መሬት ላይ ያለውን ሀቅ ያገናዘበ)፣ ከትናንሽ ክስተቶች ባሻገር ያለውን ትልቅ ምስል (big picture) እና የረዥም ጊዜ አንድምታ ታሳቢ ያደረገ፣ ከሌሎች የነእፓ እንቅስቃሴዎች ጋር የተናበበ፣ ወቅቱን የዋጀ እንዲሁም የፖለቲካ ትክክለኛነት (Political correctness) ይገኙበታል፡፡ አብዛኛው የፓርቲው መግለጫዎች በአማርኛው ቋንቋ የተዘጋጁ ሲሆን፤ ዓለም ዓቀፍ አንድምታ ባላቸው ጉዳዮች ዙሪያ በዓለም አቀፍ ቋንቋዎች ማለትም በእንግሊዝኛ እና በአረብኛ ቋንቋዎች መግለጫዎችን አዘጋጅቷል፡፡ ፓርቲው እስከ ዛሬ ያወጣቸው የአቋም መግለጫዎች ይዘት የፓርቲው ***ሚዛናዊ እና ምክንያታዊ ፖለቲካ*** ህያው ማሳያ ናቸው፡፡

የነእፓን የአቋም መግለጫዎች በአንድ ላይ የያዘው ይህ ሰነድ ፓርቲው በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የወሰዳቸውን አቋሞች እና ያስተላለፋቸውን መክረ ሀሳቦች ለመረዳት፣ እንዲሁም በፖለቲካ ፓርቲዎች ርዕዮተ ዓለም፣ የፖለቲካ ፕሮግራም እና አስተሳሰብ ዙሪያ ጥናት እና ምርምር ለሚያደርጉ ተመራማሪዎች የነእፓን መግለጫዎች ተደራሽ ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡

# ይዘት

1. የሰላም ስምምነቱ ሙሉ ለሙሉ ይተገበር ዘንድ የሁለትዮሽ ግንኙነት ተጠናክሮ ይቀጥል!! ..... 1
2. በደቡብ አፈሪካ በመንግስት እና በህወኃት መካከል የተደረሰውን የሰላም ስምምነት አስመልክቶ ከነአፓ የተሰጠ መግለጫ..... 3
3. የመንግስት ጸረ-ሙስና ዲስኩር ከቃል ወደ ተግባር ይሸጋገር!! ..... 4
4. መንግስት ለዜጎች ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ ፍትሀዊ ምላሽ ይስጥ!! ..... 6
5. በአፍሪካ ህብረት አሸማጋይነት ሊካሄድ የታቀደው የሰላም ድርድር እንዲሳካ ሁሉም አካላት የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል!! ..... 7
6. መልካም አዲስ ዓመት 2015፡ ሰላም የሁሉ ነገር መሰረት ነው!! ..... 8
7. سد النهضة هو مشروع أفريقي ووسيلة نحو تكامل إقليمي قوي !! ..... 10
8. GERD is an African Project and a means towards strong regional integration ..... 12
9. በቄለም ወለጋ በንጹሀን ላይ የደረሰውን ጭፍጨፋ ነአፓ በጽኑ ያወግዛል!! ..... 14
10. ነአፓ በወለጋ ዞን ሰላማዊ ዜጎች ላይ የደረሰውን የጅምላ ጭፍጨፋ በጽኑ ያወግዛል!! ..... 16
11. ከነአፓ ስራ አፈጻጻሚ ኮሚቴ በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የተሰጠ መግለጫ ..... 17
12. በሰሜን ኢትዮጵያ ያንዣበበውን የጦርነት ስጋት አስመልክቶ ከነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የተሰጠ መግለጫ!! ..... 21
13. በደቡብ ክልል በአብያተ ክርስቲያናት ላይ የደረሰውን ጥቃት አስመልክቶ ከነአፓ የተሰጠ መግለጫ ..... 23
14. ነአፓ በዜጎች ላይ የሚደርሱ ኃይማኖት-ተኮር ጥቃቶችን በእጅጉ ያወግዛል-የጎንደር መስጊድ ቃጠሎ!! ..... 25
15. በአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች የእምነት ነጻነት ሊከበር ይገባል ..... 28
16. ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ነኝ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አቋም መግለጫ ..... 31
17. The performance of the AU should be enhanced to match its ambitions!! ..... 34
19. የአርብቶ አደሩን ማህበረሰብ ተጋላጭነት በዘላቂነት ለማስወገድ የፖሊሲ ትኩረት ሊደረግ ይገባል!! ..... 37
20. ትኩረት በውጭ ሀገር ለሚኖሩ ወገኖቻችን! ..... 38
21. ጠንካራ እና ዘመኑን የዋጀ የሀገር መከላከያ ተቋም የሀገር ህልውና መሰረት ነው!! ..... 39
22. የሰሜኑን ጦርነት በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚደረግን ጥረት ነአፓ በጽኑ ይደግፋል!! ..... 40
23. “እንኳን ወደ ውድ ሀገራችሁ በሰላም መጣችሁ” ..... 43
24. “የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን”ን ለማቋቋም መንግስት የወሰደው ተነሳሽነት የሚደገፍ ነው ..... 44
25. የነአፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ እና ያስተላለፋቸው ውሳኔዎች ..... 46
26. ለአዲሱ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል መልካም ምኞታችንን እንገልጻለን!! ..... 48
27. ነአፓ ከመንግስት ለቀረበለት የአብረን እንስራ ጥያቄ የሰጠው ምላሽ ..... 49
28. መልካም የስራ ዘመን እንመኛለን!! ..... 50
29. በጦርነት የተፈናቀሉ ወገኖች አፋጣኝ ትኩረት ይሻሉ!! ..... 51

30. መልካም አዲስ አመት 2014፡ የሀገርን ህልውና ለማስጠበቅ የተቀናጀ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ስራ መስራት ያስፈልጋል!! ..... 52
31. ነእፓ ብሄራዊ የምርጫ አስተባባሪ ኮሚቴ መግለጫ ..... 58
34. ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በኢትዮጵያ የእንግሊዝ ኤምባሲን ጎበኘ፡፡ ..... 59
35. የነእፓ ከፍተኛ አመራሮች በኢትዮጵያ የጀርመን ኤምባሲን ጎበኙ፡፡ ..... 60
36. የነእፓ ሊቀመንበር ከአሜሪካ ኤምባሲ የፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊ ጋር ተወያዩ፡፡ ..... 61
37. በታሪካዊው የነጃሺ መስጂድ ላይ የደረሰውን ጥቃት ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በጽኑ ያወግዛል፡፡ ..... 62
38. በሀገር መከላከያ ተቋማት ላይ የሚደረግን ጥቃት ነእፓ ይቃወማል!! ..... 63
39. በሰላማዊ ዜጎች ላይ የሚደርሰው ጥቃት በአስቸኳይ ሊቆም ይገባል!! ..... 64
40. Ethiopians never exchange sovereignty for US Dollar፡ “Ethiopians’ Life Matter” ..... 66
41. ወለድ አልባ የፋይናንስ ስርአት ለፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል እና ለዴሞክራሲያዊ አንድነት!! ..... 67
42. የአንበጣ መንጋ በገበሬዎች ላይ በማድረስ ላይ ያለውን ጉዳት ለመቀነስ አስቸኳይ ሀገራዊ ንቅናቄ ያስፈልጋል!! ..... 68
43. መንግስት ህግ የማስከበር ሀላፊነቱን ህግን አክብሮ ይወጣ!! የፍርድ ቤት ውሳኔ ይከበር!! ..... 69
44. በብሄራዊ መግባባት ዙሪያ ነእፓ ጥናታዊ ጽሁፍ አቀረበ፡፡ ..... 70
45. የህዳሴ ግድብ የመጀመሪያ ዙር የውኃ ሙሊት መጠናቀቅ ብሄራዊ ስኬት ነው!! ..... 71
46. የሀገር መከላከያ ሰራዊትን ለማጠናከር እና ለማዘመን የሚሰራ ስራ የሚደገፍ ነው!! ..... 72
47. የሃይማኖት እኩልነት ለሀገር ሰላም እና እድገት የመሰረት ድንጋይ ነው!! ..... 73
48. “የዜጎች ሰብአዊ መብት የማይታለፍ ቀይ መስመር ነው” ..... 74
49. ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ሀገራዊ መግባባት (National Dialogue) ለማስጀመር የሚያስችል ሰነድ ይፋ አደረገ፡፡ ..... 77
50. በታላቁ የህዳሴ ግድብ ውይይት ብሄራዊ ጥቅማችን ለድርድር ሊቀርብ አይገባም!! ..... 78
51. ፓርቲ እና መንግስት ይለዩ!! ..... 79

## የሰላም ስምምነቱ ሙሉ ለሙሉ ይተገበር ዘንድ የሁለትዮሽ ግንኙነት ተጠናክሮ ይቀጥል!!

ጥቅምት 23፣ 2015 በፌዴራል መንግስት እና በህወኃት መካከል የተፈረመውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ ለሁለት አመት በሰሜን ኢትዮጵያ የቆየው ጦርነት በድርድር ለማፍታት መግባባት ላይ መደረሱ ይታወሳል። ይህንኑ ስምምነት ተከትሎ በኬንያ ዋና ከተማ ናይሮቢ በመንግስት እና በህወኃት ከፍተኛ አመራሮች ሁለት ዙር ውይይት ተካሂዷል። ስምምነቱ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ባለፉት አምስት ሳምንታት ስምምነቱን ተግባራዊ ለማድረግ በሁለቱም ወገኖች አወንታዊ እርምጃዎች እየተወሰዱ የሚገኙ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ የተኩስ አቁም ስምምነት፣ አፋጣኝ የሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦት፣ ተዋጊዎች ከውጊያ ቀጠና ማስወጣት ተግባራዊ እንደሆኑ በመንግስት እና በህወኃት ተገልጿል።

በዛሬው እለትም የሰላም ስምምነቱን አተገባበር አንድ እርምጃ ወደፊት ሊወስድ የሚችል እርምጃ በፌዴራል መንግስት ተወስዷል። በዚህም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባኤ በክቡር አቶ ታገሰ ጫፎ የሚመራ የፌዴራል መንግስት ከፍተኛ የልኡካን ቡድን በዛሬው እለት ወደ መቀሌ ተጉዞ ከትግራይ ክልል ኃላፊዎች ጋር ውይይት ማድረጉ ተሰምቷል። ይህ ጉዞ የሰላም ስምምነቱን በሂደት ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋጾ እንደሚኖረው የሚታመን ሲሆን፣ የሰሜኑ የርስ በርስ ጦርነት በሰላማዊ መንገድ እንዲቋጭ ለሚመኙ የህገራችን ዜጎች ትልቅ ብስራት ነው። በዛሬው እለት ወደ ትግራይ የተደረገው ጉዞ ከሁለት አመት በላይ በትግራይ እና በማእከላዊ መንግስት መካከል ተቋርጦ የነበረውን መንግስታዊ እና ማህበራዊ ግንኙነት ወደ ነበረበት ለመመለስ ከፍተኛ አስተዋጾ ይኖረዋል ተብሎ የታመነል።

ማንኛውም ጦነርት እና አለመግባባት በሰላማዊ መንገድ በድርድር እና በጠረጴዛ ዙሪያ ሊፈታ ይገባል የሚል ጽኑ እምነት ያለው **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** የሰላም ስምምነቱን በእጅጉ የደገፈ ሲሆን፣ ስምምነቱን ተግባራዊ ለማድረግ በመንግስትም ሆነ በህወኃት በኩል የሚወሰዱ እርምጃዎችን ይደግፋል። ጦርነቱ በህገራችን ላይ ያስከተለውን ሁለንተናዊ ጉዳት በአጭር ጊዜ ቀልብሰን በሰሜናዊ የህገራችን ክፍል ዘላቂ ሰላም እውን ለማድረግ፣ የሰላም ስምምነቱን በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። የዛሬው የፌዴራል መንግስት ልኡክ የመቀሌ ጉብኝት ከዚህ አንጻር ሊደገፍ ተሚገባው እርምጃ ነው። የሰላም ስምምነቱን በአጭር ጊዜ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ሆኖ በህገራችን አስተማማኝ እላም እውን ይሆን ዘንድ፣

- የየብስ እና የአየር ትራንስፖርት፣ ቴሌኮም፣ ባንክ እና ሌሎች በጦርነቱ የወደሙ መሰረተ ልማቶችን መልሶ ለመገንባት የተጀመረውን እንቅስቃሴ በማጠናከር በአጭር ጊዜ ውስጥ በመላው ትግራይ እንዲሁም በአጎራባች የአፋር እና የአማራ ክልሎች ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች እንዲጀመር፣

- በጦርነቱ ምክንያት በዜጎች መካከል የሻከሩ ማህበራዊ ግንኙነቶችን እና ጥላቻን አስወግዶ፣ የዜጎችን ማህበራዊ ትስስር ለማጠናከር እና ህገራዊ አንድነትን ለማጎልበት የህዝብ ለህዝብ ግንኙነትን ሊያድሱ የሚችሉ ተግባራትን በመንግስት እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እንዲካሄድ፣

- በትግራይ ክልል እና በሌሎች የህገራችን አካባቢዎች መካከል የህዝብ ለህዝብ ግንኙነቶችን በአፋጣኝ ለማስጀመር እና ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶችን ለማጠናከር ወደ ትግራይ የሚደረገውን የአየር በረራ በአፋጣኝ እንዲጀመር፣

- በሰላም ስምምነቱ ያልተካተቱ ነባር ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ልዩነቶችን በቀጣይ በሀገራችን ይካሄዳል ተብሎ በሚጠበቀው ሀገራዊ ምክክር ማእቀፍ ውስጥ የፖለቲካ ልዩነቶች በጠረጴዛ ዙሪያ በዘላቂነት እንዲፈቱ፣

- በሰላም ስምምነቱ መሰረት በትግራይ ክልል የሚገኙ የውጭ ኃይሎች በአፋጣኝ የሀገራችንን ድንበር ለቀው እንዲወጡ ማድረግ እና የኢትዮጵያ መከላከያ የሀገራችንን ድንበር እንዲጠብቅ እንዲደረግ፣

- በመጨረሻም መንግስት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ለሁለት አመት የዘለቀውን ጦርነት በሰላማዊ መንገድ ለመፍታ ያሳየውን ተነሳሽነት በሌሎች የሀገራችን አካባቢዎች በተለይም ኦሮሚያ፣ ጋምቤላ እና ቤኒሻንጉል ክልሎች ከሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ኃይሎች ጋር የፖለቲካ ልዩነቶች በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ጥረት ያደርግ ዘንድ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ጥሪውን ያቀርባል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ታህሳስ 17፣ 2015፣ አዲስ አበባ**

# በደቡብ አፈሪካ በመንግስት እና በህወኃት መካከል የተደረሰውን የሰላም ስምምነት አስመልክቶ ከነኢፓ የተሰጠ መግለጫ

ላለፉት ጥቂት ቀናት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት እና በህወኃት መካከል በደቡብ አፍሪካ ሲካሄድ የነበረው የሰላም ድርድር በዛሬው እለት በስምምነት መጠናቀቁ ታውቋል:: **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ሁለት አመት ያስቆጠረውን እጅግ አውዳሜ ጦርነት በሰላማዊ መንገድ ለመቋጨት ለተደረሰው ስምምነት ያለውን ከፍተኛ ድጋፍ እየገለጸ ለድርድሩ መሳካት በጎ አስተዋጾ ላደረጉ አካላት ሁሉ አድናቆቱን ይገልጻል::

ልክ የዛሬ ሁለት አመት ጥቅምት 24፣ 2013 የተለኮሰው የጦርነት እሳት ባለፉት 24 ወራት ሀገራችንን እና ህዝባችንን ከፍተኛ የህይወት፣ የንብረት እና የስነልቦና ዋጋ አስከፍሏል:: **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ጦርነቱ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ችግሩ በሰላማዊ መንገድ ይፈታ ዘንድ ጥሪ ሲያቀርብ መቆየቱ የሚታወስ ሲሆን፣ ጦርነቱን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት በዛሬው እለት ለተደረገው ስምምነት ከፍተኛ ዋጋ ይሰጣል::

በዛሬው እለት ስምምነት የተደረሰባቸው ነጥቦች ወደ ተግባር ተለውጠው መላው የሀገራችን ህዝቦች በጉጉት የሚጠብቁት ሰላም እና መረጋጋት እውን ይሆን ዘንድ ዋነኛ ተደራዳሪዎቹ የፌዴራል መንግስት እና ሕወኃት፣ የፖለቲካ ኃይሎች እንዲሁም መላው የሀገራችን ህዝቦች ለስምምነቱ ተፈጻሚነት የበኩላቸውን ይወጡ ዘንድ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ጥሪ እያቀረበ፣ በዛሬው እለት በተደረሰው የሰላም ስምምነት ለመላው የሀገራችን ህዝቦች የእንኳን ደስ አላችሁ መልእክቱን ያስተላልፋል::

**መጪው ዘመን በሀገራችን ሰላም፣ ወንድማማችነት፣ አንድነት፣ ልማት እውን ይሆን ዘንድ አጥብቀን እንመኛለን::**

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ጥቅምት 23፣ 2015**
**አዲስ አበባ**

# የመንግስት ጸረ-ሙስና ዲስኩር ከቃል ወደ ተግባር ይሸጋገር!!

ሙስና እና ብልሹ የመንግስት አሰራር የሀገርን እድገት እና የህዝብን ደህንነት በእጅጉ ይጎዳሉ፡፡ ሙስና ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ያቀጭጫል፣ ዜጎች መሰረታዊ አገልግሎቶችን እንዳያገኙ በመንፈግ ለእንግልት እና ብዝበዛ ይዳርጋል፡፡ ሙስና ሰፊውን የማህበረሰብ ክፍል በድህነት አረንቋ በመዝፈቅ ጥቂቶች በሀብት እንዲንበሸበሹ የሌብነት በርን ይከፍታል፡፡ ሙስና ዘርፈ ብዙ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳትን የሚያስከትል ሲሆን ከፍተኛ የዋጋ ንረት እና የኑሮ ውድነት፣ ጥራት የጎደላቸው የመንግስት ፕሮጀክቶች፣ የመንግስት ገቢ ማሽቆልቆል፣ የአካባቢ ብክለት እና የተፈጥሮ ሀብት ውድመት፣ ምርታማነት በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ፣ የተደራጀ የወንጀል ድርጊት መስፋፋት፣ ፍትሀዊ ያልሆነ የገቢ እና የሀብት ክፍፍል፣ የማህበራዊ ፍትህ መዛባት፣ ወዘተ ከብዙ በጥቂቱ ይገኙበታል፡፡

ሙስና በሀገራችን ታሪክ ረዥም ዘመናትን ያስቆጠረ ፖለቲካዊ እና አስተዳደራዊ ነቀርሳ ነው፡፡ ሙስና በሀገራችን አይነት እና ይዘቱ እየተለዋወጠ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ የመጣ ሲሆን፣ ባለፉት ጥቂት አመታት እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ በለውጡ ማግስት አንጻራዊ “መሻሻል” አሳይቷል የተባለለት የሙስና ወንጀል ብዙም ሳይቆይ አገርሽቷል፡፡ ከወረዳ እስከ ፌዴራል መንግስት፣ በመንግስት መስሪያ ቤቶች የትኛውንም አገልግሎት ለመስጠት ዜጎች ከአቅማቸው በላይ ጉቦ እንዲከፍሉ ማስገደድ መደበኛ ሊባል በሚችል ደረጃ የተለመደ ተግባር ሆኗል፡፡

ባለፉት ሁለት አመታት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተቀሰቀሰው ጦርነት ምክንያት የተፈጠረው ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ በሙስና ምክንያት ይበልጥ ተባብሷል፡፡ በተለያየ ደረጃ በመንግስት መዋቅር የተሰገሰጉ ሙሰኞች በጦርነት የተጠመደውን የመንግስት እና የህዝብ ትኩረት እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም በሙስና ተግባር ተዘፍቀዋል፡፡ ከጥቃቅን እና አነስተኛ እስከ ከፍተኛ የንግድ እና ኢንቨስትመንት ፍቃድ ለማውጣት፣ ለመኖሪያ ወይም ለኢንቨስትመንት መሬት ለማግኘት፣ የጤና፣ ትምህርት፣ ትራንስፖርት፣ የፍትህ ወዘተ አገልግሎት ለማግኘት ዜጎች ለከፋ የሙስና ወንጀል ይዳረጋሉ፡፡

በአሁኑ ወቅት ሙስና በሁሉም መስኮች እና በአብዛኛው የመንግስት መስሪያ ቤቶች በስፋት የሚስተዋል ወንጀል ሲሆን፣ የተወሰኑ ዘርፎች በሙስና ይበልጥ የተዘፈቁ ስለመሆናቸው የመንግስት ማረጋገጫ በቂ ነው፡፡ ባለፉት ጥቂት ወራት መንግስት በሀገራችን ሙስና በከፍተኛ ሁኔታ እየተንሰራፋ መምጣቱን በተደጋጋሚ ገልጿል፡፡ መንግስት በተለያዩ መድረኮች በሀገራችን ያለውን መጠነ ሰፊ የሙስና ወንጀል እና ሙስና ይበልጥ ተንሰራፍቶባቸዋል የተባሉ የመንግስት መስሪያ ቤቶችን ሲገልጽ መስማት የተለመደ ሆኗል፡፡ከቁጥጥር የወጣ የሚመስለውን ሙስና ለመከላከል በሚል መንግስት በቅርቡ የፀረ ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴ ማቋቋሙን ይፋ አድርጓል፡፡ ይሁን እንጂ ችግሩ ከመቀነስ ይልቅ ይበልጥ እየሰፋ መምጣቱን ከዜጎች የእለት ተእለት ሮሮ መረዳት ይቻላል፡፡

ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል መንግስት በሙሰኞች ላይ ፈጣን እና አስተማሪ ቅጣት መውሰድ የሚገባው ሲሆን ከላይ እስከ ታች የተዘረጋውን ረዥም የሙስና መረብ መበጣጠስ፣ በሙሰኞች ላይ ያለርህራሄ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል፡ ፡ መንግስት ሙስናን ለመዋጋት ያለውን ቁርጠኝነት ለማሳየት በየትኛውም ደረጃ በሚገኙ የፓርቲ ወይም የመንግስት ኃላፊዎች ላይ አፋጣኝ እና አስተማሪ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ በሙሰኞች ላይ የሚወሰድ እርምጃ በዘገየ ቁጥር ወንጀሉ ይበልጥ

እንዲስፋፋ፣ ሙሰኞችም የልብ ልብ እንዲሰማቸው ያደርጋል፡፡ ሰለ ሙስና አመት ከአመት እየደሰኮሩ ተጨባጭ እርምጃ አለመውሰድ የመንግስትን አቅመ ደካማነት እና ችግሩን ለመቅረፍ ያለው ቁርጠኝነት አናሳ መሆኑን ያሳያል፡፡

የሙስና ወንጀል ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት የጥቅም ትስስር ፈጥረው በጥብቅ ሚስጥር እና አንዳንዴም ህጋዊ አሰራርን እንደ ሽፋን በመጠቀም የሚፈጸም ተግባር በመሆኑ፣ ሙስናን ለመከላከል ዜጎችን ያማከለ፣ በቴክኖሎጂ የታገዘ ከፍተኛ የክትትል እና ቁጥጥር ስርአት መዘርጋት ያስፈልገል፡፡ ሙስና ተቋማዊ እና መዋቅራዊ ይዘት ያለው ወንጀል በመሆኑ በዘመቻ ወይም ግብረ ኃይል በማቋቋም የሚፈታ ችግር አይደለም፡፡ ላለፉት በርካታ አመታት መንግስት ሙስናን “ለመዋጋት” ያደረጋቸው ዘመቻዎች ውጤት አልባ የሆኑት ሙስና መዋቅራዊ ችግር መሆኑን ካለመረዳት የመነጨ ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት በሙስና ላይ የሚደረጉ ዘመቻዎች የጥቂት ሳምንታት ወይም ወራት ርእስ አንቀጽ እና የፖለቲካ ፍጆታ ከመዋል አልፈው ችግሩን ከመሰረቱ መፍታት አልቻሉም፡፡

በወረርሽኝ፣ በድርቅ፣ በእርስበርስ ጦርነት እና በአለም አቀፍ ግጭቶች ሳቢያ በደቀቀው የሀገራችን ኢኮኖሚ ምክንያት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በቀን አንዴ ምግብ ማግኘት ህልም በሆነባት ሀገር፣ ጥቂቶች በሙስና ባጋበሱት ሀብት የተንደላቀቀ ህይወት የሚኖሩ፤ ዜጎች ውሀ፣ ዳቦ፣ መብራት፤ መጠለያ፣ እንዲሁም መሰረታዊ የጤና እና የትምህርት አገልግሎት ማግኘት እንደ ሰማይ በራቃቸው በአሁኑ ወቅት በህዝብ የተሰጣቸውን ኃላፊነት ችላ ብለው ከድህ ዜጎች የተሰበሰበን ግብር ከሀገር አሸሽተው በውጪ ሀገር ሀብት የሚያደልቡ ሙሰኞች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በቃችሁ ሊባሉ ይገባል፡፡

የሀገራችንን ህልውና እና የዜጎችን ደህንነት እየተፈታተነ የሚገኘውን ሙስና ለመዋጋት ዜጎች ሙስናን በመጠየፍ እና ሙሰኞችን በማጋለጥ የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡ ከዚህ ባሻገር ዜጎች ሙስናን መከላከል እና መቆጣጠር የማይችል ፓርቲ እና መንግስትን የሚሸከም ትከሻ እንደሌላቸው በየትኛውም ደረጃ በሚካሄዱ ምርጫዎች በካርዳቸው ድምጻቸውን ሊያሰሙ ይገባል፡፡ ሙስናን መዋጋት እና መልካም አስተዳደርን ማስፈን የመንግስት ተቀዳሚ ተግባር ነው፡፡ ሙስናን መቆጣጠር ያልቻለ ፓርቲ እና መንግስት ልማትን ማረጋገጥ፣ ሰላምን ማስፈን፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፍትህን እውን ማድረግ አይችልም፡፡ በመሆኑም መንግስት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የጀመረው ጸረ ሙስና ዲስኩር ውጤታማ ይሆን ዘንድ ከቃል ያለፈ ተግባራዊ እርምጃ በመውሰድ ቁርጠኝነቱን በተግባር ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

**ህዳር 20፣ 2015**
**አዲስ አበባ**
**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**

# መንግስት ለዜጎች ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ ፍትሀዊ ምላሽ ይስጥ!!

የሀገራችን ህዝቦች ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው ተከብረው **በነጻነት እና በእኩልነት** ለመኖር ረዥም እና እልህ አስጨራሽ ትግል አካሂደዋል። በተለያየ ጊዜ ኢትዮጵያን ያስተዳደሩ መሪዎች የዜጎችን ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በኃይል ለመጨፍለቅ እና ነጻነታቸውን ለመግፈፍ ያደረጉትን ሙከራ በመቃወም መላ የሀገራችን ህዝቦች በሁሉም መአዘን ከፍተኛ ትግል አካሂደዋል፣ ትልቅ መስዋእትነትም ከፍለዋል። ከአራት አመት በፊት በሀገራችን የተጀመረው የፖለቲካ ተሀድሶ እውን ይሆን ዘንድ ትልቅ ዋጋ የተከፈለበት የለውጥ እንቅስቃሴ ካነሳቸው ጥያቄዎች አንዱ ዜጎች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት ማረጋገጥ ነው።

የዜጎች ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ ባለፉት ጥቂት አመታት በተለይም **በደቡብ ኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል** በስፋት እየተነሳ ይገኛል። ከዚሁ ጥያቄ ጋር ተያይዞ ሁለት ክልሎች ተወልደው ፌዴሬሽኑን የተቀላቀሉ ሲሆን፣ ራስን በራስ የማስተዳደሩ ጥያቄው ዛሬም እንደቀጠለ ነው። በኢፌዴሪ ህገ መንግስት የተረጋገጠውን የዜጎች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት በተግባር የማስፈጸም ኃላፊነት የመንግስት ቢሆንም፣ ባለፉት ጥቂት ወራት መንግስት ለዜጎች ጥያቄ እየሰጠ ያለው ምላሽ ከዜጎች ህገ መንግስታዊ መብት ጋር እንዳይጋጭ ከፍተኛ ስጋት ፈጥሯል።

የዜጎች በክልል ወይም ከዚያ በታች ባሉ የአስተዳደር እርከኖች የመደራጀት ጥያቄ የሚፈጽምበት አግባብ በኢፌዴሪ ህገ መንግስት በማያሻማ መልኩ ተቀምጦ እያለ፣ ጥያቄውን በአግባቡ ላለማስተናገድ አንዳንድ የመንግስት አካላት የሚወስዷቸው እርምጃዎች እና የሚፈጥሯቸው ፖለቲካዊ እና አስተዳደራዊ መሰናክሎች የዜጎችን ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብት ከመገደብ አልፎ የሀገርን ሰላም እንዳያናጉ፣ እንዲሁም የህዝቦችን አንድነት እንዳይሸረሽሩ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል። በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ለሁለት አመት በተካሄደው ጦርነት እና አሁንም በአንዳንድ የሀገራችን ክፍሎች ባሉ ግጭቶች ምክንያት ሰላሟ የደፈረሰው ሀገራችን፣ በዜጎች ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ ላይ በሚደረጉ አላስፈላጊ ጫናዎች እና ከሀገሪቱ ህጎች ጋር የሚቃረኑ እርምጃዎች በህገራችን ያለውን የፖለቲካ አለመረጋጋት ይበልጥ እንዳያባብሱ የሚመለከታቸው የፌዴራል፣ የክልል እና የዞን አመራሮች ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል።

የመላው የሀገራችን ህዝቦች ዋነኛ ጠላት የሆነውን ድህነት ለማስወገድ፣ በሁሉም የሀገራችን ክፍል ሰላም እና መረጋጋትን ለማስፈን፣ በዜጎች መካከል አንድነት እና ወንድማማችነትን ለማረጋገጥ . . . ጠንካራ የዴሞክራሲ ስርአት መገንባት እና ለዜጎች ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ ፍትሀዊ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል። **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** የኢትዮጵያውያን የግል እና የቡድን መብቶች ሳይሸራረፉ እንዲከበሩ ማስቻል ትልቅ ትኩረት ከሚሰጣቸው የፖለቲካ አጀንዳዎች መካከል አንዱ ሲሆን፣ ዜጎች ለሚያነሷቸው **"ማንነቴ ይታወቅልኝ እና ይከበርልኝ"** ጥያቄዎች ፍትሀዊ እና ህጋዊ ምላሽ ሊሰጣቸው ይገባል ብሎ በጽኑ ያምናል። በመሆኑም በተለይም በደቡብ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች ዜጎች ለሚያነሷቸው ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መንግስት ህግን መሰረት ያደረገ አፋጣኝ እና ፍትሀዊ ምላሽ እንዲሰጥ እንጠይቃለን።

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ሀዳር 23፣ 2015**
**አዲስ አበባ**

## በአፍሪካ ህብረት አሸማጋይነት ሊካሄድ የታቀደው የሰላም ድርድር እንዲሳካ ሁሉም አካላት የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል!!

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በመካሄድ ላይ ያለው ጦርነት ሙሉ ለሙሉ ቆሞ በሀገራችን የተሟላ ሰላም ይረጋገጥ ዘንድ መላው የሀገራችን ህዝቦች በተስፋ እና በጉጉት እየጠበቁ እንደሚገኙ ይታወቃል፡፡ ጦርነቱን ለማቆም ከዚህ ቀደም በርካታ የሰላም ጥሪ እና የድርድር ሙከራዎች ሲደረጉ መቆየቱ የሚታወስ ቢሆንም፣ ሙከራዎቹ ውጤታማ ባለመሆናቸው ጦርነቱ ሊቆም አልቻለም፡፡

ጦርነቱን ለማስቆም በሚደረገው አለም አቀፍ ጥረት በግምባር ቀደምትነት የሚሰራው የአፍሪካ ህብረት በመንግስት እና በሕወሓት መካከል ድርድር እንዲካሄድ ሰሞኑን ጥሪ ማቅረቡ ተሰምቷል፡፡ በዚሁ መሰረት ህብረቱ ጊዜ እና ቦታ ወስኖ ድርድር ለማስጀመር ለፌዴራል መንግስት እና ለሕወሓት ጥሪ ማቅረቡ የታወቀ ሲሆን፣ ሁለቱም አካላት ጥሪውን መቀበላቸውን በይፋ አስታውቀዋል፡፡በአፍሪካ ህብረት በኩል የተመቻቸው ይህ የውይይት መድረክ ደብዝዞ የቆየው የሰላም እድል መልሶ እንዲያንሰራራ ትልቅ ተስፋን ፈንጥቋል፡፡

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ላለፉት ሁለት ዓመታት የቆየው ጦርነት በሰላማዊ መንገድ እንዲቋጭ ተከታታይ ጥሪ ሲያቀርብ የቆየው **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በመንግስት እና በሕወሓት መካከል ድርድር እንዲካሄድ በአፍሪካ ህብረት የቀረበው ጥሪ ተስፋ ሰጪ ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ሀገራችንን እጅግ ከፍተኛ ሰብአዊ እና ቁሳዊ ዋጋ እያስከፈለ የሚገኘው ይህ ጦርነት በአፋጣኝ እና በአስተማማኝ ሁኔታ ይቋጭ ዘንድ በአፍሪካ ህብረት አስተባባሪነት ሊካሄድ የታቀደው የውይይት መድረክ ውጤታማ ይሆን ዘንድ የሚመለከታቸው አካላት የድርሻቸውን እንዲወጡ ነኢፓ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

ስለ ድርድር ስናስብ በጦርነቱ ምክንያት ውድ ህይወታቸውን ያጡ ዜጎቻችንን፣ ያለ አሳዳጊ እና ያለ ጧሪ የቀሩ እልፍ ህጻናት እና አረጋውያንን እያሰብን ሊሆን ይገባል፡፡ ስለ እርቅ ስናስብ ጦርነቱ በአማራ፣ በአፋር፣ በትግራይ ክልሎች ነዋሪዎች ብሎም በሌሎች የሀገራችን አካባቢዎች ላይ ያደረሰው እጅግ አሳዛኝ ስቃይ፣ እንግልት እና መከራ እየተሰማን ሊሆን ይገባል፡፡ ስለ ሰላም ስናስብ ሀገራችን በጦርነቱ ምክንያት የገባችበትን ዘርፈ ብዙ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ምስቅልቅል በአጠረ ጊዜ መቆምን እየናፈቅን ሊሆን ይገባል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በአፍሪካ ህብረት አነሳሽነት የተፈጠረው ይህ ታሪካዊ የሰላም እድል ተሳክቶ በሀገራችን ሰላም እና መረጋጋት፣ አንድነት እና ወንድማማችነት ይሰፍን ዘንድ የሰላም እድሉ እንዳይመክን ሂደቱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸው አካላት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ እየጠየቀ፣ መላው የሀገራችን ህዝቦች ለሂደቱ መሳካት ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**መስከረም 26፣ 2015**
**አዲስ አበባ**

# መልካም አዲስ ዓመት 2015፡ ሰላም የሁሉ ነገር መሰረት ነው!!

## አዲሱ ዓመት የሰላም እና እንዲሆን እንመኛለን!!

በዓለም የአስራ ሶስት ወራት የጊዜ ቀመር ባለቤት የሆነችው ሀገራችን ኢትዮጵያ 2014ን ተሰናብታ እነሆ ዛሬ አዲሱን ዓመት አንድ ብላ ጀምራለች፡፡ ቀናት፣ ሳምንታት፣ ወራት ተነባብረው ዓመት ያልፋሉ፣ በአዳዲስ ዓመታት ይተካሉ፡፡ የሀገራችን አዲስ አመት ከሌሎች የሚለዩት አያሌ ምክንያቶች ያሉት ሲሆን፣ የጊዜ ቀመራችን ከተፈጥሮ ጋር ተቀናጅቶ አዲሱ ዓመት ለምድራችን አዲስ ገጽታ ማልበሱ ይበልጥ ልዩ ያደርገዋል፡፡መስከረም ሲጠባ የሀገራችን ምድር በአደይ አበባ ይሸቆጠቆጣል፣ የሀገራችን ሰማይ በብርሀን ይደምቃል፡፡ በዚህም ምክንያት አዲስ አመት ሁሌም ተናፋቂ፣ አስደሳች እና ብሩህ ተስፋ ፈንጣቂ ሆኖ በኢትዮጵያውያን ልብ ውስጥ ተቀርጿል፡፡ ይህ የሀገራችን አዲስ አመት ልዩ ባህሪ “የጊዜ እና ቦታ” ዝምድና እና ቁርኝት ይበልጥ ጎልቶ የሚታይበት የሀገራችን ሌላው መለያ ነው፡፡

ዘመን ሲፈራረቅ በውስጡ አያሌ ነገሮችን ይዞ ይነጉዳል፡፡ በዘመን ሽግግር የጊዜ ሳጥን በውስጡ እጅግ በርካታ እና ጉራማይሌ እውነታዎች ቆጥሮ ይከንፋል፡፡ ደስታ እና ሀዘን፣ ስኬት እና ውድቀት፣ ከፍታ እና ዝቅታ፣ ልደት እና ሞት፣ ሳቅ እና ለቅሶ፣ ድል እና ሽንፈት፣ ማትረፍ እና መክሰር. . . በዘመን ኡደት ውስጥ በግለሰብም ሆነ በሀገር ላይ እየተፈራረቁ የሚያልፉ ሀቆች ናቸው፡፡ የሀገራችን እውነታም ዘመን ለማይሽረው ለዚህ የዘመን ህግ ተገዥ ሆኖ 2014 ተገባዶ አዲሱን አመት ሀ ብለን ጀምረናል፡፡

በ2014 ሀገራችን አያሌ ክስተቶችን ያስተናገደች ሲሆን፣ እንደ ከዚህ ቀደሞቹ ጥቂት ዓመታት ሁሉ በጦርነት እና በግጭት የተሞላው የሀገራችን ፖለቲካ ለበርካታ ኢትዮጵያውያን ሞት እና ስደት፣ ርሀብ እና ስቃይ፣ ሀዘን እና ትካዜ ምክንያት ሆኖ አልፏል፡፡ ከሁለት አመት በፊት በትግራይ ክልል ተለኩሶ በአፋር እና አማራ ክልሎች የተዛመተው ጦርነት፣ በዓመቱ መገባደጃም የብዙዎችን ህይወት እየቀጠፈ፣ በርካቶችን ከቤት ንብረታቸው እያፈናቀለ፣ ኢኮኖሚያችንን እየበላ፣ ሴት፣ ህጻናት እና አቅመ ደካሞችን ለጉዳት እየዳረገ፣ የዜጎችን ማህበራዊ የትስስር መረብ እየበጣጠሰ ቀጥሏል፡፡

እርግጥ ነው በተገባደደው አመት ሀገራችን መልካም ነገሮችንም አሳልፋለች፡፡ የሀገራችን ኩራት፣ የዜጎች የአንድነት ካስማ፣ የሉአላዊነታችን ምልክት የሆነው የህዳሴ ግድብ ሶስተኛ ዙር የውሀ ሙሊት መጠናቀቅ፣ የግድቡ ሁለተኛ ተርባይን ኃይል ማመንጨት መጀመር፣ አትሌቶቻችን በአለም መድረክ የሀገራችን ሰንደቅ አላማ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ ማድረጋቸው በዜጎች ልብ ውስጥ ለአፍታም ቢሆን የደስታን ብርሀን ፈንጥቀው አልፈዋል፡፡

ከአለም ድሀ ሀገራት መካከል አንዷ የሆነችው ሀገራችን፣ ካለችበት ውስብስብ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለመላቀቅ ከምንም በላም ሰላም እና መረጋጋት ያስፈልጋታል፡፡ ያለ ሰላም፣ አርሶ፣ ዘርቶ፣ አጭዶ፣ ጎተራን መሙላት፣ ፋብሪካ ተክሎ ማምረት፣ ነግዶ ሸጦ ለውጦ ማትረፍ አይቻልም፡፡ ያለ ሰላም ተምሮ ተመራምሮ ራስን እና ሀገርን መጥቀም፣ ወልዶ መሳም፣ እንዳሻን መንቀሳቀስ አይቻልም፡፡ ***ሰላም የሁሉ ነገር መሰረት ነው!!*** ሰላምን ማስፈን አርቆ ማሰብን፣ ይቅር ባይነትን፣ ከታሪክ መማርን ይሻል፣ ሰላምን ማረጋገጥ ሰለሰላም ከመናገር ባሻገር ሀቀኛ እና ተግባራዊ እርምጃዎችን መውሰድን ይጠይቃል፣ ሰላም መገንባት ከህሊና ወቀሳ እና ከታሪክ ተጠያቂነት ማምለጥ እንደማይቻል መገንዘብን፣ በኃላፊነት እና በተጠያቂነት ስሜት መስራትን ይሻል፡፡

**መላው የሀገራችን ህዝቦች፣**

አዲስ ዓመት የተስፋ እና የደስታ ምንጭ ነው፡፡ አዲስ አመት በመጣ ቁጥር ዜጎች ለራሳቸው፣ ለቤተሰቦቻቸው፣ ለሀገራቸው እና ለመላው የሰው ዘር ሁሉ መልካም መልካሙን ይመኛሉ፡፡ እኛም ይህንኑ ለመላው ህዝባችን ተመኝን፡፡ በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር ለምትኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን መጪው ዓመት የሰላም፣ የአብሮነት፣ የአንድነት እና የደስታ እንዲሆን **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ይመኛል፡፡

አዲሱ አመት በሰሜን፣ በምእራብ በሌሎች የሀገራችን አካባቢዎች ያሉ ጦርነት እና ግጭቶች ሙሉ ለሙሉ ቆመው በሀገራችን አራቱም መአዘናት እውነተኛ ሰላም የሚሰፍንበት፣ ዜጎች ከስጋት እና ጭንቀት ተላቀው በደስታ እና በፍቅር የሚኖሩበት፣

የዜጎቻችንን ወገብ ያጎበጠው የኑሮ ሸክም ቀንሶ መላው የሀገራችን ህዝቦች በሀሴት የሚኖሩበት፣ በተለያዩ በሽታዎች የሚሰቃዩ ወገኖቻችን ከህመማቸው ድነው የጤና እና የደስታ ህይወት የሚኖሩነት እንዲሆን ከልብ እንመኛለን::

አዲሱ አመት ሀገራችን ቀስፈው ከያዟት አያሌ እና ውስብስብ ችግሮች እንደ ከረምቱ ጎርፍ፣ ጥቁር እና ጭፍግግ ዳመና አልፈው፣ አዲስ የተስፋ ብርሀን የሚፈነጥቅበት፣ አእዋፋት የሰላም ዜማ የሚያዜሙበት፣ የጦርነት ነጋሪት ቆሞ መልካም መልካሙን የምንሰማበት የእርቅ እና የሰላም ዘመን እንዲሆን እንመኛለን::

**የተከበራችሁ ኢትዮጵያውያን፣**
**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ሰላም የሁሉ ነገር መሰረት ነው ብሎ በጽኑ ያምናል:: **ነእፓ** ለሰላም እውን መሆን ሁሌም ሲያደርገው እንደቆየው ሁሉ በአዲሱም አመት በሀገራችን አስተማማኝ ሰላም እውን ይሆን ዘንድ አቅሙ የፈቀደውን ሁሉ ያደርጋል:: **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** አሁናዊ ግጭቶች በውይይት እና በድርድር፣ ታሪካዊ ቁርሾዎች እና ግጭቶች በሀገራዊ ምክክር እና ብሄራዊ መግባባት ይፈቱ ዘንድ ጥረቱን የሚቀጥል ሲሆን፣ መላው የሀገራችን ህዝቦች ለሰላም፣ ለወንድማማችነት እና እህትማማችነት፣ ለአንድነት እና ለአብሮነት በጋራ እንዲቆሙ በዚህ አጋጣሚ ጥሪውን ያቀርባል::

**መልካም አዲስ አመት**
**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**መስከረም 1፣ 2015**
**አዲስ አበባ**

## سد النهضة هو مشروع أفريقي ووسيلة نحو تكامل إقليمي قوي!!

أعلنت إثيوبيا مؤخرًا عن إنجازاتها المزدوجة بشأن سد النهضة الإثيوبي الكبير. الأول هو بدء توليد الطاقة من التوربين الثاني والثاني الانتهاء من الجولة الثالثة لملء السد. وبعد جولات متتالية لملء المياه ، أصبح السد الآن يحتوي على 22 مليار متر مكعب من المياه ، أي أكثر من ربع السد بعد اكتماله وينتج 750 ميغاواط. كشفت السلطات أن البناء الإجمالي للسد قد وصل إلى 85٪ وسيتم الانتهاء منه بالكامل في العامين المقبلين.

جاء هذا الإنجاز التاريخي بعد صعوبات دبلوماسية وفنية ومالية شديدة هددت استمرارية بناء السد. أصبح خبر اكتمال ملء الجولة الثالثة وتوليد الطاقة التوربينية الثانية مصدر سعادة كبيرة واعتزاز وطني لجميع الإثيوبيين وأصدقاء إثيوبيا. حقا هذا نجاح كبير وانتصار وطني. يعرب حزب الحرية والمساواة عن أقصى درجات دعمه وفرحه للخطوة الكبيرة التي قطعها نحو الانتهاء من المشروع الكبير.

كما أعربت الحكومة الإثيوبية ؛ الهدف من بناء سد النهضة اقتصادي بحت. سد النهضة هو أحد الأدوات الاقتصادية لإثيوبيا للخروج من الفقر وتمكين البلاد من أن تكون واحدة من البلدان ذات الدخل المتوسط في المستقبل المنظور. إنه مشروع وطني يهدف إلى تحرير إثيوبيا ومواطنيها من أغلال الفقر المدقع والجوع. سد النهضة هو تعبير واضح عن شعب إثيوبيا لاستخدام مواردهم الطبيعية بطريقة عادلة ومنصفة ومعقولة.

يرمز سد النهضة إلى وحدة الشعب الإثيوبي ويعبر عن الإرادة السياسية القوية لقيادته. سد النهضة هو أحد المشاريع الوطنية الإستراتيجية التي تتكاتف فيها جميع القوى السياسية ، متجاوزة الخلافات السياسية والأيديولوجية ، وتظهر تضامنًا قويًا لإنجازها بنجاح. ساهم الإثيوبيون في الداخل والخارج بأموالهم ودرايتهم وعمالةهم وغير ذلك منذ بدء بناء السد. إن الإنجاز الكبير الذي حققه مشروع سد النهضة الآن هو نتيجة الجهود السياسية والدبلوماسية والمالية المشتركة لشعب وحكومات إثيوبيا التي بذلت في السنوات الإحدى عشرة الماضية.

لقد حظيت سياسة إثيوبيا الواضحة للحصول على حصة عادلة ومعقولة من مياه النيل بقبول ودعم كبير من المجتمع الدولي ، بما في ذلك بعض دول الشرق الأوسط والدول العربية. ومع ذلك ، منذ بداية هذا المشروع الوطني ، عارضت دول المصب ، وتحديداً مصر والسودان ، المشروع على الرغم من تأكيد إثيوبيا المتكرر للالتزام بقوانين الدولية والاتفاقيات الثلاثية المبرمة بين الدول الثلاث بما في ذلك اتفاقية الإطار التعاوني .(CFA) كما بذلت المؤسسات الأفريقية والدولية الأخرى جهودًا للتوسط وحل الخلاف الذي فشل بسبب الموقف العنيد والمتحدي لدول المصب.

أصبح سد النهضة ، الذي دخل مرحلته النهائية الآن ، حقيقة واقعة وتحول إلى أمل وطموح ليس فقط للأثيوبيين ولكن أيضًا لشعوب وحكومات الدول المجاورة. أصبح سد النهضة جزءًا لا يتجزأ من حياة جميع الإثيوبيين ؛ إنها تضيء منازل ملايين الأسر الإثيوبية الفقيرة ، وتوفر فرص عمل لمئات الآلاف من الشباب الإثيوبيين. خارج الحدود الإثيوبية ، تنتظر الدول المجاورة بفارغ الصبر الاستفادة من الطاقة الكهربائية الناتجة عن سد النهضة. يُعد توليد الطاقة المتوقع للسد 6 آلاف ميجاوات مساهمة كبيرة في تحقيق رؤية إفريقيا لإضاءة القارة وتحقيق طموح إفريقيا لقارة موحدة ومزدهرة.

في هذا المفترق التاريخي ، يتعين على دول المصب ، وتحديداً مصر والسودان ، مراجعة موقفها تجاه سد النهضة والبدء في الدخول في حوار بناء مع إثيوبيا للوصول إلى حل يربح فيه الجميع ويحل العداء السياسي. مرة أخرى ، يجب على شعوب وحكومات دول المصب أن تفهم حق إثيوبيا الطبيعي في الحصول على حصة عادلة من مياه النيل. لقد حان الوقت لاعتبار سد النهضة مشروعًا إقليميًا مشتركًا وفرصة لدعم مساعي التنمية للدول وكوسيلة نحو تكامل الاقتصادي إقليمي قوي.

ولتحقيق هذه الغاية ، يجب على دول المصب ، بما في ذلك السودان ومصر ، تنسيق الجهود مع إثيوبيا وإنهاء العداوات السياسية والدبلوماسية. يجب على حكومات هذه الدول والدول الأخرى في حوض النيل إعادة صياغة سياساتها باعتبار سد النهضة أمرًا واقع جديدًا.

**حزب الحرية والمساواة**
**16 أغسطس 2022.**
**(ነሀሴ 10፣ 2014)**
**اديس ابابا**

## GERD is an African Project and a means towards strong regional integration
## Downstream countries should coordinate efforts with Ethiopia

Ethiopia has recently announced its twin accomplishments on the Grand Ethiopian Renaissance Dam (GERD); the first is the start of power generation of the second turbine and the second is the completion of the third-round filling of the dam. After successive rounds of fillings, the dam now contains 22 billion $m^3$ of water, which is more than a quarter of the dam, and produces 750 MW. Authorities have disclosed that the overall construction of the dam has reached 85% and will be fully completed in the coming 2 years.

The historic accomplishment came after severe diplomatic, technical and financial difficulties which threatened the continuity of the construction of the dam. The news of the completion of the 3rd round filling and the 2nd turbine power generation has become a source of great joy and national pride for all Ethiopians and friends of Ethiopia. Indeed, this is an incredible hydro-political and hydro-diplomatic achievement. Freedom and Equality Party express its highest support and joy for the great stride made towards finalizing the grand project.

As expressed by subsequent Ethiopian governments the goal of constructing GERD is purely economic. GERD is one of Ethiopia's economic instruments to get out of poverty and enable the country to be one of the middle-income countries in the foreseeable future. It is a national project that aims to free Ethiopia and its citizens from the shackles of abject poverty and hunger. GERD is an unequivocal expression of the people of Ethiopia to utilize their natural resources in a fair, equitable, and reasonable way.

GERD symbolizes the unity of the Ethiopian people and expresses the strong political will of its leadership. The GERD is one of the strategic national projects where all political forces join hands, transcending political and ideological differences, and showing strong solidarity for its successful completion. Ethiopians at home and abroad have contributed their money, know-how, labor and more since the start of the construction of the dam. The high project achievement which GERD has reached now is the result of the joint political, diplomatic, and financial efforts of the people and governments of Ethiopia exerted in the last eleven years.

Ethiopia's clear policy for an equitable and reasonable share of the Nile waters has won huge acceptance and support from the international community including some Middle Eastern and Arab countries. However, since the inception of this mega national project, downstream countries, specifically Egypt and Sudan have been opposing the project despite Ethiopia's repeated assurance to abide by international water laws and tripartite agreements made among the three countries including the Cooperative Framework

Agreement (CFA). African and other international institutions have also exerted effort to mediate and resolve the disagreement, which has failed due to the stubborn and defiant position of the downstream countries.

The GERD, which is now in its final phase, has become a reality and turned out to be a hope and aspiration not only for Ethiopians but also for the people and governments of the neighboring countries. GERD has become part and parcel of the life of all Ethiopians; it is lighting the homes of millions of poor Ethiopian families, creating job opportunities for hundreds of thousands of Ethiopian youths. Beyond Ethiopian borders, neighboring countries are eagerly waiting to utilize the power generated by GERD. The expected 6 thousand MW power generation of the dam is a huge contribution towards Africa's vision to light the continent and realize Africa's ambition for a united and prosperous continent.

In this historic junction, downstream countries, specifically Egypt and Sudan, have to review their position vis-à-vis the GERD and start to engage in a constructive dialogue with Ethiopia to reach a win-win solution for the long-standing political hostility. Once again, the people and governments of the downstream countries should understand Ethiopia's natural right to have a fair share from the Nile water, and its commitment not to reduce the share of the lower stream countries. It is time to consider GERD as a joint regional project and as an opportunity to support the development endeavors of individual countries and as a means toward strong regional integration.

To this end, downstream countries, including Sudan and Egypt, should coordinate efforts with Ethiopia and end political and diplomatic hostilities. The governments of these countries and other countries in the Nile basin should reframe their policies taking GERD as a new normal.

**Freedom and Equality Party**
**15 August 2022. (ነሐሴ 9፣ 2014)**
**Addis Ababa**

# በቄለም ወለጋ በንጹሀን ላይ የደረሰውን ጭፍጨፋ ነኢፓ በጽኑ ያወግዛል!!

ከአስራ አምስት ቀን በፊት በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ወለጋ ዞን ጊምቢ ወረዳ በንጹሀን ላይ ጥቃት ተፈጽሞ ቁጥራቸው እጅግ ከፍተኛ የሆኑ ሰላማዊ ዜጎች ዘግናኝ በሆነ መንገድ በግፍ መጨፍጨፋቸው ይታወሳል። መላ የሀገራችን ህዝቦች ከዚህ መሪር ሀዘን ሳይወጡ በትላንትናው እለት በቄለም ወለጋ ዞን ሐዋ ገላን ወረዳ ሌላ ዙር የጅምላ ጭፍጨፋ ተካሂዷል። መላው **የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** አባላት እና አመራሮች በንጽህን ዜጎች ላይ በደረሰው አሳዛኝ ጭፍጨፋ የተሰማንን ጥልቅ ሀዘን እንገልጻለን።

ባለፉት አራት አመታት በተለያየ ጊዜ በተለይም በወለጋ ዞኖች በንጹሀን ላይ ተደጋጋሚ ጥቃት ደርሷል። በዚህ ምክንያት በሺዎች የሚቆጠሩ ህጻናት፣ ሴቶች እና አረጋውያን ለጅምላ ጭፍጨፋ፣ ለአካል ጉዳት እና ለስደት ተዳርገዋል። ከሞት የተረፉ ጥቂቶች እድሜ ልካቸውን አፈር ገፍተው ያፈሩትን ሀብት እና ንብረት በቅጽበት አጥተዋል። በደረሱት ጥቃቶች ህይወታቸውን ለማትረፍ በመስጂዶች የተጠለሉ ሴት፣ ህጻናት እና አቅመ ደካሞች እንኳ ሳይቀሩ ያለርህራሄ ተጨፍጭፈዋል።

ማባሪያ ያጣው የዜጎች ሞት፣ ስደት፣ እልቂት ዛሬም ቀጥሏል፣ የንጹሀን ደም እና እንባ ዛሬም ይፈሳል። ከቡር የሆነው የዜጎች ህይወት "ቁጥር" ሆኗል፤ በየአካባቢው በግፍ ለሚጨፈጨፉ ዜጎች በጥቂት መስመሮች መግለጫ ከማውጣት ያለፈ ትኩረት የሚሰጥ የመንግስት አካል ጠፍቷል፣ የክልል እና የፌዴራል መንግስታት በአራቱም የሀገራችን ማእዘናት በአሰቃቂ ሁኔታ በተደጋጋሚ በግፍ የሚጨፈጨፉ ዜጎችን ህይወት ለመታደግ አልቻሉም።

በዜጎች ላይ እየደረሰ ላለው የጅምላ ጭፍጨፋ ዋነኛ ተጠያቂ የዜጎችን ህይወት የመጠበቅ ህገ-መንግስታዊ ግዴታ ያለበት መንግስት ነው። ተጠያቂነትን ለመሸፋፈን የሚደረግ ውል የሌለው ማስተባበያ በማንኛውም መመዘኛ ተቀባይነት የለውም። **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በቄለም ወለጋ ዞን ሐዋ ገላን ወረዳ በንጹሀን ላይ የደረሰውን የጅምላ ጭፍጨፋ በጽኑ እያወገዘ፣

1. ትላንት በቄለም ወለጋ እና ከሳምንታት በፊት በጊምቢ ወረዳ የደረሰው ጭፍጨፋ በገለልተኛ አካል ተጣርቶ ውጤቱ በአፋጣኝ ለህዝብ ይፋ ይሆን ዘንድ መንግስት አስፈላጊውን እንዲያደርግ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ጥሪውን ያቀርባል፣
2. ባለፉት ጥቂት አመታት በተለያዩ የወለጋ አካባቢዎች በንጽህን ላይ በደረሰው ተደጋጋሚ ጥቃት ቁጥሩ እጅግ ከፍተኛ ህዝብ አልቋል። በቀጣይም ተመሳሳይ ጥቃቶች ላለመድረሳቸው እርግጠኛ መሆን አይቻልም። በመሆኑም ታጣቂዎች በዜጎች ላይ የሚያደርሱትን ጥቃት ለመከላከል በተለይም የፌዴራል መንግስት የደህንነት አካላት በተቀናጀ መንገድ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ **ነኢፓ** ጥሪውን ያቀርባል፣
3. በአካባቢው በተደጋጋሚ ጥቃት የደረሰባቸው ዜጎች ከተለያዩ የአማራ ዞኖች በተለይም ከወሎ አካባቢ በሰፈራ የሄዱ መሆናቸው ይታወቃል። በመሆኑም መንግስት እነዚህ ዜጎች ባሉበት አካባቢ በሰላም እንዲኖሩ ደህንነታቸውን መጠበቅ ካልቻለ፣ የፌዴራል መንግስት ከኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች ጋር በመቀናጀት ችግሩ ዘላቂ መፍትሄ የሚያገኝበትን አማራጭ እንዲፈልግ **ነኢፓ** ጥሪውን ያቀርባል፣
4. የዜጎችን ደህንነት ለመጠበቅ የፌዴራል እና የክልል የጸጥታ ኃይሎች ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ በተጨማሪ፣ ለአደጋ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩ ዜጎች ተደራጅተው ራሳቸውን ከታጣቂዎች የሚጠበቁበት አሰራር ሊዘረጋ ይገባል።

በመሆኑም ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ተደጋጋሚ ጥቃት በደረሰባቸው አካባቢዎች የሚኖረው ማህበረሰብ ራሱን መከላከል የሚችልበት አሰራር እንዲፈጠር መንግስት ኃላፊነቱን እንዲወጣ **ነኢፓ** አጥብቆ ያሳስባል፣

5. ላለፉት ሶስት አስርት አመታት በብልሹ አሰራር በተጨማለቀ የመንግስት መዋቅር ውስጥ በሀገር ሰላም እና ደህንነት እንዲሁም በዜጎች ሞት እና ስቃይ የሚነግዱ በመንግስት መዋቅር ውስጥ የተሰገሰጉ ጸረ ሰላም እና ጸረ ህዝብ ኃይሎች ስላለመኖራቸው እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ በመሆኑም በተለይም የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በወለጋ አካባቢ በዜጎች ላይ በተደጋጋሚ የደረሰው ጥቃት ዳግመኛ እንዳይከሰት ለመከላከል በክልሉ ልዩ ልዩ ተቋማት ያለውን የሰው ኃይል በጥንቃቄ እንዲፈትሽ ነኢፓ ጥሪ ያቀርባል፣
6. በመጨረሻም በየአካባቢው የሚከሰቱ ግጭቶች እና በዜጎች ላይ የሚደርሱ ኢ-ሰብአዊ ጥቃቶች በሀገራችን ያለው የተካረረ የፖለቲካ ስርአት መገለጫዎች ናቸው፡፡ መንግስትን መንግስት ከሚያደርጉት ምሰሶዎች አንዱ እና ዋነኛው የዜጎችን ህይወት መጠበቅ ሲሆን፣ መንግስት ይህንን መሰረታዊ ኃላፊነት መወጣት ካልቻለ መሰረታዊ የመንግስትነት ባህሪውን እንዳጣ ይቆጠራል፡፡ በመሆኑም የዜጎችን ሰላም እና ደህንነት በመጠበቅ ረገድ ተደጋጋሚ አቅመ ቢስነት ያሳየው መንግስት፣ ችግሩን ከሌሎች የፖለቲካ ኃይሎች ጋር በመተባበር እና በመቀናጀት በዜጎች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ለማቆም የሚያስችል የአሰራር ስርአት እንዲዘረጋ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በጽኑ ያሳስባል።

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ሰኔ 28፣ 2014**
**አዲስ አበባ**

# ነኢፓ በወሊጋ ዞን ሰላማዊ ዜጎች ላይ የደረሰውን የጅምላ ጭፍጨፋ በጽኑ ያወግዛል!!

በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ወሊጋ ዞን ጊምቢ ወረዳ ቶሌ ቀበሌ በንጹሀን ላይ ጥቃት እንደተፈጸመ እና በጥቃቱም በርካታ ሰላማዊ ዜጎች በግፍ እንደተገደሉ የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ያስታወቀ ሲሆን፣ ጥቃቱን የተለያዩ ዓለም አቀፍ የዜና አውታሮችም ዘግበውታል፡፡ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በየትኛውም ቦታ እና ጊዜ በንጹሀን ዜጎቻችን ላይ የሚደርስን ጥቃት በእጅጉ የሚያወግዝ ሲሆን በጊምቢ ወረዳ ቶሌ ቀበሌ በግፍ በተጨፈጨፉ ወገኖች የተሰማውን ጥልቅ ሀዘን ይገልጻል፡፡

በሀገራችን በተለይም ባለፉት ጥቂት አመታት በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች እጅግ አሰቃቂ ጥቃቶች በሰላማዊ ዜጎች ላይ የተፈጸሙ ሲሆን ይህም ችግር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ መጥቷል፡፡ የክልልም ሆነ የፌዴራል መንግስታት በዜጎች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ማስቆም አልቻሉም፡፡ መንግስት በዜጎች ላይ ጥቃት፣ ግድያ እና መፈናቀል በሚፈፅሙ አካላት ላይ የህግ የበላይነትን በሚያረጋግጥ መልኩ የተፋጠነ ህጋዊ እርምጃ መውሰድ አለመቻሉ ተደጋጋሚ አሰቃቂ እና ዘግናኝ ግድያዎች እንዲፈጸሙ ምክንያት ሆኗል፡፡ በሰላማዊ ዜጎች ላይ ኢ-ሰብአዊ በሆነ መንገድ የሚፈጸሙ የጅምላ ጭፍጨፋዎች፣ ግድያዎች ሀገራችንን ወደ ለየለት ቀውስ እና የእርስ በርስ ግጭት እየገፋት ይገኛል፡፡

መቋጫ ያጣው የዜጎች ሞት፣ ስደት እና የጅምላ ጭፍጨፋ ዛሬም በወሊጋ የበርካታ ሰላማዊ ዜጎችን ህይወት አስከፍሎናል፡፡ መንግስት የዜጎችን ሰላም እና ደህንነት የመጠበቅ ህገ መንግስታዊ ግዴታውን በመጠቀም በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በጋምቤላ፣ በቤኒሻንጉል እና በሌሎችም የሀገራችን አካባቢዎች በሰላማዊ ዜጎች ላይ የሚደርሰውን ግፍ እንዲያስቆም፣ በተለያዩ አካባቢዎች በሰላማዊ ዜጎች ላይ ዘግናኝ ጭፍጨፋ የሚፈፅሙ አካላትን መንግስት በአፋጣኝ ለህግ እንዲያቀርብ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ጥሪውን ያቀርባል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ሰኔ 13፣ 2014፣**
**አዲስ አበባ**

# ከነኢፓ ስራ አፈጻሚ ኮሚቴ በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የተሰጠ መግለጫ

እየተገባደደ ያለው ዓመት ሀገራችን አያሌ የሰላም፣ የምጣኔ ሀብት፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ የውጭ ግንኙነት ውጣ ውረዶች ያስተናገደችበት ዓመት ነው። ሙሉ ለሙሉ ያልተቋጨው የሰሜኑ ጦርነት፣ በተለያዩ ክልሎች የተከሰቱ እና ከፍተኛ የህይወት እና የንብረት ዋጋ ያስከፈሉ፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን ከመኖሪያ አካባቢያቸው ያፈናቀሉ ግጭቶ፣ የማክሮ ኢኮኖሚ መናጋት፣ የዜጎችን ጀርባ ያጎበጠ ከፍተኛ የኑሮ ውድነት፣ ታሪካዊ ቁርሾ እና ቂም በቀልን አስወግዶ ሀገራዊ ሰላም እና አንድነትን ለማረጋገጥ በተጀመረው የሀገራዊ ምክክር ዙሪያ በፖለቲካ ልሂቃን መካከል የተፈጠረው እሰጣገባ እና በሂደቱ ላይ ያሳደረው አሉታዊ ተጽእኖ፣ 'ድህረ ጦርነት' አስቸኳይ የነፍስ አድን ዘመቻ እና ዘላቂ መልሶ ግንባታ መስተጓጎል፣ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት እና የዜጎች በሰላም ወጥቶ የመግባት ስጋት፣ በጠራራ ጸሀይ በከተሞች የተንሰራፋው ዘረፋ እና ነጠቃ፣ እና ሌሎች ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ሀገራችን ያለችበትን ተጨባጭ ከብዙ በጥቂቱ የሚያሳዩ ሀቆች ናቸው።

በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ያሉ ግጭቶች ዜጎች በስጋት ውስጥ እንዲኖሩ ያደረገ ሲሆን፣ የተፈጠረው ከባድ የኑሮ ውድነት በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ቤተሰቦች ላይ ከፍተኛ ጫና አሳድሯል። በሀገራችን የሚታዩት ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮች ውስብስብ እና መዋቅራዊ ይዘት ያላቸው ሲሆኑ፣ ባለፉት ጥቂት አመታት ተባብሰው ቀጥለዋል። በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተለኮሰው ጦርነት በሀገራችን በሁሉም ዘርፎች ያሉትን ችግሮች ይበልጥ ከማባባሱም በተጨማሪ እንዲወሳሰቡ አድርጓል።

በአንጻሩ መንግስት እየተስተዋሉ ያሉትን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና የሰላም ችግሮች ለመቅረፍ 'ተአምራዊ ስኬቶችን አስመዝግቢያለሁ' ቢልም ይህ የመንግስት አቋም መሬት ላይ ካሉት ችግሮች አንጻር ለበርካታ የሀገራችን ዜጎች **'ላም አለኝ በሰማይ'** አይነት ሆኗል። የዳቦ እና የዘይት፣ የስኳር፣ የአትክልት እና ፍራፍሬ፣ እንዲሁም የነዳጅ እና የቤት ኪራይ ዋጋ ወዘተ ለአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል አልቀመስ ባለበት በአሁኑ ወቅት በመንግስት የሚሰጡ መግለጫዎች እውነታን ተቀብሎ ለችግሮቹ ዘላቂ መፍትሄ ለማበጀት በመንግስት በኩል ያለውን አነስተኛ ዝግጁነት እና ተነሳሽነት ያሳያል።

በፌዴራልም ሆነ በክልል መንግስታት የመልካም አስተዳደር ስርአት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መድረሱን ጥናቶች ያሳያሉ፣ ዜጎች ይመሰክራሉ። ቀላል የማይባሉ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት በጥቅም ትስስር፣ በትውውቅ፣ በአምቻ ጋብቻ፣ በጉቦና እና በጥቅማ ጥቅም መስራት እጅግ የተለመደ እና "መደበኛ" አሰራር ሊሆን ምንም አልቀረው። መንግስት በብልሹ አሰራር የተዘፈቁ መስሪያ ቤቶችን አስመልክቶ በቂ መረጃ እንዳለው በአደባባይ ቢያሳውቅም ችግሩን ከስሩ ለመፍታት ያሳየው ተነሳሽነት እና ቁርጠኝነት ሲበዛ አናሳ ነው።በዚህም ምክንያት እጅግ በተንዛዛ እና ብልሹ አሰራሮች የዜጎች ሰቆቃ እና እንግልት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከተ መጥቷል።

**የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሰኔ **11**፣ 2014 ባደረገው መደበኛ ስብሰባ ከላይ በአጭሩ የተጠቀሱትን ጨምሮ የሀገራችንን ወቅታዊ ሁኔታ በስፋት እና በጥልቀት ከመረመረ እና ከገመገመ በኃላ፣

1. በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተካሄደውን ጦርነት እና አሁንም ድረስ ያልረገበውን ውጥረት በሰላማዊ መንገድ ለመቋጨት መንግስትም ሆነ የትግራይ ኃይሎች ፍላጎት እንዳላቸው እና ለዚህም ዝግጅት በማድረግ ላይ መሆናቸውን በተለያዩ አጋጣሚዎች ገልጸዋል። **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** የፖለቲካ ልዩነት በዘላቂነት ሊፈታ የሚችለው በጠረጴዛ ዙሪያ እና

በድርድር እንደሆነ የሚያምን ሲሆን፣ ይህንኑ አቋሙን ግጭቱ ከተፈጠረበት ጊዜ አንስቶ ሲያስተጋባ ቆይቷል። ከዚህ ጽኑ የሰላም አሳቤ በመነሳት፣ ሀገራችንን እጅግ ውድ ዋጋ ያስከፈላት ጦርነት ሙሉ ለሙሉ ቆሞ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ሰላም እንዲሰፍን ለሚደረግ ተነሳሽነት **ነኢፓ** ጠንካራ ድጋፍ የሚሰጥ ሲሆን፣ ለሰላም ውጥኖች ተፈጻሚነት አቅሙ የሚፈቅደውን ድጋፍ ያደርጋል። ከዚህ አኳያ የፌዴራል መንግስት እና የትግራይ ኃይሎች ጦርነቱን በድርድር ለመቋጨት ያሳዩት ፈቃደኝነት በአፋጣኝ ወደ ተግባር ተለውጦ ድርድሩ በአጠረ የጊዜ ሰሌዳ እንዲጀመር **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ጥሪውን ያቀርባል፣

2. ሁሉን አካታች ሀገራዊ ምክክር በማድረግ የሀገራችንን ታሪካዊም ሆነ የቅርብ ጊዜ ችግሮች ለመፍታት፣ የሀገረ መንግስቱን ሰላም እና አንድነት እየተፈታተኑ ያሉ ስር የሰደዱ አለመግባባቶችን ለመቅረፍ በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ማህበራት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ከፍተኛ እንቅስቃሴ ሲያደጉ መቆየታቸው ይታወሳል። በዚህ ሂደት ውስጥ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** የድርሻውን ለማበርከት ከፍተኛ እንቅስቃሴ አድርጓል። ይሁን እንጂ ባለፉት ጥቂት ወራት የሀገራዊ ምክክሩን በገለልተኛ አካል ለማካሄድ በሚል የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ተቋቁሞ የቅድመ ዝግጅት ስራ እየተከናወነ ሲሆን፣ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በሂደቱ ገለልተኝነት፣ ግልጸኝነት፣ ነጻነት እና ተአማኒነት ላይ ያላቸውን ስጋት እየገለጹ ይገኛሉ። በሀገራችን ሊካሄድ ለታሰበው ብሄራዊ መግባባት ስኬታማነት የሂደቱ ዋና ተዋናኝ በሆኑ የፖለቲካ ኃይሎች መካከል መተማመን እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ መተማመንን የሚሸረሽሩ ተግባራትን ማስወገድ ለድርድር ሊቀርብ አይገባም። ይህ ሁኔታ በዚሁ ከቀጠለ ትልቅ ተስፋ የተጣለበት የሀገራዊ ምክክር እንዳይሰናከል ከፍተኛ ስጋት አድሮብናል። በመሆኑም መንግስት ከሂደቱ ጋር በተያያዘ ከተለያዩ አካላት ለሚነሱ ጥያቄዎች ጆሮ በመስጠት እና አስፈላጊ ማስተካከያዎች በማድረግ የሀገራዊ ምክክሩ ስኬታማ ይሆን ዘንድ ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ እናሳስባለን። በተመሳሳይ የተቋቋመው የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ከሀገራዊ ምክክሩ ማንም እንዳይገለል እና ሂደቱ ሁሉን አሳታፊ እንዲሆን አስፈላጊውን ሁሉ ሊያደርግ ይገባል።

3. በመሰረታዊ ሸቀጦች ላይ የታየው ከፍተኛ የዋጋ ንረት በአብዛኛው ህዝባችን ላይ ከፍተኛ የኑሮ ውድነትን አስከትሏል። ለተፈጠረው የዋጋ ውድነት የተለያዩ ውስጣዊ እና ዓለም አቀፋዊ ምክንያቶች ቢኖሩትም፣ የመንግስት ተቋማት ብልሹ አሰራር፣ ቅጥ ያጣ የንግድ ስርአት፣ ደካማ የመንግስት ገቢያን የመቆጣጠር አቅም፣ መረን የለቀቀ ሙስና፣ ስርአት አልበኝነት የተጠናወተው የመሬት አስተዳደር ችግሩን ይበልጥ አባብሰውታል። እውነታው ይህ ሆኖ እያለ የመንግስት ተቋማት የተፈጠሩትን አስተዳደራዊ የአሰራር ክፍተቶችን  አምኖ ተገቢ የእርምት እርምጃ ለመውሰድ ጥረት ከማድረግ ይልቅ፣ ችግሩ በጥቅሉ ዓለም አቀፋዊ እንደሆነ ለማሳየት እየሞከሩ ይገኛሉ። **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በሀገራችን የተፈጠረው ከፍተኛ የዋጋ ንረት እና የኑሮ ውድነት መሰረታዊ ምክንያት የፖሊሲ፣ አስተዳደራዊ እና የሀገራችንን ተጨባጭ ያላገናዘበ የመንግስት የወጪ ስርአት እንደሆነ በጽኑ ያምናል። በመሆኑም መንግስት የተፈጠረውን ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት ለመቀነስ ተጨባጭ የፊሲካል (የመንግስት ገቢ እና ወጪ) እና የገንዘብ ፖሊሲ ማሻሻያዎችን እንዲያደርግ ጥሪ እናቀርባለን፣

4. ከላይ በተጠቀሱት ችግሮች ማለትም ጦርነት፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ ከፍተኛ የዋጋ ንረት፣ ግጭት እና መፈናቀል ወዘተ ከፉኛ ከተጎዱ ዘርፎች አንዱ የሀገራችን ግብርና ነው። ወትሮም የዝናብ ጥገኛ የሆነው የግብርና ሴክተር፣ በግብአት

እጥረት፣ በመሬት ይዞታ መበጣጠስ፣ በባህላዊ የአሰራር ስርአት፣ ዝቅተኛ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ወዘተ ምርታማነቱ እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ሀገራችን ከፍተኛ የምግብ ዋስትና ችግር ካለባቸው የዓለም ሀገራት አንዷ ሆናለች፡፡ በቅርቡ ይፋ የተደረጉ ዓለም አቀፍ ጥናቶች ሀገራችን በቀጣይ አመት ከፍተኛ የምግብ ዋስትና እጥረት ሊገጥማት እንደሚችል ስጋታቸውን ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም ሀገራችን ያለባትን ከፍተኛ የምግብ ዋስትና ስጋት እና በቀጣይ አመት ሊያጋጥም የሚችለውን አደጋ ለመታደግ በያዝነው የመኸር ወቅት ማዳበሪያ እና ምርጥ ዘርን ጨምሮ ሌሎች የግብርና ግብአቶች በተመጣጣኝ ዋጋ በወቅቱ ለገበሬው እንዲደርሱ የፌዴራል እና የክልል መንግስታት የድርሻቸውን እንዲወጡ እናሳስባለን፣

5. የነዳጅ ዋጋ ማሻቀብ በሀገራችን ለተከሰተው የሸቀጦች እና የአገልግሎቶች ዋጋ ማሻቀብ አንዱ ምክንያት ሲሆን የነዳጃ ዋጋን ለማረጋጋት መንግስት ከፍተኛ ድጎማ ሲያደርግ መቆየቱ የታወሳል፡፡ ይሁን እንጂ የነዳጅ ዋጋ ድጎማው በአጠቃላይ የመንግስት በጀት ላይ የፈጠረውን ከፍተኛ ጫና ለመቀነስ መንግስት ለነዳጅ የሚያደርገውን ድጎማ ካለፉት ወራት ጀምሮ ደረጃ በደረጃ መቀነስ መጀመሩ ይታወቃል፡፡ የነዳጅ ዋጋ ድጎማ ሙሉ ለሙሉ ሲነሳ ሁሉም የነዳጅ ምርቶች ዋጋ አሁን ካለበት ከእጥፍ በላይ እንደሚጨምር ይጠበቃል፡፡ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በመርህ ደረጃ ነጻ ገበያ እና ውድድር ለጤናማ ምጣኔ ሀብታዊ እድገት የተሻለ አሰራር መሆኑን ቢቀበልም፣ የነዳጅ ድጎማው የሚነሳበት አግባብ ከፍተኛ ጥንቃቄ እና ጥናት የሚፈልግ መሆኑን ያምናል፡፡ በተለይም ሀገራችን ገና ያልተቋጨ እጅግ አውዳሚ ከሆነ ጦርነት ለማገገም ጥረት በማድረግ ላይ ባላችበት እና ዜጎች እጅግ በከፋ ድህነት እና የኑሮ ውድነት እየተሰቃዩ ባሉበት ወቅት የነዳጅ ድጎማውን ሙሉ ለሙሉ ማንሳት ምጣኔ ሀብታዊ ችግሮቻችንን ይበልጥ እንዳያከብደው መንግስት የነዳጅ ድጎማውን ሙሉ ለሙሉ ለማንሳት ያስቀመጠውን የጊዜ ሰሌዳ በጥንቃቄ እንዲከልስ እንጠይቃለን፣

6. በሰሜኑ የሀገራችን የተካሄደው ጦርነት በአፋር፣ አማራ እና ትግራይ ክልሎች ላይ ከፍተኛ ሰብአዊ እና ቁሳዊ ውድመት አስከትሏል፡፡ በጦርነቱ ምክንያት የተፈናቀሉ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች ዛሬም ድረስ እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን፣ ቀጣዮቹ የክረምት ወራት የእነዚህን ዜጎቻችንን ችግር ይበልጥ የከፋ ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም የክልል እና የፌዴራል መንግስት ተቋማት እንዲሁም የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በጦርነቱ ክፉኛ ለተጎዱ አካላት የሚያደርገውን የአስቸኳይ ጊዜ ሰብአዊ ድጋፍ አጠናክረው እንዲቀጥሉ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ጥሪውን ያቀርባል፡፡ ከዚህ አንጻር በዓለም የምግብ ፕሮግራም እና ሌሎች ዓለም አቀፍ ተቋማት ለትግራይ ክልል እያደረገው ያለው ድጋፍ የሚያበረታታ ሲሆን፣ ከዚህ ጎን ለጎን በአፋር እና አማራ ክልል በጦርነቱ ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች አስቸኳይ እና በቂ እርዳታ እና ድጋፍ እንዲደረግላቸው እንጠይቃለን፣

7. ባለፉት ጥቂት ወራት በመካከለኛው ምስራቅ በተለይም በሳውዲ አረቢያ እስር ቤቶች በአስቸጋሪ ሁኔታ የሚገኙ ወገኖቻችን ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ መንግስት ጥረት ሲያደርግ መቆየቱ ይታወሳል፡፡ በዚሁ መሰረት እስከ አሁን ከ36ሺ በላይ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው መመለስ ችለዋል፡፡ መንግስት ዜጎቻችንን ወደ እናት ሀገራቸው ለመመለስ እስከ አሁን እያደረገ ያለው ጥረት የሚደነቅ ሲሆን፣ ይህ ተግባር ተጠናክሮ አሁንም በከፍተኛ ችግር ውስጥ የሚገኙ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎቻችን ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ መንግስት አስፈላጊውን እንዲያደርግ **ነእፓ** ጥሪውን

ያቀርባል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ወደ ሀገራቸው ለተመለሱ ዜጎች መንግስት እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርጉላቸው ጥሪ እናቀርባለን፣

8. በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በጋምቤላ እና በቤኒሻንጉል የተለያዩ አካባቢዎች በመንግስት የጸጥታ ኃይሎች እና በታጣቂዎች መካከል ግጭቶች እየተካሄዱ እንደሆነ መንግስት በተለያዩ ኦጋጣሚዎች ገልጿል፡፡ **ነእፓ** ኃይል የመጠቀም መብት ሊኖረው የሚገባው መንግስት ብቻ እንደሆነ ያምናል፡፡ ይሁን እንጂ የመንግስት የደህነነት ተቋማት ህግን የማስከበር ግዴታቸውን በሚወጠቡት ወቅት የህግ የበላይነትን የማክበር እና በሰላማዊ ዜጎች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ተገቢውን ጥንቃቄ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡ ከዚህ አንጻር በተለያዩ ጊዜያት እና ቦታዎች ዜጎች እጅግ አሰቃቂ በሆነ መንገድ በጅምላ ሲገደሉ የሚያሳዩ መረጃዎች እጅግ አሳዛኝ እና አስፈሪ ናቸው፡፡ የጸጥታ አስከባሪ ኃይሎች በተጠርጣሪዎች ላይ ተገቢውን የፍትህ ስርአት ባልጠበቀ መልኩ የሚወስዱት እርምጃ፣ የሀገርን አንድነት የሚንድ፣ ዜጎች በጸጥታ ተቋማት ላይ ያላቸው እምነት ክፉኛ የሚሸረሽር እና የህዝብን ስነ ልቦና የሚረብሽ አደገኛ ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም የፌደራልም ሆነ የክልል መንግስታት በዜጎች ላይ ያልተገባ ጉዳት በሚፈጽሙ የጸጥታ አካላት ላይ ፈጣን እና ተገቢው የዲሲፕሊን እርምጃ እንዲወስዱ ነእፓ ያሳስባል፡፡

9. የሰብአዊ መብት አያይዝ እና ሀሳብን በነጻ የመግለጽ መብት መረጋገጥ ከአራት አመት በፊት በሀገራችን ለተጀመረው ‘ሪፎርም’ ዋነኛ ገፊ ምክንያቶች ነበሩ፡፡ እነዚህ የሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ‘በለውጡ’ ማግስት አንጻራዊ መሻሻል የታየባቸው ቢሆኑም፣ የለውጥ ሂደቱ መንፈቅ ሳይቆይ በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የመሰረታዊ መብቶች መሸራረፍ በስፋት መስተዋል ጀምሯል፡፡ በማንኛውም ወንጀል ተጠርጥሮ በህግ የሚፈለግ ግለሰብ ለፍርድ የሚቀርብበት ህገ መንግስታዊ አግባብ ሊጠበቅ ይገባል፡፡ በተመሳሳይ መንግስት ዜጎች ሀሳባቸውን በነጻ የመግለጽ ህገ መንግስታዊ መብታቸው እንዳይሸራረፍ የማክበር እና የማስከበር ኃላፊነት እና ግዴታ አለበት፡፡ በመሆኑም መንግስት በማንኛውም ሁኔታ እና ምክንያት የዜጎች ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዳይሸራረፉ፣ ተጠርጣሪዎች ከህግ እና ደንብ ውጪ የአካልም ሆነ የስነልቦና ጉዳት እንዳይደርስባቸው እና የፍርድ ቤት ውሳኔዎች እንዲከበሩ ህገ መንግስታዊ ግዴያውን እንዲወጣ እናሳስባለን፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ሰኔ ፲፩ 2014፣**
**አዲስ አበባ**

# በሰሜን ኢትዮጵያ ያንጥበበውን የጦርነት ስጋት አስመልክቶ ከነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የተሰጠ መግለጫ!!

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል አንድ አመት ከግማሽ በላይ የዘለቀው ጦርነት ለጥቂት ወራት ጋብ ካለ በኃላ ሰሞኑን በአካባቢው ዳግም ግጭት እንዳይቀሰቀስ ከፍተኛ ስጋት ተፈጥሯል። ከ2013 መባቻ ጀምሮ የተቀሰቀሰው ጦርነት በሀገራችን ላይ እጅግ ከፍተኛ እና ዘርፈ ብዙ ጉዳት አድርሷል። በጦርነቱ ሀገራችን ከከፈለችው ከፍተኛ ዋጋ በዜጎች ላይ የደረሰው ሞት፣ የአካል ጉዳት እና የስነልቦና ስብራት እጅግ አሰቃቂው እና አሳዛኙ ነው። ጦርነቱ የሀገራችን ተስፋዎች የነበሩ ወጣቶችን ህይወት ቀጥፏል፣ አረጋውያንን ያለ ጧሪ፣ ህጻናትን ያለ አሳዳጊ አስቀርቷል። ጦርነቱ በዜጎች ላይ ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰት እንዲፈጸም ምክንያት ሆኗል፣ በዜጎች ማህበራዊ ትስስር ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል።

የጦርነቱ ኢኮኖሚያዊ ጉዳት በሀገራችን ታሪክ ወደር አልተገኘለትም። ጦርነቱ ሰፊ የሀገራችን አንጡራ ሀብት ፈሶባቸው የተገነቡ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መሰረተ ልማቶችን አውድሟል። በተጎሳቆለ ምህዳይ ላይ ይካሄድ የነበረው የአካባቢው የግብርና እንቅስቅሴ በጦርነቱ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት ሲሆን፣ አርሰው የሚያበሉ የገበሬ እጆች ለልመና ተዘርግተዋል፣ የአርብቶ አደሩ የኑሮ ዋስትና የሆኑት እንስሳት የጦርነቱ ሰለባ ሆነዋል። ጦርነቱ ከፍተኛ የኑሮ ውድነት፣ ስራ አጥነት፣ የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት፣ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እጥረት እና የውጭ እዳ ጫና እና ቀውስ አስከትሏል። ጦርነቱ የሀገራችንን የውጪ ግንኙነት በእጅጉ የጎዳ ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ ገጽታችንን አጠልሽቶታል። በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጎች በመጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ እግጅ አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ይገኛሉ።

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተካሄደው ጦርነት እነዚህ እና ሌሎች በርካታ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ጉዳቶችን ያስከተለ ሲሆን የሰሜኑ ጦርነት በሌሎች የሀገራችን አካባቢዎች ካሉ ግጭቶች ጋር ተዳምሮ ሀገራችንን ከፍተኛ ቀውስ ውስጥ አስገብቷታል። ጦርነቱን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የተለያዩ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ተቋማት ባደረጉት ግፊት ባለፉት ጥቂት ወራት በአካባቢው አንጻራዊ መረጋጋት የተፈጠረ ቢሆንም፣ ሰሞኑን ከአካባቢው የሚወጡ መረጃዎች ሀገራችን ዳግም ወደ ግጭት እንዳትመለስ ከፍተኛ ስጋት ፈጥሯል።

ባለፈው አንድ አመት ተኩል በተካሄደው ጦርነት ሀገራችን ከደረሰባት ሰብአዊ፣ ቁሳዊ እና የስነልቦና ስብራት ሳታገግም ለዳግም ግጭት መነሳት በማንኛውም መመዘኛ ተቀባይነት የለውም። ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም አይታ በማታውቀደው ደረጃ የጦርነትን አስከፊነት የቀመሰችበት ጦርነት ዳግም እንዲቀሰቀስ መፍቀድ ታሪክ ይቅር የማይለው ከፍተኛ ስህተት ነው።  በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ዳግም ያንጥበበው የጦርነት ዳመና ሙሉ ለሙሉ እንዲገፈፍ የፌዴራሉ መንግስት እና የትግራይ ኃይሎች ከፍተኛ እና ታሪካዊ ኃላፊነት አለባቸው፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በሰሜኑ** የሀገራችን ክፍል ሌላ ዙር ጦርነት እንዳይቀሰቀስ ከፍተኛ ስጋት ያደረበት ሲሆን፣ ያንጥበበው የጦርነት አደጋ ተቀርፎ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል አስተማማኝ እና ዘላቂ ሰላም ይረጋገጥ ዘንድ ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ጥሪውን ያስተላልፋል። **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** የተፈጠረውን የጦርነት ስጋት ማስወገድ ይቻል ዘንድ፣

- በዚህ ጦርነት ከፍተኛ ጉዳት ከደረሰባቸው ክልሎች አንዱ ትግራይ ሲሆን በጦርነቱ የክልሉ ህዝብ ከፍተኛ ሰብአዊ እና ቁሳዊ ጉዳት ደርሶበታል። በክልሉ እና በህዝቡ ላይ የደረሰው ከፍተኛ ጉዳት ዘላቂ ሰላም በመፍጠር በአፋጣኝ ሊቀየር ይገባል። በመሆኑም ትግራይን በማስተዳደር ላይ ያሉ ኃይሎች በትግራይ ህዝብ ላይ የደረሰውን ከፍተኛ ጉዳት ለመቀነስ እና በክልሉ ላይ ያንዣበበውን የጦርነት ስጋት ለመግታት ዳግም ወደ ጦርነት ከሚያመሩ ወታደራዊ፣ ፖለቲካዊ እና የሚዲያ እንቅስቃሴዎች እንዲቆጠቡ፣ በአንጻሩ ለሰላም መረጋገጥ የድርሻቸውን እንዲወጡ፣

- በጦርነቱ ምክንያት በትግራይ ክልል የተፈጠረውን ከፍተኛ የምግብ፣ የመድሀኒት እና ሌሎች ቁሳቁሶች ችግር ለመቅረፍ የፌዴራል መንግስት አስቸኳይ ሰብአዊ ድጋፍ ወደ ክልሉ እንዲገባ መፍቀዱ ይታወሳል። በዚሁ መሰረት የፌዴራል መንግስቱ ምግብ፣ መድሀኒት እና ሌሎች ሰብአዊ ድጋፎች በበቂ ሁኔታ ወደ ክልሉ እንዲደርስ አስፈላጊውን እንዲያደርግ፣

- የፌዴራሉ መንግስት፣ እንዲሁም የአማራ እና የአፋር ክልላዊ መስተዳድሮች እና የትግራይ ኃይሎች የተፈጠረውን ዳግም ወደ ጦርነት የመመለስ አደጋ ለማስወገድ እና ችግሩን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚጠበቅባቸውን እንዲያደርጉ፣ የፌደራል መንግስት ጦርነቱ በሰላማዊ መንገድ እና በድርድር እንዲያልቅ የድርድር ፍኖተ ካርታ አዘጋጅቶ በአስቸኳይ ወደ ተግባራዊ እርምጃ እንዲገባ፣

- የሀገር ሽማግሌዎች፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ማህበራት፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ በውጭ ሀገራት የምትገኙ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን፣ ባለሀብቶች፣ የተፈጠረውን የግጭት ስጋት ለማስወገድ የድርሻቸሁን እንድታበረክቱ፣ የሚዲያ ተቋማት እና አክቲቪስቶች ካለፈው ትምህርት በመውሰድ ግጭት ቀስቃሽ የሆኑ መልእክቶችን ከማሰራጨት በመቆጠብ እና ሰላምን በማቀንቀን ሀገራችን ዳግም ወደ ጦርነት እንዳትገባ ሙያዊ ግዴታችሁን ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ እንድትወጡ፣

- በመጨረሻም በማንኛውም ሁኔታ ለሚቀሰቀስ የእርስ በርስ ጦርነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ትልቅ ዋጋ የሚከፍሉት ዜጎች ናቸው። ከአንድ አመት በላይ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተካሄደው ጦርነት ትልቅ ዋጋ የከፈሉትም መላው የሀገራችን ህዝቦች ናቸው። በመሆኑም በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ያንዣበበው የጦርነት ስጋት ተወግዶ ሰላም እንዲረጋገጥ መላው የሀገራችን ህዝቦች ጦርነትን በማውገዝ እና የሰላምን አርማ ከፍ አድርጎ በማውለብለብ ሰላም እንዲሰፍን የበኩላችሁን እንድትወጡ **ነኢፓ** ጥሪውን ያቀርባል።

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ግንቦት 8፣ 2014**
**አዲስ አበባ**

# በደቡብ ክልል በአብያተ ክርስቲያናት ላይ የደረሰውን ጥቃት አስመልክቶ ከነኢፓ የተሰጠ መግለጫ

## "እሳት በውሃ እንጂ በእሳት አይጠፋም!!"

በአማራ ክልል በጎንደር እና በደባርቅ ከተሞች በመስጂዶች እንዲሁም በሙስሊሞች ህይወት፣ ሀብትና ንብረት ላይ የደረሰውን ጥቃት ተከትሎ በተለያዩ የሀገራችን አከባቢዎች መላው የሀገራችን ህዝቦች፤ የሀይማኖት ተቋማት፤ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማህበራት ድረጅቶች፣ ታዋቂ ግለሰቦች እና የመንግስት አካላት አውግዘዋል። ድርጊቱን በማውገዝ ህዝባዊ ተቃውሞ ከተደረገባቸው አከባቢዎች አንዱ በደቡብ ክልል የስልጤ ዞን የወራቤ ከተማ እና ሳንኩራ ወረዳ ይገኙበታል። በዞኑ ከተደረገው የተቃውሞ ሰልፍ ጋር ተያይዞ በወራቤና በሳንኩራ ከተሞች በአብያተ ክርስቲያናት እና በሰው ህይወት ላይ ጉዳት ደርሷል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በዞኑ የሰው ህይወት መጥፋትና የክርስትና እምነት ተከታዮች የእምነት ተቋማት ላይ የተፈፀመዉን ጥቃት እጅግ አጥብቆ ያወግዛል። **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በየትኛውም አካባቢ የሚገኙ የዬትኛውም እምነት ተቋማት ከማንኛውም ጥቃት ሊጠበቁ ይገባል የሚል ጽኑ እምነት ያለው ሲሆን፣ በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ በአምልኮ ቦታዎች ላይ የሚደርስን ጥቃት በእጅጉ ይቃወማል። ጥፋት በጥፋት እና ወንጀልን በወንጀል መመለስ ከህግም ሆነ ከስነ ምግባር አንፃር የተወገዘ እና በሀገራችን እየተፈጠረ ያለዉን የጥቃት አዙሪት ይበልጥ የሚያባባስ ተግባር ነው።፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሚያዚያ 19/2014 ባወጣው መግለጫ በየትኛውም ጊዜ እና ቦታ የሀይማኖት ተቋማትን እና የአንድ እምነት ተከታዮችን ህይወትና ንብረት ኢላማ ያደረጉ ጥቃቶች ፍፁም ተቀባይነት የሌላቸው መሆናቸውን እና ሃይማኖት ተኮር ጥቃቶች ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ በቀላሉ የሚሰራጩ የሀገርን እና የህዝብን ሰላም የሚያናጉ አደገኛ ተግባራት መሆናችውን ማሳሰቡ ይታወሳል።

ከሰሞኑ መነሻውን ጎንደር በማድረግ በተለያዩ አከባቢዎች ሃይማኖትን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች መበራከት በሀገራችን ሰላምና ጸጥታ ላይ ከፍተኛ ስጋት የደቀኑ ሲሆን በዜጎች ደህንነት ላይም ከፍተኛ አደጋ አድርሷል። **ነኢፓ** እነዚህ ጥቃቶች በአጭሩ እና በአፋጣኝ መቆም አለባቸው ብሎ በጽኑ ያምናል። በእምነት ተቋማት፣ በሰዉ ህይወት እና ንብረት ላይ በተለያየ ቦታ እና ወቅት እየተፈሙ ያሉ ጥቃቶችን በመከላከል ረገድ አንዳንድ የፀጥታ እና የደህንነት ተቋማት ያሳዩት ዳተኝነት ጥቃቶች እየተስፋፉ እና እየጨመሩ እንዲመጡ አስተዋፅዖ አድርጓል።

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በዱቡብ ክልል ስልጤ ዞን በቤተክርስቲያናት እና በሰዎች ህይወት ላይ የደረሰውን ጥቃት እያወገዝ በአጠቃላይ ሰሞኑን በጎንደር፣ በደባርቅና በስልጤ ዞን የደረሱ ጉዳቶች በሀገራችን ሰላምና በህዝባችን አንድነት ላይ የሚፈጥሩት አደጋና ስጋት ከግምት ውስጥ በማስገባት፣

1. መላው የሀገራችን ህዝቦች በየትኛውም ቦታና ጊዜ በመስጂዶችና በአብያተ ክርስትያናት እንዲሁም በእምነቱ ተከታዮች ህይወት እና ንብረት ላይ የሚደርስን ጥቃት በማውገዝ በድርጊቱ የሚሳተፉ አካላትን እንዲከላከል እንዲሁም ወንጀል ፈፃሚዎችን አሳልፎ በመስጠት እንዲረባረብ፤

2. የፈደራል እና የክልል የጸጥታና የፍትህ ተቋማት የአምልኮ ተቋማትንና ምዕመናንን ሲላማ በማድረግ ጥቃት በሚያደርሱ ወንጀለኞች ላይ አፋጣኝና የማያዳግም እርምጃ በመውሰድ የዜጎችን ህይወት፣ ሀብትና ንብረት የመጠበቅ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ፣

3. የሚዲያ ተቋማት፤ የማህበረሰብ አንቂዎች፤ ታዋቂ ግለሰቦች በየትኛውም ጊዜና ቦታ ኃይማኖትን መነሻ በማድረግ የሚነሱ ግጭቶችን አስመልክቶ በሚሰሯቸው ዘገባዎች እና በሚያሰራጯቸው መረጃዎች ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ፣ ሚዛናዊነት የተላበሱ እና ግጭትን እና ጥፋትን ከማባባስ እንዲቆጠቡ፣

4. በየአካባቢው ኃይማኖትን መሰረት አድረገው የሚነሱ ግጭቶና በዜጎች ህይወት፣ ሀብትና ንብረት የሚደርሱ ጥቃቶች የዜጎች የሰብዓዊ መብት ጥቃት አካል ናቸው። በመሆኑም እስካሁን በዜጎች ሰብዓዊ መብቶች ላይ የደረሱ ጉዳቶችን ለይቶ ተገቢ የህግ እርምጃ መወሰድ ይቻል ዘንድ የሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ አካላት የሚጠበቅባችሁን እንድታደርጉ **ነፃነትና እኩልነት ፓርቲ** በአጽንኦት ይጠይቃል፣

5. የሰው ልጆች ህይወት፣ ክብር፣ ሀብትና ንብረት በየትኛውም ሃይማኖት የተከብሩ እንደሆነ ሁሉም እምነቶች ያስተምራሉ።በመሆኑም የክርስትናም ሆነ የእስልምና ሃይማኖት አባቶች፣ መሪዎች፣ መምህራን፣ ዳኢዎች/ሰባኪያን ሃይማኖትን መሰረት በማድረግ በሌሎች እምነት ተከታዮች ላይ የሚደረግ ጥቃት ምንም ዓይነት ሃይማኖታዊ መሰረት የሌለው መሆኑን የእምነት ተከታዮቻቸውን በማስተማር ምዕመናን ከዚህ ዓይነት ውግዝ ተግባር እንዲቆጠቡ ከወትሮው በተሻለ እና በተለየ እንዲያስተምሩ፣

6. የመንግስት የፀጥታና የፍትህ አካላት ግጭቱን ለመከላከል የሚያሳዩት ቁርጠኝነት ወይም ዳተኝነት ችግሩን ለመፍታት ከፍተኛ እና ቀጥተኛ ሚና አለው። በመሆኑም የጸጥታና የፍትህ ተቋማት የሀገርን ሰላምና የዜጎችን ደህንነት መጠበቅ ሙያዊ ኃላፊነትና ግዴታ ጭምር በመሆኑ ኃላፊነታቸውን በፍጹም ገለልተኝነት እና ተጠያቂነት እንዲወጡ ነእፓ ያሳስባል፣

7. ሀገራችን እምነት ተኮር ግጭቶችን ጨምሮ በተለያዩ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ቀውሶች ውስጥ በማለፍ ላይ ባለችበት በአሁኑ ወቅት፣ መላው የነእፓ አባላት እና በየደረጃው ያላችሁ አመራሮች በየአካባቢው ሰላም እና መረጋጋት፣ ወንድማማችነት እና አብሮነት እንዲሰፍን በተለመደው የሚዛናዊነት መርህ መሰረት ለሀገር ሰላምና ለዜጎች ደህንነት መረጋገጥ የበኩላችሁን እንድትወጡ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ጥሪውን ያቀርባል።

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ሚያዚያ 22 2014**
**አዲስ አበባ**

# ነኢፓ በዜጎች ላይ የሚደርሱ ኃይማኖት-ተኮር ጥቃቶችን በእጅጉ ያወግዛል-የጎንደር መስጊድ ቃጠሎ!!

## በጎንደር ከተማ ሰላማዊ ነዋሪዎች ላይ ጥቃት ባደረሱ ወንጀለኞች ላይ መንግስት አፋጣኝ እርምጃ እንዲወስድ ነኢፓ ጥሪ ያቀርባል!!

በታሪካዊቷ የጎንደር ከተማ፣ ሚያዝያ 18፣ 2014 በወርሀ ረመዳን በህገ ወጥ መንገድ የተደራጁ ግለሰቦች ለቀብር ስነስርአት በወጡ ዜጎች ላይ በከፈቱት ድንገተኛ እና ከባድ ጥቃት በርካታ ንጽሀን ዜጎች ሞተዋል፣ በርካቶች ቆስለዋል እንዲሁም ከፍተኛ ሀብት ወድሟል። ጥቃት አድራሾቹ የሽብር ተግባራቸውን በማስፋት በከተማው ውስጥ ነዋሪዎችን በኃይማኖት እየለዩ በህይወታቸው እና ሀብት ንብረታቸው ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል። ጥቃቱን እጅግ አደገኛ እና አሳሳቢ የሚያደርገው ነዋሪዎችን በኃይማኖት በመለየት ሙስሊሞችን ኢላማ ያደረገ መሆኑ ነው።

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በጎንደር ከተማ በንጹሀን ዜጎች ላይ የደረሰውን አሳፋሪ የሽብር ጥቃት በጽኑ ያወግዛል፣ በዚህ የሽብር ጥቃት ለተገደሉ ወዳጅ ቤተሰቦች እንዲሁም ለመላው የጎንደር ከተማ ህዝብ መጽናናትን ይመኛል።

ይህ አሳዛኝ ጥቃት የተፈጠረው ኢትዮጵያ በሰሜን ክፍል ከአንድ አመት በላይ ከቆየ አውዳሚ የእርስ በእርስ ጦርነት ለመውጣት እና ለማገገም በምትታትርበት፣ ህዝባችን በጦርነቱ የደረሰበት ቁስል ባልሻረበት እንዲሁም በሌሎች የሀገራችን አካባቢዎች ግጭቶች በተበራከቱበት እና ሀገራችን በከፍተኛ የሰላም እጦት እየተናጠች ባለችበት ወቅት ነው። ሀገር በተለያዩ ግጭቶች እየታመሰች ባለች በዚህ ወቅት ሀይማኖትን መሰረት ያደረገ ሌላ ግጭት መጫር ኃላፊነት የጎደለው አሳፋሪ ተግባር ነው። በጎንደር ከተማ በትላንትናው እለት በንጹሀን የከተማው ነዋሪዎች ላይ የደረሰው ጥቃት የሀገራችንን ሰላም እና መረጋጋት የማይሹ የውስጥ እና የውጭ ኃይላት አጀንዳን ከማስፈጸም ተለይቶ የማይታይ ወንጀል ነው። ድርጊቱ ከከተማው አልፎ የሀገራችንን ሰላም እና ደህንነት ሊያውክ የሚችል አደገኛ ተግባር በመሆኑ መላው የሀገራችን ህዝቦች ሊያወግዙት ይገባል።

የአማራ ክልል የተለያዩ ኃይማኖት፣ ቋንቋ እና ባህል ያላቸው ህዝቦች በወንድማማችነት፣ በሰላም እና በፍቅር የሚኖሩበት ክልል ሆኖ ለዘመናት ዘልቋል። በተመሳሳይ ታሪካዊቷ የጎንደር ከተማ ሙስሊም ክርስቲያኑ በሰላም እና በወንድማማችነት የሚኖርበት ከተማ ሆና አያሌ ዘመናት ተቆጥረዋል። ጎንደር የሀገራችን መለያ፣ የአንድነታችን መገለጫ፣ ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር ዘር፣ ቀለም ሀይማኖት ሳይለያቸው ጎብኚዎች የሚጎርፉባት የሰላም እና የአብሮነት ከተማ ሆና ብዙ ዘመናት ያሳለፈች ከተማ ናት። በዚህች የሰላም ከተማ የጦርነት እሳት መለኮስ የከተማይቱን ታሪክ እና የነዋሪዎቿን ማንነት የማይመጥን የወንጀል ድርጊት ነው።

ይሁን እንጂ መላው የሀገራችን ህዝቦች ከምናውቀው የክልሉ እና የጎንደር ከተማ የሰላም እና የአብሮነት ታሪክ በተጻራሪ፣ የዜጎች አንድነት እና ወንድማማችነት የማይመቻቸው ጽንፈኛ እና አክራሪ ቡድኖች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በክልሉ በተለይም በጎንደር ከተማ እና በአካባቢው ጥላቻን በመስበክ በሰላም እና በፍቅር በሚኖረው ህዝብ መካከል በተደጋጋሚ ግጭት እየቀሰቀሱ ይገኛሉ። በትላንትናው እለት በጎንደር ከተማ በንጹሀን ላይ የተፈጸመው የሽብር ጥቃት በአካባቢው እየገነገነ ለመጣው የጥላቻ እና የግጭት ትርክት አንዱ ማሳያ ነው።

በትላንትናው እለት የተፈጸመው ይህ ጥቃት ከዚህ ቀደም በክልሉ ሌሎች ከተሞች የተፈጸሙ ኃይማኖት-ተኮር የሽብር ጥቃቶችን የሚያስታውስ ሲሆን፣ አፋጣኝ መፍትሄ ከልተበጀለት የከፋ አደጋ ማስከተሉ አይቀሬ ነው። ጥቃቱ ከከተማው፣ ከዞኑ እና ከክልሉ አልፎ የሀገራችን የሰላም ስጋት እንዳይሆን **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ከፍተኛ ስጋት አድሮበታል።

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በትላንትናው እለት በጎንደር ከተማ ነዋሪዎች ላይ የደረሰውን ኃይማኖት-ተኮር ጥቃት በጽኑ እያወገዘ፣

- የጎንደር ከተማ፣ የዞኑ እና የክልሉ የጸጥታ እና የፍትህ አካላት በትላንትናው እለት የሽብር ጥቃት የተሳተፉ ወንጀለኞችን በአስቸኳይ ለህግ እንዲያቀርብ እያሳሰብን፣ የክልሉ መንግስት በህገ ወጥ መንገድ የተደራጁ እና ኃይማኖታዊ ግጭት በሚቀሰቅሱ ኃይሎች ላይ ተመጣጣኝ እና የማያዳግም እርምጃ እንዲወስድ ጥሪውን እያቀረበ፣

- የክልሉ እና የጎንደር ከተማ የጸጥታ እና የፍትህ ተቋማት በከተማው የሚኖሩ ዜጎችን በእኩልነት እና ያለ አንዳች አድልዎ የመጠበቅ ህገ መንግስታዊ ግዴታ ያለባቸው መሆኑን በመረዳት፣ የከተማውን እና የክልሉን ነዋሪዎች ሰላም እና ደህንነት የመጠበቅ ግዴታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ያሳስባል፣

- የትላቱ የጎንደሩ ከተማ ጥቃት ሊከሰት የቻለበት አንዱ ምክንያት ቀደም ሲል በክልሉ ሌሎች አካባቢዎች ኃይማኖት-ተኮር ጥቃት ባደረሱ ወንጀለኞች ላይ ተመጣጣኝ እርምጃ አለመወሰዱ ነው። በመሆኑ በቀላሉ ሊዛመቱ እና የሀገራችንን ሰላም እና ደህንነት ሊያናጉ የሚችሉ ኃይማኖት-ተኮር ግጭቶችን በሚቀሰቅሱ ህገ ወጥ ኃይሎች ላይ የክልል እና የፌዴራል መንግስታት ፈጣን እና የማያዳግም እርምጃ እንዲወስዱ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ያሳስባል፣

- በሰሜኑ የሀገራችን ክልል ከተፈጠረው ጦርነት ማግስት እጅግ በርካታ ቀላል እና ከባድ መሳሪያዎች በህገወጥ መንገድ በተደራጁ ቡድኖች እጅ ወድቀዋል። እነዚህ መሳሪያዎች በሚመለከታቸው የክልል እና የፌዴራል መንግስት አካላት ስር ካልዋሉ ለዜጎች ሰላም እና ደህንነት ከፍተኛ ስጋት ይደቅናሉ። በመሆኑ የፌዴራል እና የክልል መንግስታት በህገ ወጥ ቡድኖች እጅ የሚገኙ ቀላል እና ከባድ መሳሪያዎችን በመሰብሰብ ህገ መንግስታዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ እና የዜጎችን ህይወት እንዲታደጉ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ያሳስባል፣

- **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በትላንቱ የጎንደር ከተማ ጥቃት ሀብት ንብረታቸው ለወደመባቸው የሽብር ጥቃት ሰለባዎች የከተማው አስተዳድር፣ የክልሉ መንግስት፣ ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች እንዲሁም መላው የሀገራችን ህዝቦች ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪውን ያቀርባል፣

- በየትኛውም ጊዜ እና ቦታ ኃይማኖታዊ ግጭቶችን የሚጭሩ ኃይሎች ዓላማ ኃይማኖት ሳይለየው ተቻችሎ እና ተከባብሮ የሚኖረውን ህዝብ በማጋጨት ሀገራችንን ወደለየለት የኃይማኖት ጦርነት ማስገባት ነው። በመሆኑም መላው የሀገራችን ህዝቦች የሀገራችንን ሰላም የማይሹ ጸረ ሰላም ኃይሎች የሚቀሰቅሷቸውን ኃይማኖት-ተኮር ግጭቶችን ለማክሸፍ በአንድነት እንዲቆሙ እና ወንጀሎችን በአንድነት እንዲያወግዙ **ነኢፓ** በአጽንኦት ይጠይቃል፣

- በመጨረሻም በወንድማማችነት እና በአንድነት የምትታወቀው የጎንደር ከተማ ህዝብ አንዴ በኃይማኖት ሌላ ጊዜ በብሄር ሊከፋፍሉህ የሚሹ የጥፋት ኃይሎችን እንዲሁም ታሪካዊቷን ከተማህን የግጭት አውድማ ሊያደርጉ የሚሹ ጽንፈኛ ቡድኖችን በጋራ በማውገዝ የጥፋት ኃይሎችን ሴራ እንድታከሽፍ **ነኢፓ** ጥሪውን ያቀርባል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ሚያዝያ 19 2014**
**አዲስ አበባ**

# በአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች የእምነት ነጻነት ሊከበር ይገባል

## በአዲስ አበባ አንዳንድ ትምህርት ቤቶች በተማሪዎች ላይ የተፈጸመን የዕምነት ነጻነት ጥሰት አስመልክቶ ከነኢፓ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ የተሰጠ የአቋም መግለጫ፡፡

ካለፉት ጥቂት ወራት ጀምሮ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ አንዳንድ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተማሪዎችን የሀይማኖት እና የአምልኮ ነጻነት በሚጋፋ መልኩ በተማሪዎች ላይ ጫና እና እንግልት ሲፈጸም ተስተውሏል፡፡ በተማሪዎች እና ወላጆቻቸው ላይ የተላለፈው ውሳኔ ከዜጎች የግለሰብ እና የቡድን መብቶች መከበር ህገ መንግስታዊ ድንጋጌዎች አንጻር ሲታይ፣ ከሀገራችን የትምህርት ሴክተር ፖሊሲዎች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች አኳያ ሲቃኝ፣ ከሀገራችን የመቻቻል እና የአብሮነት ታሪክ እንዲሁም ከሀገር ሰላም እና አንድነት አኳያ ሲገመገም፣ ህገ ወጥ እና ኢ-ህገ መንግስታዊ ድርጊት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የሀይማኖት ነፃነት መርጎ በኢፌዴሪ ህገ-መንግስት እዉቅና የተሰጠው ሲሆን የህገ-መንግስቱ አንቀጽ 27(1) ማንኛዉም ሰዉ የመረጠዉን ሀይማኖት ወይም እምነት የመያዝ ወይም የመቀበል፣ ሀይማኖቱንና እምነቱን ለብቻ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል፣ የመተግበር፣ የማስተማር ወይም የመግለጽ መብትን እንደሚያካትት ይደነግጋል፡፡ ከሀገራችን ህጎች በተጨማሪ የሃይማኖት እና የእምነት ነፃነቶች በተለያዩ ዓለም አቀፍ ህጎች እና ስምምነቶች ሰፊ እውቅና የተሰጣቸው ሲሆን ከሰብአዊ መብቶች ጋር የተቆራኙ ናቸው፡፡

በአዲስ አበባ በተማሪዎች ላይ የአምልኮ ክልከላ ያደረጉ ትምህርት ቤቶች እንደ ምክንያት የሚያቀርቡት የሴኩላሪዝም መርህን ነው፡፡ ይሁን እንጂ ትምህርት ቤቶቹም ሆኑ አንዳንድ የትምህርት ሴክተር ኃላፊዎች ሴኩላሪዝምን የተረዱበት እና የተገበሩበት አውድ ከሴኩላሪዝም ጽንሰ ሀሳብ ጋር የሚጋጭ ነው፡፡ የሴኩላሪዝም ጽንሰ ሀሳብ ዋነኛ አስተምህሮ የመንግስት ተቋማትን ከሀይማኖት ተቋማት መለየት ነው፡፡ ሴኩላሪዝም መንግስት ሀይማኖትን መሰረት ባደረገ መልኩ በዜጎች መካከል ልዩነት እና አድልዎ እንዳያደርግ የሚከለክል አስተሳሰብ ነው፡፡ ሴኩላሪዝም መንግስት እና ኃይማኖት አንዱ በሌላው ውስጥ ጣልቃ ሳይገባ የሚሰሩበት አሰራር ነው፡፡

በሴኩላሪዝም እና በትምህርት ጥራት ስም በተማሪዎች ላይ የተላለፈው ውሳኔ የትምህርት ሴክተሩን ተግዳሮቶች እና የሀገራችንን ወቅታዊ ተጨባጭ ሁኔታ በእውን ያገናዘበ አይደለም፡፡ የሀገራችን የትምህርት ዘርፍ በደቂቃዎች ውስጥ ከሚከናወን የአምልኮ ስርአት ይልቅ ከፍተኛ ትኩረት እና ርብርብ የሚጠይቁ ድርብርብ ችግሮች አሉበት፡፡ የተደራሽነት፣ የጥራት፣ እና የፍትሀዊነት ችግሮች የትምህርት ዘርፋችን መሰረታዊ ችግሮች ሲሆኑ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት አያሌ ሙከራዎች ቢደረጉም ችግሮቹ ዛሬም እንደቀጠሉ ናቸው፡፡

የተለያዩ አስተዳደራዊ እና ህጋዊ መንገዶች በመጠቀም የተቀናጀ እና መዋቅራዊ ኢ-ፍትሀዊነት ጎልቶ ከታየባቸው ማህበራዊ አገልግሎቶች አንዱ እና ዋነኛው የሀገራችን የትምህርት ዘርፍ ሲሆን በታሪክ የተፈጠረው አድሏዊ አሰራር ዛሬም ድረስ ሁለንተናዊ ተጽእኖው እንደቀጠለ ነው፡፡ በሀገራችን የትምህርት ዘርፍ የተፈጠረውን ታሪካዊ መዛነፍ ለማስተካከል ሰፊ እና

ተከታታይ የእርምት እርምጃዎች መውሰድ የሚያስፈልግ ሲሆን፣ ታሪካዊ መዛነፉን ይበልጥ ሊያሰፉ ከሚችሉ አፍራሽ እርምጃዎች መቆጠብ ያስፈልጋል፡፡

ሀይማኖት በሀገራችን ህዝቦች ዘንድ ያለውን ቦታ ስንመለከት ሀይማኖት የአብዛኛው የሀገራችን ህዝቦች አንዱ እና ዋነኛው የማንነት መገለጫ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በአለም "የሀይማኖተኛነት መለኪያ Religiosity Index" ከአለም ቀዳሚ ስፍራ መያዟ ለዚህ አንድ ትልቅ ማሳያ ነዉ፡፡ ኢትዮጵያ ከሀይማኖት ጋር ጠንካራ ቁርኝት እንዲኖራት የሀገራችን የትምህርዘርፍ ከፍተኛውን ድርሻ ተጫውቷል፡፡ የሀገራችን የትምህርት ታሪክ ይህንን እውነታ በግልጽ ያሳያል፡፡

በተማሪዎች ላይ የእምነት ነጻነትን የሚሸረሽር ውሳኔ ያስተላለፉ ትምህርት ቤቶች ድርጊታቸው የዓለም አቀፍ ተሞክሮንም የጣሰ ውሳኔ ነው፡፡ ከእምነት እና አምልኮ ነጻነት ጋር በተያያዘ የአለም አቀፍ ተሞክሮ የሚያሳየዉ ት/ቤቶች ለተማሪዎቻቸዉ በቡድንም ሆነ በተናጠል የእምነታቸዉን አስገዳጅ ትእዛዛት እንዲተገብሩ ከመፍቀድ ባለፈ ምቹ ሁኔታ እና ቦታ ያመቻቻሉ፡፡ የሴኩላሪዝም አስተሳሰብ ደርጅቷል በሚባልባቸው የአውሮፓና የአሜሪካ ሀገራት አንድ ሰው የሌሎችን መብት እና ሞራል ጠብቆ የግል ሀይማኖታዊ አምልኮ መፈጸም የተለመደ ተግባር ነው፡፡

የትምህርት ቤቶቹ ውሳኔ የሀገራችንን ወቅታዊ የፖለቲካ እና የሰላም እንዲሁም ሌሎች ማህበረ ኢኮኖሚ ጉዳዮችም በውል ያላገናዘበ ነው፡፡ ሀገራችን ሰላሟን እና አንድነቷን በሚፈታተኑ በርካታ ውስጣዊ እና ውጫዊ ችግሮች በተወጠረችበት በአሁኑ ወቅት መሰረታዊ የሰብአዊ መብት አካል የሆኑ የእምነት እና የአምልኮ ነጻነቶችን በመገደብ በህዝብ እና በመንግስት መካከል ግጭት ሊፈጥር የሚችል ተግባር መፈጸም አርቆ ማስተዋል የጎደለው ተግባር ነው፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** አዲስ አበባ ቅርንጫፍ በከተማችን አንዳንድ ትምህርት ቤቶች በተማሪዎች ላይ የወሰዱት እርምጃ በህገ መንግስት የተረጋገጡ የዜጎችን የሀይማኖት ነጻነት የሚጋፋ፣ ከሴኩላሪዝም አስተሳሰብ ጋር የሚጋጭ፣ ከአለም አቀፍ ተሞክሮ በተቃራኒ የቆመ፣ የሀገራችን ህዝቦች ማህበራዊ መስተጋብር እና በሀይማኖት ተቻችሎ የመኖር አኩሪ ታሪክ ከግምት ውስጥ ያላስገባ እንዲሁም የሀገራችንን አሁናዊ የፖለቲካ ትኩሳት እና የሰላም እጦት በእውኑ ያላገናዘ ውሳኔ ሆኖ አግኝቶታል፡ :በመሆኑም ከላይ በዝርዝር የተመለከቱትን የህግ፣የታሪክ፣የፖለቲካ እንዲሁም ዓለማቀፍ ተሞክሮ እና "የሴኩላሪዝምን" ትክክለኛ ትርጉም እና እንድምታ ታሳቢ በማድረግ፣

1. በቅርቡ በአዲስ አበባ አንዳንድ ትምህርት ቤቶች በተማሪዎች ላይ የተወሰደው እርምጃ በአስቸኳይ እንዲቆም፣ የተማሪዎችን ሰብአዊ መብት በሚጋፋ መልኩ "በሴኩላሪዝም" ስም ተማሪዎች እና ወላጆች ሀይማኖትታዊ እና የአምልኮ ነጻነታቸውን በሚገፍ መልኩ ቅጽ እንዲሞሉ የተሰራው አስገዳጅ ተግባር እንዲቋረጥ፣
2. ከተማሪዎች የአምልኮ ነጻነት፣ ከተማሪዎች ባህላዊ እና ሀይማኖታዊ አለባበስ ጋር ተያይዞ ከሀገራችን የትምህርት ዘርፍ ደንቦች እና መመሪያዎች ውጪ አንዳንድ የትምህር ቤት አመራሮች በግል ፍላጎት እና ጥላቻ የሚወስዱትን ህገ ወጥ ተግባር ስርአት ለማስያዝ የፌዴራል እና የክልል የትምህርት አካላት እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው የአስተዳደር እና የጸጥታ አካላት አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስዱ፣

3. የሴኩላሪዝም መርህ በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 90(2) እንደተደነገገዉ የትምህርት ይዘትና ፖሊሲ ከሀይማኖት ተጽኖ ነፃ እንዲሆን እንጅ ተማሪዎች ከእምነት ተግባራቸዉ እንዲቆጠቡ ማስገደድ አለመሆኑን በመገንዘብ፣ በዜጎች የአምልኮ ነጻነት እና ሀይማኖታዊ አለባበስ ላይ የሚደረጉ ጣልቃ ገብነቶች ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ መፍትሄ እንዲያገኙ መንግስት ሀላፊነቱን እንዲወጣ፣

4. የኢፌዴሪ የትምህርት ሚንስቴርም ይሁን የክልል የትምህርት ቢሮዎች "ትምህርትን፣ ከሀይማኖት፣ ከፖለቲካ እና ከባህል ተጽእኖ ነጻ ማድረግ በሚል" ምክንያት በተለያየ ጊዜ የሚያወጡዋቸው መመሪያዎች በህገ መንግስቱ የተረጋገጡ የዜጎችን የሀይማኖት እና የአምልኮ ነጻነቶች እንዳይሸራርፉ መንግስት የማያዳግም ህግ ሊያወጣ ይገባል፣ ይህንን ህግ በሚተላላፉ አካላት ላይም ተገቢውን አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ፣

5. የተለያዩ ሀይማኖቶች በጊዜ የተገደቡ የአምልኮ ስርአቶች እንዳሏቸው ይታወቃል:: ይህንን መብት መገደብ የእምነት ነጻነትን ከመገደብ ተለይቶ አይታይም:: በተለይም አኩሪ የሀይማኖት መቻቻል ባህል ባለቤት በሆነችው ሀገራችን የዚህ አይነት እርምጃ ከባድ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ እንድምታ ያለው ተግባር በመሆኑ በጊዜ እንዲገታ፣

6. የዜጎችን ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ለማክበር እና ለማስከበር፣ የሀይማኖትን ነጻነት እና እኩልነት ለማረጋገጥ ቃል ገብቶ በስልጣን ላይ የሚገኘው ፓርቲ እና መንግስት ኃላፊነት እና ተጠያቂነት በጎደለው መልኩ "በሴኩላሪዝም" ስም የዜጎችን የእምነት እና የአምልኮ ነጻነት በሚገድቡ የትምህርት ቤት አመራሮች ላይ ተገቢ አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ እና ይህ አሰራር በሌሎች እንዳይደገም ግልጽ ደንብ እና መመመሪያ እንዲያዘጋጅ፣

7. በመጨረሻም በከተማችን የተፈጠረው ችግር ዘላቂ እና ህጋዊ መፍትሄ እስኪያገኝ፣ ተማሪዎች እና ወላጆች የመብት ጥያቄያቸውን በትእግስት እና በሰላማዊ መንገድ በማቅረብ ለችግሩ ሰላማዊ መፍትሄ ለመስጠት በሚደረገው ጥረት የበኩላቸውን ትብብር እንዲያደርጉ፤ ነኢፓ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጥሪውን እያቀረበ፣ ለችግሩ ዘላቂ መፍትሄ እስኪፈጠር ድረስ ጉዳዩን በቅርበት የምንከታተል እና የድርሻችንን የምንወጣ መሆኑን እንገልጻለን::

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ**
**ሚያዝያ 3፣ 2014**
**አዲስ አበባ**

# ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ነኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አቋም መግለጫ

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ነኛ መደበኛ ጉባኤውን መጋቢት ነ፰፣ 2014 በአዲስ አበባ አካሂዷል፡፡ በጉባኤው ላይ ከተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የተወከሉ ከ900 በላይ የፓርቲው አባላት፣ አመራሮች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች አመራሮች፣ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች፣ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ተወካዮች ተገኝተዋል፡፡ በጉባኤው ላይ የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ በአዋጅ ቁጥር ነ162/2011 መሰረት ተስተካክሎ የጸደቀ ሲሆን የተጓደሉ የፓርቲው ብሄራዊ ምክር ቤት አባላትም ተመርጠዋል፡፡

የጉባኤው ተሳታፊዎች በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት ያደረጉ ሲሆን በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ያለው ጦርነት እና ጦርነቱን በሰላም ለመፍታት ያሉ እድሎች፣ በጦርነቱ ሰብአዊ እና ቁሳዊ ጉዳት የደረሰባቸዉ ዜጎች አስቸኳይ ድጋፍ እና መልሶ ማቋቋም፣ ሁሉን አቀፍ ሀገራዊ ምክክር፣ የኢኮኖሚ ቀውስ፣ የዋጋ ግሽበት እና የኑሮ ዉድነት፣ በሀገራችን ያለው የሰብአዊ መብት አያያዝ፣ የህግ የበላይነት፣ የዜጎች መፈናቀል፣ ሞት እና ግድያ ፤ ድርቅ እና ረሀብ፣ የመልካም አስተዳደር እጦት፣ ሙስናና ብልሹ አሰራር፣ የአካባቢ ምርጫ፣ የዉጭ ግንኙነት እና ዲፕሎማሲ፤ በዉጪ የሚኖሩ ዜጎች ሁኔታ፣ በውይይቱ ከተዳሰሱ ጉዳዮች መካከል ናቸው፡፡

**የተወዳችሁ የሀገራችን ህዝቦች፣**
ባለፉት አራት አመታት ሀገራችን በፖለቲካ ሽግግር ውስጥ ትገኛለች፡፡ በሀገራችን በለውጥ ማግስት ሁሌም እንደሚደረገው በ2010 ሪፎርም ማግስትም በለውጡ መንግስት ተስፋ ሰጪ ውሳኔዎች ተወስደዋል፡፡ በዚህም የፖለቲካ እስረኞች፣ ጋዜጠኞች፣ ጦማሪያን ከእስር ተፈተዋል፣ የዴሞክራሲ ተቋማትን ለማጠናከር ይረዳሉ የተባሉ አንዳንድ የህግ ማሻሻያዎች ተደርገዋል፡፡ ሌሎች ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ማሻሻዎችንም ለማስተዋወቅ ጥረት ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ በለውጡ ማግስት ጋብ ብሎ የነበረው ፖለቲካዊ ቀውስ ብዙም ሳይቆይ ተባብሶ ቀጥሏል፡፡ የዜጎች ስደት እና ሞት፣ ግጭት፣ ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ ተባብሶ ቀጠለ፡፡

በፌዴራል መንግስት እና በህወሀት መካከል የተጀመረው ጦርነት ባለፈው አንድ አመት በሀገራችን ከተከሰቱ ፖለቲካዊ ቀውሶች አንዱ እና ዋነኛው ነው፡፡ ጦርነቱ ሀገራችንን በሰው ህይወት እና በንብረት እጅግ ውድ ዋጋ አስከፍሏታል፡፡ በጦርነቱ ምክንያት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ተሰደዱ፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ህይወት አለፈ፡፡ በጦርነቱ ምክንያት አያሌ ህጻናት እና አረጋውያን ለከፋ ችግር ተጋለጡ፣ ሴት እህቶቻችን ለጾታዊ ጥቃት ተጋለጡ፣ ሰብአዊ ክብራቸው ተደፈረ፡፡

በአሁኑ ሰአት ጦርነቱ ጋብ ያለ ቢመስልም ሙሉ ለሙሉ አልቆመም፡፡ በአፋር ክልል የትግራይ አዋሳኝ ወረዳዎች የሚገኘው አርብቶ አደር ማህበረሰብ በከፍተኛ ችግር ውስጥ ይገኛል፡፡ በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ አርብቶ አደሮች ከቀያቸው ተፈናቅለው በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ጦርነቱ በተለይ በአማራ፣ በአፋር እና በትግራይ ክልሎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ ሲሆን መላው የሀገራችን ህዝቦች እና አካባቢዎች የጦርነቱን ገፈት ቀምሰዋል፡፡ የጦርነት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጦስ ረዥም ጊዜ እንደሚቆይ የሀገራት የጦርነት ታሪክ ምስክር ነው፡፡

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ከተከሰተው ጦርነት በተጨማሪ ሀገራችን በበርካታ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ችግሮች ተወጥራለች፡፡ ከጥቂት ወራት ወዲህ በምስራቅ እና ደቡብ ኢትዮጵያ በተከሰተው ድርቅ በርካታ የአርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር ማህበረሰብ ለከፋ ርሀብ፣ ሞት እና ስደት ተጋልጧል፡፡ መንግስትን ጨምሮ ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ድርጅቶች ባወጧቸው ሪፖርቶች መሰረት በሶማሊ ክልል እንዲሁም በምስራቅ እና ደቡብ ኦሮሚያ አካባቢዎች በድርቁ ሳቢያ ከፍተኛ ሰብል ወድሟል፣ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ከብቶች ሞተዋል፣ ከሞት የተረፉት እንስሳት በመኖ፣ ውሀ እና መድሃኒት እጥረት ህይወታቸው ለአደጋ ተጋልጧል፡፡ በድርቁ በተጠቁ አካባቢዎች የሚኖረው ማህበረሰብ አሳሳቢ የምግብ ዋስትና እጥረት ያጋጠመው ሲሆን፣ ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆኑ ህጻነት እና እናቶች ለከፍተኛ የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ተጋልጠዋል፡፡

ጉባኤው ከላይ በተዘረዘሩ ወቅታዊ የሀገራችን ችግሮች ዙሪያ  በስፋት ከተወያያ በኋላ የሚከተሉትን ባለ 10 ነጥብ የአቋም መግለጫ አዉጥቷል፡-

1. በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተለኮሰው የጦርነት እሳት ሙሉ ለሙሉ ይቆም ዘንድ ሁሉም አካላት ግጭቱን ለማስቆም ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ነጻነትና እኩልነትፓርቲ  ጥሪውን ያቀርባል፡፡ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** መንግስት በቅርቡ ለትግራይ ክልል ተጨማሪ ሰብአዊ ድጋፍ ከወትሮው በተሻለ መጠን እና ስፋት እንዲደርስ ለማድረግ ያሳየውን ተነሳሽነት እያደነቅ ውሳኔው በተቻለ ፍጥነት ተግባራዊ ይሆን ዘንድ የሚመለከታቸው አካላት የድርሻቸውን እንዲወጡ ጥሪውን ያቀርባል፣

2. ምንም እንኳን በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ያለው ግልጽ እና ሰፊ ጦርነት የተለየ ትኩረት ያገኘ ቢሆንም፣ በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ግጭቶች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ በእነዚህ ግጭቶች ምክንያት በሰላማዊ ዜጎች ላይ ግድያ፣ መፈናቀል እና የንብረት ውድመት ዛሬም ድረስ ሊቆም አልቻለም፡፡ በመሆኑም መንግስት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተፈጠረውን ችግር እልባት ለመስጠት ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ጎን ለጎን በሌሎች የሀገራችን ክፍሎች የሚገኙ ዜጎችን ሰላም እና ደህንነት ለመጠበቅ በቂ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፣

3. በሶማሊ እና ኦሮሚያ ክልሎች የተከሰተው ድርቅ በሰው ህይወት፣ በከብቶች እና በአካባቢ ላይ እያደረሰ ያለውን ሰፊ ጉዳት ለመቋቋም፣ የፌዴራል እና የክልል መንግስታት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ባለሀብቶች እንዲሁም የአለም አቀፉ ማህበረሰብ አፋጣኝ ድጋፍ እንዲደርጉ፣  ለሰው እና ለእንስሳት አገልግሎት የሚውል ውሀ፣ ምግብ፣ ለህጻናት እና እናቶች  የሚያገለግል የተመጣጠነ ምግብ፣ የእንስሳት መኖ፣ የጤና አገልግሎት በድርቅ ለተጎዱ አካባቢዎች በፍጥነት የሚቀርብበት ሁኔታ እንዲመቻች **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ጥሪውን ያቀርባል፡፡

4. መንግስት በሀገራችን ሁሉን አሳታፊ ሀገራዊ ምክክር ለማድረግ ኮሚሽን ማቋቋሙ ይታወሳል፡፡ ኮሚሽኑን ለማቋቋም እስከ አሁን ድረስ በተሰሩ ስራዎች የብሄራዊ ውይይቱን ሂደት ሊያውኩ የሚችሉ ክፍተቶች ተስተውለዋል፡፡ ለተሳካ ሀገራዊ ውይይት አንዱ እና ዋነኛው መስፈርት መተማመን ሲሆን በተለይም የሂደቱ ዋና ተዋናይ በሆኑ የፖለቲካ ኃይሎች መካከል የሚኖረው ግንኙነት ለሀገራዊ ምክክሩ መሳካት ወሳኝ ነው፡፡ለተሳካ የሀገራዊ ምክክር የመንግስት ድጋፍ ወሳኝ መሆኑ እሙን ቢሆንም፣ ሂደቱ ከመንግስት ጫና እና የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ነጻ እንዲሆን ማድረግ

አስፈላጊ በመሆኑ በተለይ መንግስት እና የተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለሀገራዊ ምክክሩ መሳካት የድርሻቸውን እንዲወጡ ጥሪ እናቀርባለን፣

5. መንግስት በየጊዜው እየናረ የሚገኘውን የዋጋ ግሽበት ለመቆጣጠር እና የኑሮ ውድነትን ለመቀነስ አፋጣኝ እና ተገቢ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሊያደርግ ይገባል፡፡ የዋጋ ግሽበቱን ከሚያባብሱ ኢኮኖሚያዊ እና አስተዳደራዊ ምክንያቶች መካከል በመረጃ እና እውቀት ላይ ያልተመሰረቱ ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች፣ ወጥነት የጎደለው እና ያልተቀናጀ የመንግስት አሰራር፣ ሙስና፣ ይገኙባቸዋል፡፡ በሀገራችን በፍጥነት እያደገ ለሚሄደው የዋጋ ንረት እና የኑሮ ውድነት ዋነኛ ተጠያቂ መንግስት ሲሆን፣ የተፈጠረውን አጠቃላይ የኢኮኖሚ ቀውስ ለማስተካከር መንግስት አፋጣኝ የማሻሻያ እርምጃዎች እንዲወስድ እናሳስባለን፣

6. በውጭ ሀገር በተለይም በመካከለኛው ምስራቅ አንዳንድ ሀገራት የሚኖሩ ወገኖቻችን ጉዳይ አሁንም እልባት አላገኘም፡፡ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ባለፉት ጥቂት ወራት በውጪ ሀገር የሚገኙ ወገኖቻችንን አስመልክቶ ለኢትዮጲያ መንግስት እና በኢትዮጵያ የሳውዲ ኢምባሲ ስጋቱን መግለጹ ይታወሳል፡፡ ዛሬም ይህንኑ ስጋታችንን እየገለጽን በተለይም በሳኡዲ አረቢያ የሚገኙ ዜጎቻችን ወደ ሀገራቸው በአፋጣኝ መመለስ የሚችሉበት ሁኔታ ይመቻች ዘንድ በድጋሜ እንጠይቃለን፡፡

7. ሀገራችን ከከበቧት ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ችግሮች ባሻገር በላፈው አንድ ዓመት ተስፋ ሰጪ ለውጦችንም አይታለችም፡፡ ከእነዚህ መካከል የህዳሴ ግድብ ሀይል ማመንጨት መጀመር አንዱ ስኬት ነው፡፡ የህዳሴ ግድባችን የነበሩበትን በርካታ ችግሮች አልፎ ሀይል ማመንጨት በመጀመሩ መላው የነኢፓ ቤተሰቦች ከፍተኛ ደስታ ተሰምቶናል፡፡ ፕሮጀክቱ ካለው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባሻገር የአንድነታችን ምልክት በመሆኑ ስራው ሙሉ ለሙሉ እስኪጠናቀቅ ድርስ መላው የሀገራችን ህዝቦች ድጋፋችንን አጠናክረን መቀጠል እንዳለብን ማስታወስ እንወዳለን፤

8. በሀገራችን የመልካም አስተዳደር ዕጦት በተለይም ሙስና እና ብልሹ አሰራር ስር እየሰደደ፣ እየተስፋፋ እና ስርአታዊ እና ተቋማዊ ቅርፅ እየያዘ መጥቷል፡፡ ይህ በዚሁ የሚቀጥል ከሆነ ከሌሎች በርካታ ዘርፈ ብዙ ችግሮቻችን ባሻገር ሀገራችንን ወደ ከፋ ቀዉስ እና ምስቅልቅል የማስገባት አቅም ያለዉ በመሆኑ፣ መንግስት ላይ የሚታየዉ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን የመዋጋት ዳተኝነት ተስተካክሎ፣ ከቃል ያለፈ ተግባራዊ ተቋማዊ ማሻሻያ እንዲደረግ እና ህጋዊ እርምጃ እየተወሰደ የተመዘበረ የህዝብ ገንዘብ በአፋጣኝ እንዲመለስ የሚደረግበት ስርአት እንዲመቻች እንጠይቃለን፣

9. በሀገራችን የሚካሄደዉን የአካባቢ ምርጫ ለማካሄድ፣ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ንቁ ተሳትፎ ያደርጉ ዘንድ በ6ኛዉ አገራዊ የህዝብ ተወካዮች እና የክልል ም/ቤት አባላት ምርጫ የታየዉን የምርጫዉ ነፃ፣ ፍትሀዊ እና ገለልተኛ የመሆን ችግር ሙሉ በሙሉ በመቅረፍ እና በምርጫ ፋይናንስ ረገድ የተፈጠረዉን ከፍተኛ ልዩነት በማጥበብ ምርጫዉ ነፃ፤ፍትሀዊ እና ሰላማዊ ሆኖ የሚካሄድበትን አስቻይ ሁኔታዎች መንግስት እንዲያመቻች እንጠይቃን፣

10. **ነፃነት እና እኩልነት ፓርቲ** ከላይ የተጠቀሱትን የሀገራችንን መሰረታዊ ችግሮች ለመቅረፍ እና የመፍትሄ አቅጣጫዎችን መተግበር ይቻል ዘንድ ከገዢዉ ፓርቲም ሆነ ከተፎካካሪ ፓርቲዎች እንዲሁም ከሀገራችን ህዝብ ጋር በጋራ ለመስራት ቁርጠኛ መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡

**ነፃነትና እኩልነት ፓርቲ**
**መጋቢት 18፣ 2014**
**አዲስ አበባ**

## The performance of the AU should be enhanced to match its ambitions!!
## "Beyond Paper-tiger African Union"

The African Union (AU) is the apex political organization in the continent making up 55 sovereign Member states. Guided by the pan-African philosophy, the then OAU set to ensure ***freedom, equality, justice and dignity*** for the people of Africa. Liberation from old colonial masters and getting rid of apartheid were the major objectives of the OAU, which was successfully accomplished mostly in the 1950s and 60s. In 2002, the OAU was formally transformed to AU, with a vision to see *an Integrated, Prosperous and Peaceful Africa, driven by its own citizens and representing a dynamic force in the global arena. This year marks the 20th anniversary of the AU.*

In the last 6o years both the AU and, its predecessor, OAU set lofty objectives and ambitious targets in the areas of economic development, political and cultural integration, peace and security, democracy and governance etc. The constitutive act of the AU envisioned a prosperous, peaceful, fully integrated continent; a continent where free mobility of capital and labor ensured, goods and services traded freely. The OAU/AU also set more ambitious targets in the cultural, diplomacy, security, and issues related with augmenting African's global role.

However, assessment of the performances of the OAU/AU reveals a huge gap between its ambitions and achievements. Today African is infested by all economic, social, political, security and global challenges. Internal political instability, interstate border conflicts, food insecurity, abject poverty, bad governance and corruption are but some of the major features of the African polity & objective realities. Millions of African children die due to lack of food and suffer from stunted growth, significant number of children do not have access to basic health services and stay out of school.

Human rights violations are pervasive throughout Africa. Seizure of political power by military officials is still part of African political reality. Against the values and principles of the African charter on democracy, elections and governance, electoral fraud, vote buying and political corruption are common. Most of the flagship projects of the AU including the African Continental Free Trade Area (CFTA, signed in 2018) and silencing the gun (2020) seem far from reality. Covid 19 pandemic has exacerbated the already fragile socio-economic conditions of Africa.

The AU lacks institutional, financial and logistics capacity to realized its vision. Most of the specialized agencies and institutions of the AU couldn't deliver much. AU is dependent on its international partners to finance activities, including its administrative operations. The poor financial status emanates, partly from lack of commitment by member states to pay their annual contributions.

As the AU conducts its 35th submit, the AU commission and member states should take firm decisions to put the socio-economic, political and security challenges of the continent in order. The AU should operate its peace and security apparatus to end inter and intrastate conflicts including, but not limited to, successfully ending the civil war in Ethiopia and amicably resolve the Ethio-Sudan border dispute. The AU commission should introduce system to strengthen its organs including the pan-African parliament, the peace and security council and other legal and financial institutions. It should also put administrative mechanism and monitoring tools to warrant the successful and intime completion of projects and programs.

The AU should pressure member states to ratify the African Continental Free Trade Area, which is expected to lift tens of millions of Africans out of poverty. African governments should let their citizens, especially their young generation, enjoy commodities produced in fellow African countries, at a lower price. Similarly, the AU should take robust and punitive actions against those military leaders of member states that unconstitutionally seize political power.

The AU should avoid 'white-elephant' programs and institutions blindly adopted from other continental institutions, mainly from the EU. The process, mechanisms and institutions employed to realize the African Union must be conceived based on African norms, culture and socio-economic and political realities, which is different from the EU and Asia.

In the global arena, African countries should join hands to get their voices heard by the international community and secure Africa's right place in the fast changing and dynamic global economy. African must struggle to end the unjust representation of Africa in the UN Security Council and seek a permanent membership in the council. The 35th AU assembly, which is taking place this week in Addis Ababa should take appropriate measures that will end the organization's

existence as a **paper-tiger** and start a new era where the performance of the AU matches its ambitions.

**Mini-Africa Project**

Marking the 35th AU summit and in the framework of one of the flagship projects of the AU, namely, the great African Museum, **Freedom and Equality Party** (FEP) has developed and submitted a project proposal named **"Mini Africa Park"** to the AU commission and concerned Ethiopian government authorities. The project proposes the construction of a grand African park which contains all the cultural and natural heritages of all African countries in Addis Ababa, preferably in the vicinity of the African union.

The construction of the Mini Africa Park, in Addis Ababa is believed to promote the African cultural heritages, registered by UNESCO, but not known to the world, even to many Africans. From Ethiopian perspective, the Mini-Africa Park will add value to the city of Addis Ababa and make her as one of African tourist destinations.

As part of its grand vision of promoting cultural integration and fostering fraternity among the African people, FEP is proud of developing and submitting the project idea to the AU and concerned Ethiopian government officials. We hope the AU and the Ethiopian authorities will consider the project and take action for its realization.

**Freedom and Equality Party,**
**Addis Ababa**
**02/02/2022**
(ጥር 25፣ 2014)

## የአርብቶ አደሩን ማህበረሰብ ተጋላጭነት በዘላቂነት ለማስወገድ የፖሊሲ ትኩረት ሊደረግ ይገባል!!

ከአንድ አመት በላይ በቆየው አውዳሚ ጦርነት ምክንያት በከፍተኛ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ቀውስ ውስጥ የምትገኘው ሀገራችን፣ ከጥቂት ወራት ወዲህ በምስራቅ እና ደቡብ ኢትዮጵያ በተከሰተው ድርቅ በርካታ የአርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር ማህበረሰብ ለከፋ ርሀብ፣ ሞት እና ስደት ተጋልጧል። መንግስትን ጨምሮ ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ድርጅቶች ባወጧቸው ሪፖርቶች መሰረት በሶማሊ ክልል እንዲሁም በምስራቅ እና ደቡብ ኦሮሚያ አካባቢዎች በድርቁ ሳቢያ ከፍተኛ ሰብል ወድሟል፣ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ከብቶች ሞተዋል፣ ከሞት የተረፉት እንስሳት በመኖ፣ ውሀ እና መድሃኒት እጥረት ህይወታቸው ለአደጋ ተጋልጧል። በድርቁ በተጠቁ አካባቢዎች የሚኖረው ማህበረሰብ አሳሳቢ የምግብ ዋስትና እጥረት ያጋጠመው ሲሆን፣ ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆኑ ህጻናት እና እናቶች ለከፍተኛ የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ተጋልጠዋል። በድርቁ ሳቢያ የተጎዱ እንስሳት ዋጋ የቀነሰ ሲሆን፣ ህብረተሰቡ ዋጋቸው እየናረ የሚገኙ የምግብ ሸቀጦች የመግዛት አቅሙ ተመናምኗል።

ድርቁ ቀደም ሲል በሀገራችን የተከሰተው የአንበጣ መንጋ በግብርናው ዘርፍ ላይ ካሳደረው ጉዳት ጋር ተዳምሮ ሰብአዊ ቀውሱን አባብሶታል። የድርቁን አደጋ ለመቋቋም ፈጣን እና የተቀናጀ ጥረት ካልተደረገ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የአርብቶ አደሩ እና ከፊል አርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ለጉዳት ሊዳረግ እንደሚችል ስጋት ፈጥሯል። የድርቁን አደጋ ለመቋቋም እስከ አሁን በድርቁ የተጠቁ ክልሎች መስተዳድሮች፣ የፌዴራል መንግስት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ሀገር በቀል እና የውጭ ድርጅቶች፣ የክልል መንግስታት ... አስቸኳይ የነፍስ አድን ድጋፍ ለማድረግ በመንቀሳቀስ ላይ ቢሆኑም፣ የድርቁ ስፋት እና ጉዳት እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ ሰብአዊ ቀውሱን መቆጣጠር አልተቻለም። በዚህ ምክንያት አደጋው ከቀን ወደ ቀን እየከፋ መጥቷል።

በመሆኑም ድርቁ በሰው ህይወት፣ በከብቶች እና በአካባቢ ላይ እያደረሰ ያለውን ሰፊ ጉዳት ለመቋቋም፣ የፌዴራል እና የክልል መንግስታት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ባለሀብቶች እንዲሁም የአለም አቀፉ ማህበረሰብ አፋጣኝ ድጋፍ ያደርጉ ዘንድ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ጥሪውን ያቀርባል። ለሰው እና ለእንስሳት አገልግሎት የሚውል ውሀ፣ ምግብ፣ ለህጻናት እና እናቶች የሚያገለግል የተመጣጠነ ምግብ፣ የእንስሳት መኖ፣ የጤና አገልግሎት በድርቅ ለተጎዱ አካባቢዎች በፍጥነት ማቅረብ ያስፈልጋል።

ሰፊ የአርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር ማህበረሰብ የሚኖርባቸው የሶማሊ፣ አፋር፣ እንዲሁም የተወሰኑ የኦሮሚያ እና የደቡብ ብ/ብ/ህ ክልል ዞኖች ለተደጋጋሚ የድርቅ እና ሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎች ተጋላጭ መሆናቸው ይታወቃል። እነዚህ አካባቢዎች ለረዥም ዘመናት የመንግስት ፖሊሲ ትኩረት ስለተነፈጋቸው በቂ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መሰረተ ልማቶች አልተዘረጉላቸውም። በዚህ ምክንያት በተለያዩ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች በተደጋጋሚ የሚጠቁ ሲሆን ህብረተሰቡም ለአስከፊ ሰብአዊ ቀውስ ተጋላጭ ሆኗል።

በመሆኑም በአሁኑ ወቅት በሶማሊ እና ኦሮሚያ ክልሎች ያገጠመውን ድርቅ ለመቋቋም ከሚደረገው ጥረት ባሻገር የአርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎችን ተጋላጭነት ለመቀነስ ብሎም በእነዚህ አካባቢዎች ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ በቂ የፖሊሲ ትኩረት እና ለልማት የሚውል ሀብት መመደብ እንደሚያስፈልግ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ያሳስባል።

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ጥር 9፣ 2014**
**አዲስ አበባ**

# ትኩረት በውጭ ሀገር ለሚኖሩ ወገኖቻችን!

**በመካከለኛው ምስራቅ በእስር ቤቶች የሚማቅቁ ወገኖቻችን አፋጣኝ መፍትሄ ይሻሉ!!**

በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በመካከለኛው ምስራቅ፣ በአፍሪካ፣ በአውሮፓ እና በአሜሪካ ይኖራሉ፡፡ እነዚህ ወገኖቻችን ሀገራችን ውስጥ ባሉ/በነበሩ አስከፊ ድህነት፣ ጸረ ዴሞክራሲያዊ የመንግስት ስርአቶች እና በሌሎች ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ተገደው በባእድ ሀገር በልዩ ልዩ የስራ መስክ የራሳቸውን እና የቤተሰቦቻቸውን ኑሮ ለማሻሻል ይሰራሉ፡፡

በተለያዩ ሀገራት ውስጥ በሚኖሩ ዜጎቻችን ላይ የሚደርሰው ስቃይ፣ እንግልትና መከራ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡ በመካከለኛው ምስራቅ በተለያዩ ሀገራት በግለሰብ እና በድርጅት ውስጥ የሚሰሩ ኢትዮጵያውያን በተለይም ሴት እህቶቻችን በአሰሪዎቻቸው ከፍተኛ የአካል እና የስነልቦና ጉዳት ሰለባ ይሆናሉ፡፡ ባለፉት ዓመታት መንግስት በውጭ ሀገር በተለይም በመካከለኛው ምስራቅ አንዳንድ ሀገራት የሚኖሩ ዜጎችን ወደ ሀገር ቤት ለመመለስ ባደረገው እንቅስቃሴ በርካታ ኢትዮጵያውያንን ወደ ሀገር ቤት እንዲመለሱ ማድረግ ቢቻልም፣ አሁንም በርካታ ዜጎች እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ውስጥ እንደሚገኙ ከአካባቢው የሚወጡ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በተለያዩ ሀገራት ከሚገኙ ወገኖቻችን በሚደርሱት መረጃ፣ ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆነ ኢትዮጵያውያን፣ የዜጎቻችንን ክብር ብሎም ጤንነት እና ደህንነት አደጋ ውስጥ በሚጥል ሁኔታ በተለያዩ እስር ቤቶች ታጉረው እንደሚገኙ ለመረዳት ችሏል፡፡

በውጭ ሀገር የሚኖሩ ዜጎቻችን ክብር የሀገራችን ክብር ነጸብራቅ ነው፡፡ በየትኛውም ሀገር በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ላይ የሚደርስ ኢ-ሰብአዊ ድርጊት በሀገር ሉአላዊነት እና ክብር ላይ የሚደረግ ጥቃት ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡ በሀገር ውስጥ ለሚገኙ ዜጎች ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብት መከበር የምናደርገው ጥረት በባእድ ሀገራት ለሚገኙ ወገኖቻችንም ጭምር ሊደረግ ይገባል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በየትኛውም ሀገር፣ በማንኛውም ጊዜ እና ሁኔታ በወገኖቻችን ላይ የሚደርስን ጥቃት አጥብቆ ይቃወማል፡፡ በመሆኑም በውጭ ሀገር የሚገኙ ዜጎቻችን የሚያጋጥማቸውን አደጋ ለመከላከል መንግስት በተለይም የውጭ ጉዳይ ሚንስቴር እና በየሀገሩ የሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች እና ቆንስላ ጽ/ቤቶች ኃላፊነታቸው በሚገባ እንዲወጡ እያሳሰበ፣ በአደጋ ውስጥ ለሚገኙ ዜጎቻችን አፋጣኝ ድጋፍ እና ትብብር እንዲያደርጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

በተለያዩ ሀገራት በአደጋ ውስጥ የሚገኙ ዜጎቻችንን በተለይም ሰብአዊነት በጎደለው መንገድ በእስር ቤቶች የሚማቅቁ ዜጎችን ጉዳይ ልዩ ትኩረት በመስጠት፣ መረጃ በማጠናቀር ለችግሮቻቸው ዘላቂ መፍትሄ መፍጠር ይቻል ዘንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ማህበራት፣ የሰብአዊ መብት ተቋማት እና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት የበኩላቸውን ጥረት እንዲያደርጉ ነእፓ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በውጭ ሀገር በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን ሁኔታ በቅርብ በመከታተል ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ ከመንግስት እና አዲስ አበባ ከሚገኙ የሚመለከታቸው ሀገራት ኤምባሲዎች ጋር በቅርብ ዙሪያ ለመነጋገር ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

**በውጭ ሀገር የሚገኙ ዜጎቻችንን ችግር በጋራ ለመፍታት እንረባረብ፡፡**

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ጥር 7፣ 2014**
**አዲስ አበባ**

# ጠንካራ እና ዘመኑን የዋጀ የሀገር መከላከያ ተቋም የሀገር ህልውና መሰረት ነው!!

ሀገራችን ኢትዮጵያ በርካታ የውስጥ እና የውጭ የደህንነት ስጋቶች አሉባት፡፡ ግጭቶች በበዙበት የአፍሪካ ቀንድ እምብርት ላይ የምትገኘው ሀገራችን በተለያየ አጋጣሚ ግዛቷን ሊቀራመቱ ነጻነቷን ሊደፍሩ ከሞከሩ የቅርብ እና እሩቅ ጠላቶች ጋር ተፋልማለች፡፡ የሀገራችን የደህንነት ስጋቶች በዘመናችንም አልተወገዱም፤ እንዲያውም በቴክኖሎጂ የታገዙ እና ውስብስብ እየሆኑ መጥተዋል፡፡ ዓለም አቀፍ የደህንነት ስጋት ምንጮች የሆኑት ድንበር ተሻጋሪ የሽብር ጥቃቶች፣ የአካባቢ መጎሳቆል እና ስደት፣ ድህነት እና ሰብአዊ ቀውስ፣ በፍጥነት እያደገ የመጣው ሉላዊነት፣ የመከላከያ ቴክኖሎጂ ምጥቀት እና ውስብስበት (Sophistication)፣ ወዘተ የሀገራችንም የደህንነት ስጋት ምንጮች ናቸው፡፡

እነዚህን የደህንነት ስጋቶች በአስተማማኝ መንገድ ለመመከት፣ የሀገርን የምድር እና የአየር ክልል ለመጠበቅ፣ የሀገራችንን ሰላም እና የዜጎችን ደህንነት ለመታደግ፣ ግዙፍ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ አውታሮች ደህንነት ለማረጋገጥ አስተማማኝ የመከላከያ ኃይል መገንባት ያስፈልጋል፡፡ የሀገራችን የመከላከያ ኃይል ዘመኑ ያፈራቸውን ቴክኖሎጂዎች የታጠቀ፣ የሰራዊቱ አባላትም በበቂ የመከላከያ እና የደህንነት እውቀት እና ክህሎት የተካኑ ሊሆኑ ይገባል፡፡

ከዚህ አንጻር ሰሞኑን የተመረቀው አዲሱ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ዋና መስሪያ ቤት የሀገራችንን የመከላከያ አቅም ከማጎልበት አንጻር በጎ ጅማሮ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ አዲሱ የመከላከያ ዋና መስሪያ ቤት ዘመኑ ያፈራቸው የኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ፣ ደረጃቸውን የጠበቁ የስልጠና ማዕከላት፣ በቂ እና ምቹ የስራ ከባቢ እና ሌሎች የሀገራችንን የመከላከያ ዘርፍ አቅም ሊያሳድጉ የሚችሉ ግብአቶች እና አገልግሎቶች እንዳሉት ተገልጿል፡፡

**ከፓርቲ ገለልተኛ የመከላከያ ተቋም**

የሀገር መከላከያ ተቋም ተልዕኮ የሀገርን ሉዓላዊነት እና የዜጎቿን ሰላም መጠበቅ እንዲሁም ለሀገሪቱ ህገ መንግስት ዘብ መቆም ነው፡፡ በመሆኑም የመከላከያ ተቋማት ከፓርቲ ጣልቃገብነት ራሳቸውን ሊጠብቁ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ ፓርቲ እና መንግስት በተቀላቀሉባት ሀገራችን፣ በመከላከያ ተቋማት ውስጥ የፓርቲ ጣልቃ ገብነት የሀገራችን የመከላከያ ተቋም መሰረታዊ ችግር ሆኖ ቆይቷል፡፡ በተለይም በኢህአዴግ መራሹ መንግስት የመከላከያ ተቋማትን የአንድ ፓርቲ ፕሮግራም እና አጀንዳ ማስፈጸሚያ እንዲሆኑ መደረጉ በተቋሙ ብቃት እና ጥንካሬ እንዲሁም በሀገር ሰላም እና በዜጎች ደህንነት ላይ ትልቅ አደጋ አስከትሏል፡፡ ይህንን ብልሹ አሰራር እና ባህል ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡

የመከላከያ ሚንስቴር እና ተጠሪ ተቋማት በሚያደርጉት የሪፎርም እንቅስቃሴ የተቋማቱን ገለልተኝነት ማረጋገጥ እና ከፓርቲ ጣልቃ ገብነት ራሳቸውን ነጻ ማድረግ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ጥር 4፣ 2014**
**አዲስ አበባ**

# የሰሜኑን ጦርነት በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚደረግን ጥረት ነኢፓ በጽኑ ይደግፋል!!

## በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በመካሄድ ላይ ያለውን ጦርነት መንግስት በሰላማዊ መንገድ ለመቋጨት ያሳለፈውን ውሳኔ አስመልክቶ ከነኢፓ የተሰጠ የአቋም መግለጫ፡፡

### ልዩነቶቻችንን በውይይት መፍታት በሀገራችን ዘላቂ ሰላም ለመፍጠር የተሻለው መንገድ ነው!!

በሰሜን ኢትዮጵያ ከአንድ ዓመት በላይ የዘለቀው ጦርነት ሀገራችንን ከፍተኛ እና ፈርጀ ብዙ ዋጋ አስከፍሏታል፡፡ የጦርነቱ ሰብአዊ እና ቁሳዊ ኪሳራ የትየለሌ ነው፡፡ ጦርነቱ በሺዎች ለሚቆጠሩ ዜጎች ህይወት መጥፋት እና የአካል ጉዳት፣ ለሚሊዮኖች መፈናቀል፣ ለሴቶች፣ ህጻናት እና አረጋውያን እጅግ አሰቃቂ እና አስነዋሪ ጥቃት መዳረግ ምክንያት ሆኗል፡፡ በትግራይ ክልል የተጀመረው ጦርነት በአፋር እና አማራ ክልሎች የተስፋፋ ሲሆን፣ በጦርነቱ ቀጥታ ጉዳት ከደረሰባቸው ክልሎች በተጨማሪ መላ የሀገራችን ህዝቦች የጦርነቱን ገፈት ቀምሰዋል፡፡ ጦርነቱ የፈጠረው ቁርሾ እና ቂም የዜጎች ማህበራዊ ግንኙነት በእጅጉ እንዲሻከር ያደረገ ሲሆን አንድነታችን እንዲሸረሸር አድርጓል፡፡

ጦርነቱ በሀገራችን ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ውድመት ያሳደረ ሲሆን፣ በተለይም ዝቀተኛ ገቢ ባላቸው በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎቻችን ህይወት ላይ ሊገመት የማይችል ተጽኖ ፈጥሯል፡፡ ግጭት በተካሄደባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ የመሰረተ ልማት አውታሮች ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፍተኛ ሁኔታ ወድመው አገልግሎት መስጠት ከማይችሉበት ደረጃ ደርሰዋል፡፡ ቀደም ሲል በኮቪድ 19 የተጎዳው የሀገራችን ምጣኔ ሀብት፣ በጦርነቱ ምክንያት ይበልጥ ተዳክሟል፡፡ ጦርነቱ በአማራ፣ በአፋር እና በትግራይ ክልሎች ቁጥራቸው ከፍ ያለ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በርሀብ እና በሞት አደጋ ውስጥ እንዲወድቁ አድርጓል፡፡

የፌዴራሉ መንግስት እና የክልል መስተዳድሮች አብዛኛውን በጀታቸውን ለጦርነቱ እና ከጦርነቱ ጋር ለተያያዙ ፕሮጀክቶች እንዲውሉ በማድረጋቸው መደበኛ የልማት ስራዎች እንዲቀዛቀዙ፤ በዚህም ምክንያት መንግስት ለዜጎች ሊያቀርባቸው የሚገቡ ማህበራዊ አገልግሎቶች እንዲቋረጡ ሆነዋል፡፡ ጦርነቱ የሀገራችን ዋነኛ ጠላት ከሆነው ድህነት ለመላቀቅ ከምናደርገው የሞት ሽረት ትግል እንድንዘናጋ ያደረገን ሲሆን፣ ታላቁ የህዳሴ ግድብን ጨምሮ በሌሎች ግዙፍ ሀገራዊ የልማት ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል፡፡

በጦርነቱ ሳቢያ የኃያላን ሀገራት ዲፕሎማሲያዊ ጫናዎች እየበረቱ መጥተው የሀገራችን የውጭ ግንኙነት ከፍተኛ ተግዳሮት ገጥሞታል፡፡ አንዳንድ የምዕራቡ ኃያላን መንግስታት እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጦርነቱን አስመልክቶ በያዙት አቋም በሀገራችን ላይ ፈርጀ ብዙ ጫናዎች አሳድረዋል፤ ማዕቀቦችም ጥለዋል፡፡ ቁጥራቸው ትንሽ የማይባል ዓለም አቀፍ የሚዲያ ተቋማት ሀገራችንን አስመልክቶ በሚያስተላልፉት ዘገባ የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በኢትዮጵያን ላይ የተሳሳተ አመለካከት እንዲኖረው አድርገዋል፡፡ በውጤቱም በሀገራችን ገጽታ፣ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት፣ የውጭ ምንዛሬ ፍሰት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ በረዥም የመንግስትነት ታሪኳ ዛሬ ላይ የገጠመንን አይነት አያሌ የእርስ በእርስ ጦርነቶችን አስተናግዳለች፡ ፡ በስልጣን ሽኩቻ፣ በወሰን ይገባኛል፣ በሀይማኖት ወዘተ የተደረጉ ደም አፋሳሽ ጦርነቶች ሀገራችንን እጅግ ውድ ዋጋ አስከፍለዋታል፡፡ በእርስ በርስ ጦርነት ምክንያት በየዘመኑ ቁጥራቸው እጅግ ከፍተኛ ኢትዮጵያውያን ውድ ህይወት አልፏል፣

የሀገራችን አንጡራ ሀብት ወድሟል፡፡ ይሁን እንጂ በተደረጉ ጦርነቶች ለጦርነት መንስኤ የሆኑ ልዩነቶች ከስር መሰረታቸው አልተፈቱም፡፡ በእርስ በርስ ጦርነት ረዥም ዘመናት ያሳለፈችው ሀገራችን ግጭት፣ ድህነት፣ ርሀብ፣ እርዛት፣ ልመና ብሄራዊ መገለጫዎቿ ሆነዋል፡፡ በወንድማማች ህዝቦች መካከል የሚካሄድ የእርስ በርስ ጦርነት አሸናፊ እና ተሸናፊ የሌለው፣ ችግሮችን ከመፍታት ይልቅ ይበልጥ የሚያወሳስብ አውዳሚ ክስተት ነው፡፡

በየትኛውም ቦታ እና ጊዜ የሚካሄድ ጦርነት በሰው ኃይል፣ በገንዘብ እና በሀገር አንጡራ ኃብት ላይ ከፍተኛ ኪሳራ የሚያደርስ ሲሆን እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ድሀ ሀገራት ላይ ደግሞ የጦርነት ሁለንተናዊ ተጽዕኖ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ እውነታ በመነሳት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በመካሄድ ላይ ያለው ጦርነት በሀገራችን እና በህዝቦቿ ላይ ያስከተለውን ሁለንተናዊ ጉዳት መገመት አይከብድም፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በመካሄድ ላይ ያለው ጦርነት እስከ አሁን ያስከተለውን ሁለንተናዊ ጉዳት እና ጦርነቱ ከዚህ በላይ ቢራዘም በሀገራችን እና በህዝቦቿ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን እጅግ አውዳሚ ጉዳት ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ መንግስት ጦርነቱን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የወሰደውን እርምጃ ወቅታዊ እና ተገቢ ነው ብሎ ያምናል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በሀገራችን ዘላቂ ሰላም እና የተረጋጋ የፖለቲካ ምህዳር እንዲፈጠር መንግስት በተለይ ከጦርነቱ አስቀድሞ በቁጥጥር ስር አውሏቸው የነበሩ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮች የክስ ሂደት እንዲቋረጥ ማድረጉን **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በአወንታዊ መልኩ ተመልክቶታል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በሀገራችን እውነተኛ ሰላም እና መረጋጋትን ለማረጋገጥ ቀላሉ እና አዋጭ የሆነው መንገድ በልዩነቶቻችን ዙሪያ ጥልቅ ውይይት ማድረግ እንደሆነ በጽኑ ያምናል፡፡ ከዚህ የፖለቲካ እምነቱ በመነሳት ፓርቲያችን ጦርነቱ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ የሰላም አማራጮች እንዳይዘነጉ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ መቆየቱ የሚታወስ ሲሆን ጦርነቱ ሲካሄድ በቆየባቸው ወራቶችም ችግሩ በሰላማዊ መንገድ ይፈታ ዘንድ አማራጭ መንገዶች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሲያሳስብ ቆይቷል፡፡ መንግስት ጦርነቱን በሰላም ለመቋጨት የወሰደው እርምጃ በጦርነቱ ምክንያት ሀገራችን እና ህዝቦቿ እየከፈሉ ያሉትን ከፍተኛ ዋጋ ከማስቆም እና በሀገራችን የፖለቲካ መረጋጋትን ለመፍጠር ካለው ፋይዳ ባሻገር፣ በሀገራችን ሊካሄድ ለታሰበው ሁሉን አቀፍ ሀገራዊ ምክክር ስኬታማነት አወንታዊ ሚና ይኖረዋል ብለን እናምናለን፡፡

እውነተኛ ሀገራዊ ምክክር እና መግባባት የፖለቲካ አስረኞች በእስር ቤት ባሉበት እንዲሁም በአንደኛው የሀገራችን ጫፍ አውዳሚ ጦርነት እየተካሄደ ባለበት ሁኔታ ሊካሄድ አይችልም፡፡ እውነተኛ ሀገራዊ መግባባት ሊካሄድ የሚችለው ዜጎች በሂደቱ ላይ እምነት ሲኖራቸው እና ይወክሉናል የሚሏቸው አካላት በነጻነት መሳተፍ በሚችሉበት የፖለቲካ አውድ ውስጥ ብቻ እና ብቻ ነው፡፡

መላው የሀገራችን ህዝቦች ሁሌም የሚናፍቁት እውነተኛ ሰላም ይረጋገጥ ዘንድ፣ መንግስት ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነት በአስተማማኝ ሁኔታ ሊያሳይ በሚችል መልኩ ሌሎች አስፈላጊ የፖለቲካ እና የህግ ማሻሻያዎችን ሊያደርግ ይገባል፡፡ ኃላፊነት የሚሰማው መንግስት ወደ ጦርነት ሲገባም ሆነ ጦርነትን ለማቆም የሚወስናቸው ውሳኔዎች ግልጽነት፣ ተጠያቂነት እንዲሁም የሀገርን እና የህዝቦቿን ዘላቂ ጥቅም የሚያስከብሩ ሊሆን ይገባል፡፡

በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ህብረ-ብሄራዊ አንድነት ለሀገራችን ዘላቂ ሰላም መሰረት ነው ብሎ በጽኑ የሚያምነው **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ጦርነቱ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ሙሉ በሙሉ እንዲቆም እንዲሁም ሁሉን አቀፍ እና እውነተኛ ብሄራዊ ምክክር እንዲካሄድ ሲያደርገው የነበረውን ጥረት አጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ይገልጻል::

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ጥር 2፣ 2014**
**አዲስ አበባ**

# “እንኳን ወደ ውድ ሀገራችሁ በሰላም መጣችሁ”

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚንስትር ክቡር ዶ/ር አብይ አህመድ አሊ በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው እንዲመጡ ያደረጉትን ጥሪ ተቀብላችሁ ወደ ትውልድ ሀገራችሁ ለመጣችሁ እና በመምጣት ላይ ለምትገኙ ወገኖቻችን እንኳን ወደ እናት ሀገራችሁ በሰላም መጣችሁ እንላለን::

ሀገራችን ኢትዮጵያ በሰሜኑ ክፍል በጦርነት፣ በምስራቅ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገራችን አካባቢዎች በድርቅ በተጎዳችበት በአሁኑ ወቅት፣ የሀገራችሁን ሁኔታ በቅርብ ለማየት እና የወገኖቻችሁን ችግር እና ደስታ ለመጋራት፣ የዓውድ ዓመት ደስታን ከወገናችሁ ጋር ለመካፈል ወደ ሀገራችሁ መምጣታችሁ እጅግ የሚያኮራ ተግባር ነው::

**በውጭ ሀገር የሚገኙ ወገኖቻችን ወደ ሀገር ቤት መምጣት ሰፊ እንድምታ እና ትርጉማ አለው፤**

- በጦርነቱ ምክንያት የተፈጠረውን የሀገር ገጽታ መልሶ ለመገንባት፣ አንዳንድ የውጭ መንግስታት፣ አለምዓቀፍ ድርጅቶች እና የሚዲያ ተቋማት ኢትዮጵያን በተመለከተ ያሰራጩትን የተዛባ መረጃ ለማስተካከል፣ የሀገራችንን እውነተኛ አሁናዊ ሁኔታ ለዓለም ለማሳየት በውጭ ሀገር የምትገኙ ወገኖቻችን ወደ ቀያችሁ መመለስ ትልቅ ዲፕሎማሲያዊ ትርጉም አለው፣
- በኮቪድ 19፣ በጦርነት እና በቅርቡ በአንዳንድ የሀገራችን አካባቢዎች በተከሰተው ድርቅ የተጎዳው የሀገራችን ኢኮኖሚ እንዲያገግም፣ በውጭ ንግድ መቀዛቀዝ እና ዲፕሎማሲያዊ ጫና ምክንያት የተመናመነው የሀገራችን ውጭ ምንዛሬ ክምችት እንዲያንሰራራ የዜጎች የሀገር ቤት ጉብኝት ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ አለው፣
- በበዓል ዋዜማ ለበርካታ አመታት ከተለያችሁ ቤተሰብ፣ ወዳጅ፣ ዘመድ፣ ጓደኛ ጋር ተገናኝቶ አመት በዓል በጋራ ማክበር ትልቅ ባህላዊ እና ማህበራዊ ትሩፋት አለው፣
- የበርካታ ዜጎችን ህይወት ከቀጠፈው እና አያሌዎችን ለአካል ጉዳተኝነት ከዳረገው፣ ሚሊዮኖችን ከቤት ንብረታቸው ካፈናቀለው፣ የሀገራችንን ሰፊ አንጡራ ሀብት ካወደመው አስከፊ ጦርነት ወጥተን ሁሉን አቀፍ ብሄራዊ ውይይት ለማድረግ እንደ ሀገር ሰፊ ዝግጅት በማድረግ ላይ ባለንበት ወቅት የኢትዮጵያ ልጆች ወደ ሀገራችሁ መምጣት ትልቅ ፖለቲካዊ እንድምታ አለው፣

ውድ የሀገራችን ልጆች፣ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ (ነእፓ)** በድጋሚ እንኳን ወደ ሀገራችሁ በሰላም መጣችሁ እያለ ቆይታችሁ፣ የሰላም፣ የደስታ እና የጤና እንዲሆን ይመኛል:: በዚሁ አጋጣሚ በተለይ ለክርስትና እምነት ተከታይ እንግዶቻችን ከወዲሁ መልካም የገና እና የጥምቀት በአል እንዲሆንላቸሁ **ነእፓ** ልባዊ ምኞቱን ይገልጻል::

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**አዲስ አበባ**
**ታህሳስ 21፣ 2014**

# “የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን”ን ለማቋቋም መንግስት የወሰደው ተነሳሽነት የሚደገፍ ነው

***ለብሄራዊ ምክክሩ ሰኬታማነት መንግሰት ግልጽ እና አሳታፊ አሰራርን ሊከተል ይገባል!!***

ሀገራችን ኢትዮጵያ ለረዥም ዘመናት ቀስፈው ከያዟት ውስብስብ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ችግሮች ተላቃ የሀገራችንን ሰላም በማረጋገጥ የዜጎችን ደህንነት በአስተማማኝ ሁኔታ መጠበቅ ይቻል ዘንድ በአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል እና የፖለቲካ ሊሂቃን ሲቀርቡ ከነበሩ የፖለቲካ ጥያቄዎች አንዱና ዋነኛው **አካታች አገራዊ ምክክር** ማካሄድ መሆኑ ይታወሳል፡፡ በሀገራችን የቅርብ እና ሩቅ ታሪክ የተከሰቱ ፖለቲካዊ፣ አስተዳደራዊ፣ ማህበራዊ ቀውሶች በዜጎች መካከል ከፍተኛ መቃቃርን ፈጥረው በተለያዩ የታሪክ ምዕራፎች እጅግ አውዳሚ ለሆነ የእርስ በርስ ጦርነቶች ዳርገውናል፡፡ በዚህም ምክንያት ከፍተኛ የሰው ሀይል እና ሰፊ የሀገራችን አንጡራ ሀብት ወድሟል፡፡ የቂም እና የበቀል ፖለቲካ በሀገራችን ከፉኛ ናኝቶ፣ የመከባበር፣ የመደማመጥ እና የመደራደር ባህል ርቆናል፡፡

በኢትዮጵያ ረዥም የመንግስት ታሪክ ውስጥ ስልጣን በሰላማዊ መንገድ የማሸጋገር የፖለቲካ ባህል የለንም፡፡ ይህ ልዩነቶችን በጦርነት የመፍታት ባህል ዛሬም አልለቀቀንም፡፡ በብዝሀነት የከበርን ኢትዮጵያውያን ያሉንን የቋንቋ፣ የባህል፣ የእምነት እና ሌሎች ማንነቶች ማስታረቅ አቅቶን፣ ባልተስማማንባቸው ጉዳዮች ዙሪያ አንዱም ቁጭ ብለን መመካከር ሳንችል በርካታ ትውልድ እና ስርዓቶች አልፈዋል፡፡ ረጅሙ የጦርነት እና የግጭት ታሪካችን ሀገራችን ላለችበት አስከፊ ድህነት፣ ማህበራዊ ቀውስ እና የፖለቲካ አለመረጋጋት ዳርጎናል፡፡ ከዚህ የግጭት አዙሪት ለመውጣት እውነተኛ እና ሁሉን አካታች ሀገራዊ ምክክር በማድረግ አዲስ የእርቅ፣ የሰላም፣ የአንድነት፣ የእኩልነት እና የወንድማማችነት ምዕራፍ ልንጀምር ይገባል፡፡ ሀገራችን ካለችበት ፈታኝ አሁናዊ የፖለቲካ እና ማህበራዊ ተግዳሮቶች ለመላቀቅ፣ እንደ ሀገር ለዘመናት የምንሸከረከርበትን የግጭት አዙሪት በጥሰን ለመውጣት፣ ከውስጥ እና ከውጭ የገጠሙንን የህልውና አደጋዎች በአስተማማኝ ሁኔታ ለማለፍ የተሳካ ሀገራዊ ምክክር በማድረግ እርቅና ሰላምን ማስፈን የሀገራችን እጅግ አንገብጋቢ የፖለቲካ አጀንዳ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር መንግስት **“ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን”** ለማቋቋም የወሰደውን ተነሳሽነት **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ (ነእፓ)** በአድናቆት ይመለከተዋል፡፡ **ነእፓ** ባለፉት ሁለት ዓመታት በሀገራችን ሁሉን አቀፍ ብሄራዊ ውይይት (National Dialogue) ይካሄድ ዘንድ ሰፊ እንቅስቃሴ ሲያደርግ እና መንግስትም ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ ጥሪ ሲያቀርብ ቆይቷል፡፡ ከዚህ አንጻር መንግስት ኃላፊነቱን ወስዶ ይህንን ስራ የሚያስተባብር ተቋም ለማቋቋም መወሰኑ አበረታች እርምጃ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ይህ መልካም ተነሳሽነት ፍሬ አፍርቶ መላው የሀገራችን ህዝቦች በጉጉት የሚናፍቁት ሰላም በሀገራችን ይሰፍን ዘንድ መንግስት እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ለሚከተሉት ነጥቦች ትኩረት እንዲሰጡ **ነእፓ** ምክረ ሀሳቡን ያቀርባል፣

1. በሚኒስትሮች ምክር ቤት እንደፀደቀ የተነገረው ረቂቅ የኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ከመጽደቁ በፊት ባለድርሻ አካላት በተለይም የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ማህበራት፣ የሚዲያ ተቋማት እና ህዝቡ ረቂቅ አዋጁን ተመልክተው ሀሳባቸውን እንዲሰጡ ቢደረግ ሂደቱ ገና ከጅምሩ አሳታፊ እንዲሆን እድል ይፈጥራል፡፡ ይህም የኮሚሽኑን ቅቡልነት ለማሳደግ እና ሰፊ የህዝብ ይሁንታ እንዲያገኝ ይረዳል፡፡

2. ሀገራዊ ምክክር ውጤታማ ይሁን ዘንድ ከዝግጅት ምዕራፍ ጀምሮ እስከ አተገባበር ከፍተኛ ጥንቃቄ፣ ግልጽነት፣ እና ቁርጠኝነትን ይጠይቃል። ለተሳካ የሀገራዊ ምክክር የመንግስት ድጋፍ ወሳኝ መሆኑ እሙን ቢሆንም፣ ሂደቱ ከመንግስት ጫና እና የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ነጻ እንዲሆን ማድረግ አጅግ አስፈላጊ ነው። ከዚህ አንጻር በተለይ የምክክሩን ተሳታፊዎች እና አወያዮች በመምረጥ እና አጀንዳዎችን በመቅረጽ ሂደት ተቋሙ በነጻነት መስራት ይችል ዘንድ ግልጽ የህግ ማእቀፍ እና ከለላ ሊኖረው ይገባል።

3. ከሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ፣ ስኬታማ የብሄራዊ ምክክር አስቻይ የህግ እና የፖለቲካ ምህዳር ይፈልጋል። በመሆኑም የምክክር ሂደቱን ቅቡልነት ከፍ ሊያደርጉ የሚችሉ፣ በተሳታፊዎች መካከል መተማመንን ሊፈጥሩ የሚችሉ ህጋዊ እና ፖለቲካዊ መደላድሎችን መፍጠር ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ለብሄራዊ ምክክር ምቹ ከባቢ ባልተፈጠረበት ሁኔታ የሚካሄድ ሀገራዊ ምክክር ሂደቱ ከባድ ከመሆኑም በላይ የሚጠበቀው ውጤት እንዳይገኝ እንቅፋት ይሆናል።

4. ሀገራዊ ምክክር ከፍተኛ እውቀት እና ልምድ የሚጠይቅ፣ ሰፊ የንድፈ ሀሳብ እና የተግባር እንዲሁም ዓለም አቀፍ ተሞክሮን የሚጠይቅ የፖለቲካ ስራ ነው። በመሆኑም በዚህ ስራ የሚሳተፉ የስራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ምደባ በከፍተኛ ጥንቃቄ ሊከናወን የሚገባው ሲሆን፣ በተለይም ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ ኮሚሽነሮች ገለልተኛ፣ ሙያዊ ብቃት እንዲሁም የህዝብ አመኔታ እና ተቀባይነት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል። ከሙያዊ ብቃት ባሻገር የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች አሰያየም የሀገራችንን ህዝቦች ብዝሀነት ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ የብሄር፣ የእምነት እና የጾታ ስብጥርን ታሳቢ ያደረገ ሊሆን ይገባል።

5. የተሳካ ሀገራዊ ምክክር ተካሂዶ በሀገራችን እርቅ እና ሰላም ይወርድ ዘንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ድርሻ የላቀ ነው። በመሆኑም የፖለቲካ ድርጅቶች አመራሮች እና አባላት በከፍተኛ ኃላፊነት እና ተጠያቂነት ስሜት ለሂደቱ መሳካት የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል። እያንዳንዱ የፖለቲካ ድርጅት የሚያራምደው የፖለቲካ ፍልስፍና እና ፍላጎት እውን እንዲሆን በሚያደርገው ጥረት የሌሎች የፖለቲካ ኃይሎችን ሀሳብ እና ፍላጎት በቅጡ በማድመጥ እና በመረዳት "**አብሮ በማሸነፍ**" መርህ ልዩነቶቻቸውን ለመፍታት ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል፣

6. በሀገራዊ ምክክር ሂደት የጋራ ስምምነት የሚደረስባቸው አጀንዳዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ከዚህ አንጻር በፌዴራልም ሆነ በክልል የሚገኙ አስፈጻሚ አካላት ከፓርቲ ወገንተኝነት በራቀ ሁኔታ የኮሚሽኑን ውሳኔዎች ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል።

7. ባለፉት ሶስት ዓመታት ልዩ ልዩ ተቋማት በአዋጅ እንዲቋቋሙ መደረጉ የሚታወስ ሲሆን ከእነዚህ ተቋማት መካከል **የእርቀ ሰላም ኮሚሽን እና የአስተዳደር ወሰን እና የማንነት ጉዳዮች ኮሚሽን** ይገኙበታል። እነዚህ ትልልቅ ሀገራዊ ተቋማት ሲቋቋሙ በብዙዎች ዘንድ ከፍተኛ ተስፋ ተጥሎባቸው የነበረ ሲሆን፣ ከፍተኛ የሀገር ሀብትም ፈሶባቸዋል። ይሁን እንጂ የኮሚሽኖቹ እንቅስቃሴ ከተጠበቀው አንጻር ሲታይ ለብዙዎች አጥጋቢ አይደለም። ከዚህ ልምድ በመነሳት አዲስ የሚቋቋመው **"ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን"** የተጣለበትን ከፍተኛ ታሪካዊ ኃላፊነት በአግባቡ ይወጣ ዘንድ ተገቢ ትኩረት እና ድጋፍ ሊደረግለት ይገባል።

በመጨረሻም **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በሀገራችን የተሳካ ብሄራዊ ምክክር ይካሄድ ዘንድ እስከ አሁን ሲያደርገው የነበረውን እንቅስቃሴ በማጠናከር እውነተኛ ብሄራዊ መግባባት እና እርቅ በሀገራችን እውን ይሆን ዘንድ የድርሻውን ለመወጣት የሚሰራ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ያረጋግጣል።

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ታህሳስ 5፣ 2014**
**አዲስ አበባ**

# የነእፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ እና ያስተላለፋቸው ውሳኔዎች

የነእፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ባደረገው ስብሰባ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በመካሄድ ላይ ያለውን ግጭት ጨምሮ በሌሎች ወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች፣ እንዲሁም በ6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ የፓርቲው ተሳትፎ ዙሪያ ሰፊ ውይይት አድርጓል። ኮሚቴው በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በመካሄድ ላይ ያለውን ግጭት ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ማህበራዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ጫናዎች እና እንድምታዎች በዝርዝር ተመልክቷል።

በትግራይ ተጀምሮ በአማራ እና በአፋር ክልሎች በተስፋፋው ጦርነት ምክንያት በበርካታ ዜጎች ላይ የደረሰው የሞት፣ የአካል ጉዳት፣ የንብረት ውድመት እጅግ እንዳሳሰበው የገለጸው የነእፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ፣ የዜጎችን ደህንነት እና የሀገርን ህልውና ከፍተኛ አደጋ ላይ የጣለው ጦርነት በአጭር ጊዜ ተጠናቆ በሀገራችን አስተማማኝ ሰላም እና መረጋጋት ይሰፍን ዘንድ የሚመለከታቸው አካላት ታሪካዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪ ያቀረበ ሲሆን፣ ፓርቲው ጦርነቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ይቆም ዘንድ በማድረግ ላይ ያለውን እንቅስቃሴ ይበልጥ አጠናክሮ እንደሚቀጥል አረጋግጧል።

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ካለው ግጭት በተጨማሪ በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች ያሉ ግጭቶች በዜጎች ህይወት እና ንብረት እንዲሁም በሀገር ሰላም እና መረጋጋት ላይ እያሳደሩ ያለውን ተጽእኖ በተመለከተ በቀረበ የውይይት መነሻ ሀሳብ ዙሪያ ሰፊ ውይይት የተካሄደ ሲሆን፣ የዜጎችን ማንነት መሰረት በማድረግ በዜጎች ላይ የሚደረግን ማንኛውም ዓይነት ጥቃት ነእፓ በጽኑ እንደሚያወግዝ ተመልክቷል። ባለፉት ሶስት ዓመታት እየጨመረ የመጣውን ማንነትን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ለማስቆም መንግስት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራ ማዕከላዊ ኮሚቴው አሳስቧል። ማዕከላዊ ኮሚቴው ሀገራችን ያለችበትን ዘርፉ ብዙ እና እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ፣ የፓርቲው ከፍተኛ የልኡካን ቡድን ከመንግስት ከፍተኛ ኃላፊዎች ጋር በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች መወያየት የሚቻልበት ሁኔታ እንዲመቻች ጠይቋል።

**የሰብአዊ ድጋፍ ጥሪ።**

በግጭት ምክንያት ከመኖሪያ አካባቢያቸው ተፈናቅለው በአስከፊ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ወገኖችን ለመርዳት ዜጎች አቅማቸው በፈቀደ ልክ ድጋፍ እንዲያደርጉ ኮሚቴው ጥሪ አቅርቧል። በጦርነቱ ምክንያት ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉ በመቶ ሺዎች ለሚቀጠሩ ዜጎች በተለይም ሴቶች፣ ህጻናት፣ አረጋውያን እና የአካል ጉዳተኞች መንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አፋጣኝ ሰብአዊ ድጋፍ እንዲያደርጉ ማዕከላዊ ኮሚቴው ጥሪ አቅርቧል።

**6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ**

ማዕከላዊ ኮሚቴው 6ኛው ጠቅላላ ምርጫ አስመልክቶ በብሄራዊ ምርጫ አስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ የቀረበውን ዝርዝር ሪፖርት ተመልክቷል። በዚህም ምርጫው የነበሩበትን የህግ፣ የፖለቲካ፣ የአስተዳደር፣ የሎጂስቲክ እና ሌሎች ዝርዝር የአፈጻጸም ችግሮችን የዳሰሰ ውይይት ተካሂዷል። ከምርጫው ጋር ተያይዞ ነእፓ በምርጫው በነበረው ተሳትፎ የታዩ ጠንካራ

ጎኖች እና ጉድለቶች ዙሪያ ጥልቅ ውይይት ተደርጓል፡፡ ማዕከላዊ ኮሚቴው ፓርቲው በ6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ ያገኛቸው ተሞክሮዎች ለቀጣይ ምርጫዎች ግብአት በሚሆን መልኩ ተሰንደው እንዲቀመጡ አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡

**አዲስ መንግስት ምስረታ ሂደት**

ማዕከላዊ ኮሚቴው የአዲስ መንግስት ምስረታ ሂደትን የገመገመ ሲሆን ለሀገር ሰላም እና ደህንነት ሲባል የተፎካካሪ ፓርቲዎች በመንግስት አስተዳደር እንዲሳተፉ መደረጉ በጎ ጅማሮ መሆኑ ታምኖበታል፡፡ ነእፓ በገዢው ፓርቲ የቀረበለትን የአብሮ መስራት ጥያቄ በተመለከተ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ከገዢው ፓርቲ ጋር ያደረገውን ውይይት እና የወሰዳቸውን ውሳኔዎች በተመለከተ ኮሚቴው ሰፊ ውይይት አድርጓል፡፡ ኮሚቴው ነእፓን ወክለው በየትኛውም የመንግስት ኃላፊነቶች ላይ የሚሰሩ የፓርቲው አባላት በስራቸው ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ ፓርቲው ድጋፍ እና ክትትል የሚያደርግበት የአሰራር ስርአት እንዲዘረጋ አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡

**አስተዳደራዊ ውሳኔዎች**

ኮሚቴ ከላይ ከተጠቀሱት ሀገራዊ አጀንዳዎች በተጨማሪ፣ በተለያዩ ድርጅታዊ/አስተዳደራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡ በዚህም፣

1. በፓርቲው የ2013 የስራ ክንውን እና የኡዲት ሪፖርት እንዲሁም የ2014 እቅድ ላይ ተወያይቶ አጽድቋል፣
2. የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ በአዋጅ ፱62/2011 መሰረት ለማሻሻል በቀረበው ረቂቅ ላይ ተወያይቶ ከማሻሻያ ጋር ተቀብሏል፡፡ መተዳደሪያ ደንቡ በቅርብ ይካሄዳል ተብሎ በሚጠበቀው የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ ይጸድቃል፣
3. የፓርቲው የአባልነት ክፍያ መጠን ከለሳ የተደረገ ሲሆን፣ የአባላት አመታዊ መዋጮ ብር 100 (አንድ መቶ) እንዲሆን ወስኗል፡፡ ማዕከላዊ ኮሚቴው የአባልነት መዋጮን ዝቅ በማድረግ እና የአከፋፈል ስርዓቱን በማዘመን አባላትን በስፋት ማፍራት የተሻለ እንደሚሆን የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ተቀብሏል፣
4. በመጨረሻም የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ የሚካሄድበትን ጊዜ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች አስመልክቶ ውሳኔዎችን በማሳለፍ የእለቱ ስብሰባ ተጠናቋል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**

**ጥቅምት 15፣ 2014**

**አዲስ አበባ**

## ለአዲሱ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል መልካም ምኞታችንን እንገልጻለን!!

መስከረም 20 2014 በተደረገው ህዝበ ውሳኔ በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል የሚገኙ አምስት ዞኖች እና አንድ ልዩ ወረዳ የክልልነት ጥያቄ በአብላጫ ድምጽ የሕዝብ ድጋፍ አግኝቷል፡፡ በዚህም አዲሱ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ተመስርቷል፡፡

በሕዝቦች መልካም ፈቃድ እና በጠንካራ ፌዴራል ስርዓት ጽኑ እምነት ያለው **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** የፌዴራል ስርዓቱን ለተቀላቀለው አዲሱ ክልል ሕዝቦች እንኳን ደስ አላችሁ እያለ መልካም ምኞቱን ይገልጻል፡፡ አዲስ የሚደራጀው ክልላዊ መንግስት የሕዝቦችን **የነጻነት እና የእኩል** ተጠቃሚነት ጥያቄ እውን ለማድረግ ከፍተኛ የሀገር እና የህዝብ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በአክብሮት እናስታውሳለን፡፡

በሀገራችን አስተማማኝ ሰላም እንዲሰፍን፣ መላው የሀገራችን ሕዝቦች ከድህነት ተላቀው በኢኮኖሚ ያደጉ ሀገር ለመገንባት በዜጎች ፈቃድ እና ስምምነት የሚመሰረት መንግስት አስፈላጊ ነው፡፡ አዲሱ መስተዳድር እንደ ክልል ለመደራጀት በሚያደርገው እንቅስቃሴ ፓርቲያችን አቅሙ በሚፈቅደው ልክ ለማገዝ ያለውን ዝግጁነት ይገልጻል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ጥቅምት ፲፤ 2014**
**አዲስ አበባ**

# ነኢፓ ከመንግስት ለቀረበለት የአብረን እንስራ ጥያቄ የሰጠው ምላሽ

በ6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ አሸናፊ የሆነው ብልጽግና ፓርቲ የተፎካካሪ ፓርቲዎችን በመንግስት ስልጣን ውስጥ ለማሳተፍ ቃል በገባው መሰረት በክልል እና በፌዴራል መንግስት ውስጥ ለተፎካካሪ ፓርቲዎች ሹመት በመስጠት ላይ ይገኛል። በመንግስት ስልጣን ውስጥ እንዲሳተፉ ጥያቄ ከቀረበላቸው ፓርቲዎች አንዱ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** (**ነኢፓ**) ነው። በዚህም መሰረት የፓርቲያችን ሊቀመንበር ዶ/ር አብዱልቃድር አደም በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የካቢኔ አባል እንዲሆኑ ጥያቄ ቀርቦልናል። ይህንኑ ጉዳይ በተመለከት የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር ክቡር ዶ/ር አብይ አህመድ በዛሬው እለት የካቢኔ አባላቶቻቸውን ለፓርላማ ሲያሳውቁ ገልጸዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የአብረን አንስራ ጥያቄው የቀረበበትን ሂደት እና ውጤት አስመልክቶ ማብራሪያ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል።

**ነኢፓ** ብልጽግና ፓርቲ ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር በጋራ ለመስራት ያለውን ፍላጎት አድንቆ፣ በሀገራችን ፖለቲካ ታሪክ አዲስ እና ጠቃሚ በመሆኑ ድጋፉን ገልጿል። በዚሁ መሰረት መስከረም 18፣ 2014 በተቋቋመው የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ ውስጥ ለመሳተፍ ስምምነቱን ገልጾ ከአፈጻጸም ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ከገዢው ፓርቲ ጋር ውይይት አድርጓል።

በተደረገው ውይይት መሰረት በአዲስ አበባ ካቢኔ ውስጥ እንዲሳተፉ በተጠየቅነው የፓርቲያችን ሊቀመንበር ምትክ ሌላ የፓርቲው ከፍተኛ አመራር እንዲሳተፉ ከብልጽግና ፓርቲ ጋር ስምምነት ላይ ተደርሷል። በዚሁ መሰረት ፓርቲውን ወክለው በአዲስ አበባ ካቢኔ አባል እንዲሆኑ የተመረጡትን የነኢፓ አመራር ለብልጽግና ፓርቲ አሳውቀናል። ይሁን እንጂ በአዲስ አበባ ካቢኔ አባል እንዲሆኑ መርጠን የላክናቸው የፓርቲያችን ተወካይ በካቢኔው ሳይካተቱ ቀርተዋል። ይህን በተመለከት ከብልጽግና ፓርቲ የተሰጠን ማብራሪያ የለም።

**ነኢፓ** ሀገርን በጋራ ለማገልገል ተፎካካሪ ፓርቲዎች በመንግስት ስልጣን እንዲሳተፉ ብልጽግና ፓርቲ ለሰጠው እድል ከጅምሩ አድናቆቱን የገለጸ ሲሆን፣ በሀገራችን የመንግስት ታሪክ አዲስ አሰራር በመሆኑ **ነኢፓ** ከገዢው ፓርቲ ጋር አብሮ ለመስራት ዝግጁነቱን ገልጿል። ይሁን እንጂ ይህ አዲስ አሰራር ተግባራዊ ሲደረግ የተፎካካሪ ፓርቲዎች በሂደቱ በግልጽ እንዲሳተፉ ማድረግ በሀገር ደረጃ ለታሰበው አዲስ የፖለቲካ ባህል ውጤታማነት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን እንገልጻለን።

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**መስከረም 26፣ 2014**
**አዲስ አበባ**

# መልካም የስራ ዘመን እንመኛለን!!

በዛሬው እለት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት በጋራ ባደረጉት ስብሰባ የምክር ቤቶቹን አፈጉባኤዎች እና የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆነው እንዲያገለግሉ ዶ/ር አብይ አህመድ አሊን መርጧል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ለዶ/ር አብይ አህመድ እና አዲስ ለሚመሰርቱት መንግስታቸው፣ ለህዝብ ተወካዮች እና ለፌዴሬሽን ምክር ቤት አዲስ አመራሮች፣ እንዲሁም በቅርቡ ለተቋቋሙ አዲስ የክልል መንግስታት ከፍተኛ አመራሮች መልካም የስራ ዘመን እየተመኘ፣ አዲሶቹ የፌዴራል እና የክልል መንግስታት በእውነተኛ የሀገር ፍቅር ስሜት መላውን የሀገራችንን ህዝቦች በቅንነት እና በታማኝነት እንዲያገለግሉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡ በከፍተኛ የሰላም እጦት፣ ማህበራዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ ጫና ውስጥ የምትገኘው ሀገራችን ከአዲሱ መንግስት በርካታ እና አፋጣኝ ውሳኔዎችን ትጠብቃለች፣

- በጦርነት፣ በግጭት እና በፍትህ እጦት የሚንገላቱ በርካታ ዜጎቻችን ከክቡር ጠቅላይ ሚንስትሩ እና ከመንግስታቸው በሀገራችን ዘላቂ ሰላም እና መረጋጋት እውን ይሆን ዘንድ ፈጣን ፖለቲካዊ እና አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን በጉጉት ይጠብቃሉ፣
- በከፍተኛ የኑሮ ውድነት እና ስራ አጥነት አዙሪት ውስጥ የሚሰቃዩ እልፍ አእላፍ ኢትዮጵያውያን ከአዲሶቹ የፌዴራል እና የክልል መንግስታት ተጨባጭ የመፍትሄ እርምጃዎችን በታላቅ ተስፋ ይጠብቃሉ፣
- መላው የሀገራችን ህዝቦች በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተቀሰቀሰውና የበርካቶችን ህይወት ቀጥፎ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎቻችንን ያፈናቀለው ጦርነት እልባት አግኝቶ በሀገራችን ሰላም እና መረጋጋት ይሰፍን ዘንድ በተስፋ ይጠብቃሉ፣
- በትግራይ፣ በአማራ፣ በአፋር እንዲሁም በሌሎች የሀገራችን ክፍሎች በግጭት እና በጦርነቱ ምክንያት ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ ዜጎች በሀገራችን ሰላም እና መረጋጋት ሰፍኖ፣ ወደቄያቸው ተመልሰው የሰላም አየር የሚተነፍሱበትን ሰዓት በጉጉት በመጠበቅ ላይ ይገኛሉ፡፡እነዚህ እና ሌሎች በርካታ የሀገራችን ዘመን ተሻጋሪ እና ውስብስብ ችግሮች የአዲሱን መንግስት አፋጣኝ ውሳኔ ይሻሉ፡፡

ጠ/ሚንስትር ዶ/ር አብይ አህመድ እና መንግስታቸው የሀገራችንን እና የህዝባችንን ድርብርብ ችግሮች ለመቅረፍ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ መልካም የስራ ጊዜ እንዲሆንላቸው እንመኛለን፡፡ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በሰለጠነ የፖለቲካ ባህል ከገዢው ፓርቲ ጋር እየተፎካከረ እና በሀገራዊ ጉዳዮች እየተባባረ ለሀገራችን ሰላም እና እድገት የድርሻውን ለመወጣት ዝግጁ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ ይገልጻል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**መስከረም 24፣ 2014**
**አዲስ አበባ**

# በጦርነት የተፈናቀሉ ወገኖች አፋጣኝ ትኩረት ይሻሉ!!

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ባለው ግጭት በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖቻችን ከቤት ንብረታቸው መፈናቀላቸው ይታወሳል። በግጭቱ ከተጎዱ አካባቢዎች መካከል በአማራ ክልል የሰሜን ወሎ እና የዋግ ህምራ ዞኖች ይገኙበታል። ከእነዚህ አካባቢዎች የተፈናቀሉ ከፍተኛ ቁጥር ያለቸው ወገኖች በተለያዩ ከተሞች ውስጥ በአስቸጋሪ ሁኔታ በመጠለያ ካምፖች እና ትምህርት ቤቶች ውስጥ ይገኛል። ከሰሜን ወሎ እና ዋግ ህምራ ዞኖች የተፈናቀሉ ሴቶች፣ ህጻናት፣ አረጋውያን፣ እንዲሁም በመጠለያ ጣቢያዎቹ የወለዱ አራስ እናቶች በደሴ ከተማ እና በሌሎች አካባቢዎች ይገኛሉ።

እጅግ አስከፊ በሆነ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙት የግጭት ሰለባዎች ባጋጠማቸው ከፍተኛ የምግብ፣ የውሀ፣ የህክምና አገልግሎት፣ የመድሀኒት፣ የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች እጥረት ምክንያት ለከፋ አደጋ ተጋልጠዋል። በጦርነቱ ምክንያት በርካታ ትምህርት ቤቶች እና የጤና ተቋማት ወድመዋል። ችግሩን ለመቅረፍ የተለያየ አካላት ጥረት በማድረግ ላይ የሚገኙ ቢሆንም ከችግሩ ስፋት አንጻር እጅግ አናሳ ነው።

በመሆኑም በከፍተኛ አደጋ ውስጥ የሚገኙ ወገኖቻችንን ለመደገፍ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ የምትገኙ ኢትዮጵያውያን አቅማችሁ የፈቀደውን ማንኛውም አይነት ድጋፍ እንድታደርጉ ነኢፓ ጥሪውን ያስተላልፋል። የፓርቲያችን አባላት እና አመራሮች በወገኖቻችን ላይ የደረሰውን ስቃይ እና ጉዳት ለመቀነስ በየአካባቢያችሁ የመሪነት ሚና በመጫወት እና ህዝብን በማስተባበር ለወገኖቻችን ለመድረስ የድርሻችሁን እንድትወጡ እንጠይቃለን።

የፌዴራል እና የክልል መንግስታት የተፈናቀሉ ወገኖችን ለመርዳት ጥረት በማድረግ ላይ ያሉ መሆኑ ቢታወቅም በቂ እንዳልሆነ ተፈናቃይ ወገኖቻችን እና ማህበረሰቡ በመግለጽ ላይ ይገኛል። በመሆኑም የክልል መንግስታት፣ የሚመለከታቸው የፌዴራል መንግስት ተቋማት፣ ሀገር በቀል እና አለማቀፍ የእርዳታ ድርጅቶች ፈጣን እና የተቀናጀ ድጋፍ ያደርጉ ዘንድ ነኢፓ ጥሪውን ያቀርባል።

በጥቅምት ወር መጀመሪያ በሀገር ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንደሚከፈቱ የሚጠበቅ ሲሆን ከመኖሪያ አካባቢያቸው ተፈናቅለው በመጠለያዎች ውስጥ የሚገኙ ህጻናት በሚገኙባቸው አካባቢዎች ትምህርታቸውን መቀጠል የሚችሉበት ሁኔታ ከወዲሁ ሊታሰብበት ይገባል።

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**መስከረም 10፣ 2014**
**አዲስ አበባ**

# መልካም አዲስ አመት

## በአዲሱ ዓመት የሀገርን ህልውና ለማስጠበቅ የሰላም አማራጮችን ታሳቢ ያደረገ የተቀናጀ የጸጥታ፣ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ስራ መስራት ያስፈልጋል!!

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** (**ነእፓ**) አዲሱ ዓመት የሰላም፣ የጤና እና የደስታ እንዲሆን እየተመኘ ዘመኑ ሀገራችን ቀስፈው ከያዟት ግጭት፣ ጦርነት፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች የምትላቀቅበት፣ ኢትዮጵያውያን በሰላም፣ በጤና፣ በወንድማማችነትና በፍቅር የሚኖሩበት እንዲሆን ይመኛል። **ነእፓ** አዲሱ ዓመት ሀገራችን ከውስጥ እና ከውጭ የገጠሟት የህልውና አደጋዎች ተወግደው፣ በሁሉም የሀገራችን ክፍል ሰላምና መረጋጋት የሚሰፍንበት፣ ከቀያቸው የተፈናቀሉ ዜጎች ወደ ጎጇቸው የሚመለሱበት፣ የዜጎቻችንን ህይወት እጅግ መራር ያደረገው የኑሮ ሸክም ቀንሶ መላው የሀገራችን ህዝቦች በሰላም እና በደስታ የሚኖሩበት እንዲሆን ይመኛል።

የከረምቱ ጭጋግ እና ጨለማ ተገልጦ የኢትዮጵያ ምድር በአደይ አበባ ሲፈካ ጦርነት፣ ሞት እና ግጭት ከኢትዮጵያ ሰማይ ላይ ተገፈው በልቦቻችን ፍቅር፣ ደስታ እና ተስፋ እንዲሞላ፣ በአዲሱ ዓመት ህዝባችን የጦርነት እና የሞት ዜና ከመስማት ተላቆ የሰላም እና የአብሮነት መዝሙር የሚያዳምጥበት እንዲሆን **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** አጥብቆ ይመኛል።

**የተወደዳችሁ የሀገራችን ህዝቦች፣**

ሀገራችን ኢትዮጵያ በተገባደደው ዓመት እጅግ ውስብስብ ማህበረ-ኢኮኖሚና የፖለቲካ ተግዳሮቶች አጋጥመዋታል። ከገጠሟት ችግሮች አንዱ እና ዋነኛው በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተፈጠረው ግጭት ነው። ከአስር ወራት በላይ ያስቆጠረው ግጭት ከቀን ወደ ቀን እየተባባሰ ችግሩ ከትግራይ ክልል ወጥቶ የአጎራባች ክልሎችን ሰለባ አድርጓል። በግጭቱ ምክንያት ኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙና ውስብስብ የደህንነት፣ የማህበራዊ፤ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ እንዲሁም ዲፕሎማሲያዊ ፈተናዎች ውስጥ ገብታለች።

በጦርነቱ ምክንያት በሺዎች የሚቆጠር ህይወት ጠፍቷል፣ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ከመኖሪያ ቀያቸው ተፈናቅለው ለስደት ተዳርገዋል። ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የገጠር እና ከተማ ነዋሪዎች እድሜ ልካቸውን ያፈሩት ሀብት እና ንብረት ወድሟል። በግጭቱ ምክንያት ህጻናት፣ አረጋውያን እና ሴቶች ለከፋ ሰብዓዊ ቀውስ እና ማህበራዊ ኑሮ መናጋት ተጋልጠዋል። ለሀገራችን ዳር ድንበር መከበር እና ለዜጎች ሰላም መጠበቅ ቃል የገቡ የሀገር መከላከያ ሰራዊት አባላት እና ሌሎች የጸጥታ ኃይሎች ደማቸውን አፍስሰዋል፣ ውድ ህይወታቸውን ገብረዋል። ጦርነቱ በመላው የሀገራችን ህዝቦች ላይ ከፍተኛ የስነ ልቦና ጫና ፈጥሯል።

ምንም እንኳን ጦርነት የሚካሄድባቸው አካባቢዎች በግጭቱ ይበልጥ የተጎዱ ቢሆንም የጦርነቱ ወላፈን በመላ ሀገሪቱ ተዳርሷል። ጦርነቱ የፈጠረው ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪ ተጽዕኖ በሁሉም የሀገራችን ክፍል እና ህዝብ ላይ አርፏል። ጦርነት በሚካሄድበት ወቅት እና አካባቢ ግብርናም ሆነ ሌሎች ማናቸውም እንቅስቃሴ ማድረግ ስለማይቻል ሰፊ የሃገራችን መሬት ጦም እንዲያድር ግድ ሆኗል፡ ፡ በዚህም ምክንያት የቀጣዩ ዓመት የሀገራችን የምግብ ዋስትና ጥያቄ ውስጥ ገብቷል። ጦርነቱ ወትሮም በከፍተኛ ችግር ውስጥ በሚገኘው ኢኮኖሚያችን ላይ ድርብርብ ጫና ፈጥሯል። ከፍተኛ የኑሮ ውድነት እና ስራ አጥነት፣ እጅግ የተቆለለ የውጭ እዳ እና

የውጭ ምንዛሬ እጥረት፣ ከፍተኛ የዋጋ ንረት እና የምርት እጥረት የተጫነው የሀገራችን ኢኮኖሚ በጦርነቱ ምክንያት ይበልጥ ተጎድቷል። በሀገራችን በመካሄድ ላይ ባለው ግጭት ሳቢያ የትምህርት እና የጤና ተቋማትን ጨምሮ አያሌ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መሰረተ ልማት ወድሟል።

ምንም እንኳን በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ያለው ግጭት ባስከተለው ከፍተኛ ጉዳት ትኩረት ያገኘ ቢሆንም ሌሎች የሀገራችን አካባቢዎችም ከግጭት እና ከሰላም እጦት ነጻ አይደሉም። በምስራቁ የሀገራችን ክፍል በአፋር እና በሶማሌ ወንድማማች ህዝቦች መካከል ያለው ግጭት የበርካታ ንጹሃን ዜጎቻችንን ህይወት እየቀጠፈ ይገኛል። በቤኒሻንጉል እና በኦሮሚያ ክልሎች ማንነትን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶች የበርካታ ንጹሃን ህይወት እንደ ዘበት እየተቀጠፈ የሚገኝ ሲሆን፣ ከፍተኛ የአካል ጉዳት እና የንብረት መውደም አደጋም ደርሷል።

የፌዴራል እና የክልል መንግስታት የጸጥታ እና የደህንነት ተቋማት ሙሉ ኃይላቸውን እና ትኩረታቸውን በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ባደረጉበት ባለፉት ጥቂት ወራት፣ በሌሎች አካባቢዎች የተፈጠረው የጸጥታ መዋቀር መሳሳት በተለያየ አካባቢ ለሚንቀሳቀሱ የታጠቁ ቡድኖች መልካም አጋጣሚን የፈጠረ ሲሆን፣ የሰላማዊ ዜጎች ህይወት እና ንብረት ይበልጥ ለጥቃት ተጋላጭ ሆነዋል።

**የተከበራችሁ ኢትዮጵያውያን**

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተቀሰቀሰው ግጭት ተጽዕኖ በሀገር ውስጥ ብቻ የተወሰነ አይደለም። ሀገራችን ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብቷን ተጠቅማ ካለችበት አስከፊ ድህነት እንዳትላቀቅ የሚመኙ የውጭ ኃይላት በአባይ ወንዝ ላይ የጀመርነው የህዳሴ ግድብ እንዲስተጓጎል ሲያደርጉት የነበረውን ጫና በጦርነቱ ምክንያት አጠናክረው ቀጥለውበታል። ኢትዮጵያ የግድቡን የውሃ ሙሊት ከአንድም ሁለቴ በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቋ ያላስደሰታቸው የውጭ ኃይላት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ያለውን የእርስ በርስ ግጭት እንደ መልካም አጋጣሚ እየተጠቀሙበት ይገኛሉ። ጦርነቱን ተገን በማድረግ ወትሮም የሀገራችንን ሰላም እና መረጋጋት የማይሹ አንዳንድ የውጭ ኃይላት የኢትዮጵያን የውጭ ገጽታ ለማበላሸት ሰርተዋል፣ ዓለም ዓቀፍ የሚዲያ ተቋማት የሀገራችንን ገጽታ ለማጠልሸት ጥረዋል፣ ግጭቱን ምክንያት በማድረግ ፍላጎታቸውን ለመጫን የሚሹ አካላት ከፍተኛ የኢኮኖሚ እና የዲፕሎማሲ ጫና በሀገራችን ላይ ለማሳረፍ ከፍተኛ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

ሀገራችን በውስጣዊ ጉዳይ እና በግጭት ከመቼውም ጊዜ በላይ የተጠመደችበትን ይህንን ወቅት እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ጎረቤት ሀገር ሱዳን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን በመተላለፍ ድንበራችንን ጥሳ የፈጸመችው የግዛት ማስፋፋት በአካባቢው ውጥረት እንዲነግስ አድርጓል። በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተቀሰቀሰው ግጭት ሀገራችንን በሁሉም መልኩ ተጋላጭ አድርጓታል።

**ውድ የሀገራችን ህዝቦች፣**

ባለፉት ዘመናት በሀገራችን በርካታ ጦርነቶች ተካሂደዋል። ኢትዮጵያውያን ሀገራችንን ለመውረር ከመጡ የሩቅ ተስፋፊዎች እንዲሁም የድንበር ይገባኛል ጥያቄ አንስተው ወረራ ከፈጸሙ የጎረቤት ሀገራት ጋር በርካታ ጦርነት ገጥመናል። ከዚህ በተጨማሪ ሰብዓዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ደፍጥጠው ሀገር ለመግዛት የሞከሩ አምባገነን የውስጥ መንግስታትን አገዛዝ በመቃወም እልህ አስጨራሽ ጦርነቶች ተካሂደዋል።

አምባገነኑን የደርግ ስርዓት ከስልጣን ለማውረድ ለ17 ዓመታት አውዳሚ የእርስ በርስ ጦርነት የተካሄደ ሲሆን፣ ደርግን ተክቶ መንበረ ስልጣኑን የተቆጣጠረውን ኢህአዴግ መራሹን ስርዓት በመቃወም መላው የሀገራችን ህዝቦች ከፍተኛ የህይወት መስዋእትነት

ከፍለዋል፡፡ በየትኛውም ዘመን የተካሄዱ የእርስ በርስ ጦርነቶች ሀገራችንን ከፍተኛ ሰብዓዊ እና ቁሳዊ ዋጋ አስከፍሏታል፡፡ የጦርነትን አስከፊነት በተግባር የሚረዱ ኢትዮጵያውያን ጦርነትን የመጀመሪያው የችግር መፍቻ መንገድ አድርገው ባይቆጥሩም፣ ጉዳዩ የሀገር ህልውና እና የዜጎች ክብር ሲሆን ሰላምን ለማረጋገጥ ሳያመነቱ ታግለዋል፡፡

**የተከበራችሁ ኢትዮጵያውያን**

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተፈጠረውን ግጭት ገና ከጅምሩ በከፍተኛ ትኩረት እና ስጋት በቅርበት ሲከታተል ቆይቷል፡፡ **ነኢፓ** የሀገራችንን ህልውና በጽኑ እየተፈታተነ፣ የዜጎችን ህይወት እየቀጠፈ፣ ማህበራዊ መስተጋብራችንን እየበጣጠሰ፣ ሀገራችንን ለከፋ የውጭ ጫና እያጋለጠ ያለው ግጭት የሀገራችንን ጥቅም እና ክብር እንዲሁም የዜጎችን ሰላም እና ደህንነት በሚያስጠብቅ መልኩ እልባት እንዲያገኝ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

ግጭቱ ከተቀሰቀሰበት ጊዜ ጀምሮ በግጭቱ አካባቢ የሚገኙ የነኢፓ አመራር፣ አባላት እና ደጋፊዎች በግጭቱ የተጎዱ እና ከቄያቸው የተፈናቀሉ ዜጎችን ለመደገፍ ከፍተኛ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ነኢፓ ይህንን ጥረቱን በመቀጠል በግጭቱ ምክንያት ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ ዜጎችን አቅም በፈቀደ መጠን ለመደገፍ ሰፊ ዝግጅት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ነኢፓ ግጭቱ የሀገራችንን ሰላም፣ አንድነት እና ሉአላዊነት እንዲሁም የህዝቦችን ወንድማማችነት በሚያጠናክር እንዲሁም ዘላቂ እና አስተማማኝ በሆነ መንገድ እንዲፈታ ባለፉት ጊዜያት በርካታ ሙከራዎችን አድርጓል፡፡ ነኢፓ ከውስጥ እና ከውጭ የተጋረጡብንን ጫናዎች ለመከላከል ከሚደረጉ ጥረቶች ጎን፣ ጦርነቱ በአጭር ጊዜ እንዲጠናቀቅ፣ ጦርነቱ በተራዘመ መጠን በሀገራችን ላይ የሚፈጥረውን ሁለንተናዊ ጉዳት ለመቀነስ ብሎም ያንዣበቡብንን የውጭ ኃይሎች ጫና ለመመከት የሚያስችሉ አማራጮችን በተመለከት ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከሲቪክ ማህበራት፣ ከሀገር ሽማግሌዎች፣ ከምሁራን ጋር ሰፊ ውይይት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

**ነኢፓ** ይህንኑ ጥረቱን በቀጣይ አጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን፣ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ያለው ግጭት በአጭር ጊዜ እንዲቋጭ፣ ሀገራችን ካላችበት ሁለንተናዊ የግጭት አዙሪት በአስተማማኝ ሁኔታ እንድትወጣ፣ ዘላቂ ሰላም እና ልማት እውን ሆኖ አብዛኛው የሀገራችን ህዝብ ቀፍድዶ ከያዘው ድህነት እና የኑሮ ውድነት እንዲላቀቅ መንግስት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ማህበራት፣ ምሁራን፣ የሀገር ሽማግሌዎች እና የሀይማኖት አባቶች በተናጠል እና በቅንጅት ሰፊ ስራ መስራት አለባቸው ብሎ ያምናል፡፡ ከዚህ አንጻር፣

1. የፌደራሉ መንግስት ግጭቱን ለማስቆም እና ለችግሩ ሰላማዊ መፍትሄ ለማበጀት የወሰደው የተናጠል የተኩስ አቁም ውሳኔ በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሰፊ ተቀባይነትን ማግኘቱ ይታወሳል፡፡ ይሁን እንጂ ጦርነት በአንድ ወገን ፍላጎት ብቻ ሊቆም ስለማይችል ግጭቱ ከመቆም ይልቅ ይበልጥ ተባብሶ ቀጥሏል፡፡ አስተማማኝ ሰላም ሊያመጣ የሚችል የስምምነት ማእቀፍ ተዘጋጅቶ በሁሉም ወገን ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፣

2. በትግራይ ክልል የተጀመረው ጦርነት በአማራ እና አፋር ክልሎች የተስፋፋ ሲሆን ይህም ግጭቱን ይበልጥ ከማወሳሰቡም በላይ የበርካታ ንጹሀን ዜጎችን ህይወት እንዲቀጠፍ እና በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች እንዲፈናቀሉ አድርጓል፡፡ ምንም እንኳን ህወሓት በአፋር ክልል ያደረገው መስፋፋት በቅርቡ የተቀለበሰ ቢሆንም አሁንም አንዳንድ የአማራ ክልል አካባቢዎችን በኃይል ተቆጣጥሮ ይገኛል፡፡ በዚህም ሰላማዊ ዜጎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል፡፡

3. መላው **የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** አባላት እና በየደረጃው ያሉ አመራሮች በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በመካሄድ ላይ ባለው ግጭት ምክንያት እስከ አሁን ህይወታቸውን ላጡ ዜጎች የተሰማቸውን ከፍተኛ ሀዘን ሲገልጹ መቆየታቸው የሚታወስ ነው፡፡

ማንነትን መሰረት ያደረገ በየትኛውም ወገን፣ በማንኛውም ጊዜ እና ቦታ የሚፈጸምን ጥቃት ነእፓ አጥብቆ ያወግዛል፡፡ ነእፓ በየትኛውም ጊዜ እና ቦታ በንጹሀን ላይ ጉዳት ያደረሰ የትኛውም አካል በህግ ተጠያቂ መሆን እንዳለበት በጽኑ ያምናል፣

4. ምንም እንኳን በጦርነት ወቅት አንዳንድ መብቶችን መገደብ የሚያስገድድ ሁኔታ ሊፈጠር ቢችልም፣ ከግጭቱ ጋር በተያያዘ የዜጎች መሰረታዊ ሰብአዊ መብቶች እንዳይገደቡ ጥንቃቄ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የፌዴራል እና የክልል መንግስታት የሀገርን ሰላም እና የዜጎችን ደህንነት ለማስጠበቅ በሚወስዷቸው ህግ የማስከበር እርምጃዎች በህገ መንግስቱ የተረጋገጡ፣ የዜጎች ሰብአዊ መብቶች እንዳይጨፈለቁ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል፣

5. ህዝብ ከጦርነቱ ጋር በተያያዘ ፈጣን እና አስተማማኝ መረጃ የማግኘት መብት አለው፡፡ የመረጃ ክፍተት ህዝቡን ለውዥምብር የሚዳርግ ሲሆን እኩይ አላማ ያላቸው አካላት ህዝብን በማሳሳት ችግሩ ይበልጥ እንዲወሳሰብ እድል ይሰጣቸዋል፡፡ በመሆኑም መንግስት ወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ የተማከለ፣ ፈጣን፣ ተአማኒነት ያለውና የተሟላ መረጃ ለህዝብ ሊሰጥ ይገባል፣

6. በግጭት ውስጥ ከፍተኛውን ገፈት የሚቀምሱት ሰላማዊ ዜጎች በተለይም ሴቶች፣ አረጋውያ እና ህጻናት ናቸው፡፡ በመሆኑም በየትኛውም ቦታ የሚገኙ ሰላማዊ ዜጎች በግጭቱ እንዳይጎዱ እና አስቸኳይ ሰብአዊ ድጋፎችን እንዲያገኙ ሁሉም አካላት አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርጉ ነእፓ ይጠይቃል፣

7. በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ያለውን ግጭት የብሄር መልክ ለማስያዝ የሚደረጉ ሙከራዎች ለረዥም ዘመናት በጠንካራ ማህበራዊ መስተጋብር ተዋልዶ እና ተሳስረው የኖሩትን ኢትዮጵያውያንን የሚከፋፍል፣ በሀገራችን ማንነትን መሰረት ያደረገ ግጭት እና ደም መፋሰስ ይበልጥ እንዲስፋፋ የሚያደርግ አደገኛ አካሄድ ነው፡፡ በመሆኑም ግጭቱን የብሄር መልክ እንዲይዝ እና ጦርነቱን ህዝባዊ ለማድረግ የሚደረግ ሙከራ ጦርነት ከቆመም በኋላ በህዝቦች መካከል የማይሽር ጠባሳ ትቶ የሚያልፍ በመሆኑ በአስቸኳይ ሊቆም ይገባል፣

8. ጦርነት የፖለቲካ ልዩነቶችን መፍቻ የመጨረሻው አማራጭ እንጂ ተመራጭ መንገድ አይደለም፡፡ **ነእፓ** በመሰረታዊነት ውስጣዊ የፖለቲካ አለመግባባቶችን ለመፍታት ከጦርነት ይልቅ ፖለቲካዊ አማራጮች የተሻለ ውጤታማ ናቸው ብሎ የሚያምን ሲሆን፣ በጦርነትም ውስጥ ተሁኖ የሰላም በሮችን ጨርሶ አለመዝጋት ጠቃሚ እንደሆኑ ይረዳል፡፡ በመሆኑም ሀገራችንን ከፍተኛ ዋጋ እያስከፈለ የሚገኘው ይህ ጦርነት እስከ አሁን ያስከፈለንን ዋጋ እና ወደፊት ሊያስከትል የሚችለውን ሰብአዊ፣ ቁሳዊ እና ማህበራዊ ጉዳት ለማስቀረት አማራጭ የግጭት መፍቻ መንገዶች እንዳይዘጉ ነእፓ ያሳስባል፣

9. ከራሷ አልፋ በሌሎች ሀገራት ሰላምን በማስከበር ታሪክ ያላት ሀገራችን፣ ከውስጥ እና ከውጭ የሚገጥሟትን የሰላም እና የደህንነት ስጋቶች የመመከት አኩሪ ታሪክ አላት፡፡ ዛሬም በሰሜን ኢትዮጵያ የገጠመንን አደጋ ለመመከት የኢትዮጵያ የመከላከያ እና የደህንነት ተቋማት በቂ ናቸው ብለን እናምናለን፡፡ በመሆኑም የገጠመንን አሁናዊ ችግር ለመፍታት የሀገራችንን ዘላቂ የደህንነት መዋቅር እና መረጃ ለባዕድ አጋልጦ ሊሰጥ በሚችል መልኩ ድንበራችንን ለውጭ ኃይላት ክፍት ማድረግ ከፍተኛ አደጋ አለው፡፡ ይህንን ታሳቢ በማድረግ በኢትዮጵያ ድንበር ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም የውጭ ኃይል እንቅስቃሴን መንግስት በጥንቃቄ ሊያይ ይገባል፣

10. በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተቀሰቀሰው ግጭት ቁጥራቸው እጅግ ከፈተኛ የሆኑ ዜጎችን ከቄያቸው ማፈናቀሉ የሚታወቅ ሲሆን እነዚሕ ዜጎቻችን በከፍተኛ ችግር ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ለእነዚሕ ወገኖቻችን የእለት ደራሽ ድጋፍ ማድረግ እና በዘለቄታው ማቋቋም የሁለም ዜጋ ኃላፊነት ነው፡፡ በግጭቱ ውድ ህይወታቸውን ያጡ የመከላከያ ኃይል ቤተሰቦች፣ ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናት እና

ጧሪ ያጡ አረጋውያን አስቸኳይ ድጋፍ ይሻሉ፡፡ በተለይም አሁን ያለንበት የክረምት ወቅት የተፈናቃይ ወገኖቻችንን ስቃይ እና መከራ ይበልጥ የከፋ አድርጎታል፡፡ በመሆኑም ለወገን ደራሽ ወገን በመሆኑ መላው የሀገራችን ህዝቦች እና ሰብአዊ ድርጅቶች በጦርነቱ ለተጎዱ ወገኖቻችን አቅም በፈቀደ መጠን ድጋፍ እንዲያደርጉ ነእፓ ጥሪውን ያቀርባል፣

11. ጦርነቱ በትግራይ ክልል ከፍተኛ ሰብአዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ቀውስ አስከትሏል፡፡ በመሆኑም በጦርነቱ የተጎዱ ዜጎችን ለመታደግ መንግስት እና ዓለማቀፍ ተቋማት የጀመሩትን ድጋፍ በተቀናጀ መልኩ አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጥሪ እናቀርባለን፣

12. ምንም እንኳን በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ያለው ግልጽ እና ሰፊ ጦርነት የተለየ ትኩረት ያገኘ ቢሆንም፣ በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ውጥረቶች እና አልፎ አልፎም ግጭቶች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ በእነዚህ ግጭቶች ምክንያት በሰላማዊ ዜጎች ላይ ማንነትን መሰረት ያደረገ ግድያ፣ መፈናቀል እና የንብረት ውድመት እየደረሰባቸው ይገኛል፡፡ በመሆኑም መንግስት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተፈጠረውን ችግር እልባት ለመስጠት ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ጎን ለጎን በሌሎች የሀገራችን ክፍሎች የሚገኙ ዜጎችን ሰላም እና ደህንነት ለመጠበቅ በቂ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፣

13. በምስራቁ የሀገራችን ክፍል በአፋር እና ሶማሊ ወንድማማች ህዝቦች መካከል የቆየው ግጭት በተለይ ባለፉት ሶስት ዓመታት ይበልጥ ተባብሶ ቀጥሏል፡፡ የአፋር እና የሶማሊ ህዝቦች በባህል እና በእምነት እንዲሁም በአርብቶ አደር የኑሮ ዘይቤ ተመሳሳይ ናቸው፡፡ በሁለቱ ብሄረሰቦች መካከል ያለው ግጭት ረዥም ጊዜ ያስቆጠረ ቢሆንም በቂ የመንግስት ትኩረት ሳይሰጠው ዛሬ ላይ ደርሷል፡፡ በከፍተኛ የድህነት አዙሪት ውስጥ የሚኖሩት የአፋር እና የሶማሊ አርብቶ አደር ህዝቦች የሀገራችን ሰላም እና ብልጽግና ዋልታና ማገር እንደሆኑ ቢታወቅም፣ እንደ ዜጋ በቂ ትኩረት ተሰጥቷቸው አያውቅም፡፡ ይህ አደጋዊ የመንግስት አሰራር ሊቀየር ይገባዋል፡፡ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በአፋር እና ሱማሌ ህዝቦች መካከል ለዘመናት የቆየውን ችግር በአስተማማኝ ለመቅረፍ አዲስ የሰላም ፓኬጅ ለማዘጋጀት ጥረት ሲያደርግ የቆየ ሲሆን ይህንኑ የሰላም ፓኬጅ በአዲሱ ዓመት ተግባራዊ ለማድረግ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል፡፡

14. የአፍሪካን ችግር በአፍሪካውያን መፍታት የሚለውን መርህ በመከተል እና ይህ እሳቤ በተለይ በህዳሴ ግድብ ዙሪያ ከታችኛው ተፋሰስ ሀገራት ጋር የገጠመንን ጫና ለመፍታት ያስገኘውን ተጨባጭ ፋይዳ በማስታወስ፣ አፍሪካዊ ተቋማት፣ አፍሪካ ህብረት፣ ኢጋድ እና ሌሎች የኢትዮጵያ ወዳጅ የአፍሪካ መንግስታት በሀገራችን ያለው ግጭት የኢትዮጵያን እና የዜጎቿን ጥቅም እና ክብር ባስጠበቀ መልኩ ይፈታ ዘንድ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጎን እንዲቆሙ ነእፓ ጥሪውን ያቀርባል፣

15. የሀገራችን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በአብዛኛው ከኃያላን የምዕራብ ሀገራት ጋር የተቆራኘ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ይህ ወደ አንድ ያጋደለ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በጥቂት ሀገራት ላይ ጥገኛ እንድንሆን ከማድረግ አልፎ ከሀገራቱ ጋር ያለን ግንኙነት በሻከረ ወቅት ለከፍተኛ ፖለቲካዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ ችግር ዳርጎናል፡፡ ሀገራችን ያለችበት አሁናዊ ሁኔታ ይህ ሀቅ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አድርጓል፡፡ የሀገራችን የውጭ ግንኙነት ሚዛኑን የጠበቀ ይሆን ዘንድ ከምዕራቡ ዓለም ጋር ካለን ግንኙነት ትይዩ ከምስራቁ ኃያላን ሀገራት ጋር ያለንን ግንኙነት ማጠናከር እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር መንግስት በቅርቡ ከተለያዩ ሀገራት ጋር የዲፕሎማሲ፣ የኢኮኖሚና ወታደራዊ ግንኙነቱን ለማጠናከር ያደረገው እንቅስቃሴ የሚደገፍ ነው፣

16. በሀገራችን አዲስ አመት ሲገባ ለፖለቲካ እስረኞች ምህረት ማድረግ ነባር የፖለቲካ ባህል ነው፡፡ ለፖለቲካ እስረኞች የሚደረግ ምህረት የሀገራችንን የፖለቲካ ትኩሳት እና ውጥረት ለመቀነስ አወንታዊ ሚና አለው፡፡ በዚህ መሰረት የክልል እና የፌዴራል

መንግስታት ለፖለቲካ እስረኞች ምህረት በማድረግ በሀገራችን ሰላማዊ የፖለቲካ ምህዳር ለመፈጠር ብሎም በአዲሱ አመት የተሻለ የሰላም ድባብ እንዲፈጠር ለማድረግ እንዲሰሩ ነእፓ ጥሪውን ያቀርባል፣

17. የሀገራችንን ችግሮች በዘለቄታው ለመፍታት ብሄራዊ ውይይት ማድረግ ምትክ የሌለው የፖለቲካ መሳሪያ ነው፡፡ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ባለፉት ሁለት ዓመታት የብሄራዊ መግባባት አጀንዳን በእጅጉ በማቀንቀን ከፍተኛ እንቅስቃሴ ሲያደርግ መቆየቱ የሚታወስ ሲሆን፣ ይህንን እንቅስቃሴ ከምርጫ በኋላም አጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጿል፡፡ ውጤታማ የብሄራዊ ውይይት እና መግባባት ለመፍጠር ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያስፈልግ ሲሆን ሂደቱ ግልጽ እና አሳታፊ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በአዲሱ አመት ነእፓ ቀደም ሲል የጀመረውን የብሄራዊ ውይይት እንቅስቃሴ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመሆን አጠናክሮ ይቀጥላል፣

18. ወትሮም በከፍተኛ የማክሮ/ማይክሮ ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ውስጥ ያለው የሀገራችን ምጣኔ ሀብት በግጭት እና ሰላም ማጣት ተባብሷል፡፡ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ችግሩን ለመቅረፍ እና የዋጋ ግሽበቱን ለመቆጣጠር መንግስት ስር ነቀል የመዋቅር ማሻሻያዎች ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ኢኮኖሚውን ለማረጋጋትት የሚወሰዱ እርምጃዎች ችግሩን ይበልጥ እንዳያባብሱ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል፡፡ በበቂ ጥናት እና መረጃ ላይ ያልተደገፈ ግብታዊ እርምጃ ኢኮኖሚውን ይበልጥ ከማናጋት ባሻገር ሀገርን በሀቀኝነት የሚያገለግሉ ነጋዴዎችን ይጎዳል፡፡ የመንግስትን የፖሊሲ እና የአሰራር ግድፈቶች ሁሌም “በአሻጥረኛ ነጋዴዎች” ለመሸፋፈን መሞከር የሀገራችንን ኢኮኖሚ መሰረታዊ ችግሮች አይፈታም፣ ዜጎችን ጀርባቸውን ካጎበጠው የኑሮ ውድነት አይታደግም፣

19. በህገ መንግስቱ መሰረት በመስከረም ወር መጨረሻ በሀገራችን አዲስ መንግስት እንደሚቋቋም ይጠበቃል፡፡ የሚቋቋመው መንግስት በርካታ ታሪካዊ ሀላፊነቶች ያሉበት ሲሆን ከእነዚህ መካከል ዋነኛው የሀገር ሰላም እና ደህንነት ይገኝበታል፡፡ አዲሱ መንግስት የሀገራችንን  ውስብስብ ችግሮች ለመፍታት በቀጣይ አምስት አመታት በሁሉም መስክ ከፍተኛ የማሻሻያ ስራዎች ሊሰራ ይገባል፡፡ አዲሱ መንግስት ካለፉ መንግስታት ስህተት በመማር ሀገራችን ከገባችበት የቀውስ አዙሪት በአጭር ጊዜ እንድትወጣ የሚያስችሏትን ፖሊሲዎች እና ፕሮግራሞች ከተፎካካሪ ፓርቲዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት በመወያየት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ሀገራችንን አስረው የያዟት ችግሮች ከአንድ ፓርቲ አቅም በላይ በመሆናቸው አዲሱ መንግስት ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር በእውነተኛ ሀገራዊ የትብብር መንፈስ ሊሰራ ይገባል፣

**በመጨረሻም፣**

አዲሱ አመት ሀገራችን አሁን ካለችበት ድርብርብ የሰላም መደፍረስ፣ የግጭት፣ ከፍተኛ የኑሮ ውድነት እና ሌሎች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ቀውሶች ተላቃ የሰላም፣ የአንድነት፣ የወንድማማችነት፣ የእድገት እና የተስፋ ዘመን ይሆን ዘንድ እየተመኘ፣ ይህንኑ ለማሳካት መንግስት እና መላው የሀገራችን ህዝቦች የበኩላቸውን ይወጡ ዘንድ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ጳጉሜ 5 2013**
**አዲስ አበባ**

# ነእፓ ብሄራዊ የምርጫ አስተባባሪ ኮሚቴ መግለጫ

## "የነእፓ የመጀመሪያው ምዕራፍ ስትራቴጂክ ግቦች በስኬት ተጠናቀዋል!!"

**የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ብሄራዊ ምርጫ አስተባባሪ ኮሚቴ በዛሬው እለት ስብሰባ ያካሄደ ሲሆን የ6ኛው ሀገራዊ ምርጫ ሂደት እና የመጀመሪያ ደረጃ ውጤትን አስመልክቶ ግምገማ አካሂዷል፡፡ ኮሚቴው ከምርጫው ጋር በተያያዘ የነበሩ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖችን በስፋት ተመልክቶ ውሳኔዎችን አስልፏል፡፡ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ካስቀመጠቸው ስትራቴጂክ ግቦች መካከል የመጀመሪያውን ምዕራፍ በስኬት ማጠናቀቁ ድርጅታዊ ብቻ ሳይሆን ሀገራዊ ስኬት መሆኑን የገለጸው ብሄራዊ ኮሚቴው ነእፓ በሀገራችን ፖለቲካ አዲስ አስተሳሰብ እና አደረጃጀት እንዲፈጠር፣ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በሀገሩ ጉዳይ እንዲሳተፍ፣ ከኢትዮጵያ ፖለቲካ ተገፍተው የቆዩ ዜጎች በስፋት እና በንቃት እንዲሳተፉ፣ የሀገራችን ፖለቲካ ከስሜት ይልቅ በምክንያት ላይ የተመረኮዘ እንዲሆን እጅግ በጣም አጭር ጊዜ እና በአስቸጋሪ የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ ውጤታማ ስራ ማከናወኑን አመልክቷል፡፡

ነእፓ በርዕዮተ ዓለም፣ በፖሊሲ እና ፕሮግራም የሚከተለው ሚዛናዊነት የሀገራችን ፖለቲካ በወሳኝ መልኩ እንዲለወጥ ትልቅ አስተዋጾ ማድረጉ ተወስቷል፡፡ እስከ አሁን ባለው የምርጫ ውጤት ምንም እንኳን ነእፓ ለህዝብ ተወካዮች እና ለክልል ምክር ቤቶች ያቀረባቸው እጩዎች ውጤት በአንጻራዊነት አነስተኛ ቢሆንም በሁሉም የምርጫ ክልሎች ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ ነእፓን መምረጡ ፓርቲው በቀጣይ በምርጫ ተወዳድሮ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ተጨባጭ ልምድ እና ተሞክሮ ያገኘበት ምርጫ እንደነበር ተመልክቷል፡፡ ምንም እንኳን 6ኛው ጠቅላላ ምርጫ ካለፉት ምርጫዎች አንጻር የተሻሉ በጎ ጎኖች የነበሩት ቢሆንም በአንዳንድ አካባቢዎች በርከት ያሉ ግድፈቶች የተስተዋሉበት እንደነበር ተመልክቷል፡፡

ብሄራዊ ኮሚቴው ነእፓ ዛሬ ላይ ለደረሰበት የስኬት ማማ፣ በተለይ በ6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ ጠንካራ ተፎካካሪ መሆን እንዲችል ጊዜ፣ ጉልበት እና ገንዘባቸውን ለፓርቲው ሳይሰስቱ ላበረከቱ በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን የፓርቲው አባላት እና ደጋፊዎች ልባዊ ምስጋና አቅርቧል፡፡

ነእፓ በሚቀጥሉት ቀናት ምርጫውን አስመልክቶ መግለጫ የሚሰጥ ሲሆን፣ ምርጫ 2013ን አስመልክቶ ዝርዝር ሪፖርት የሚያዘጋጅ አጥኚ ቡድን በማቋቋም የብሄራዊ ኮሚቴው ስብሰባ ተጠናቋል፡፡ ስበሰባው የነእፓ የአዲስ አበባ እጩዎች ባዘጋጁት የእንኳን ደስ አለን ዝግጅት በድምቀት ተካሂዷል፡፡

"እኩልነት በተግባር"

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ሰኔ 17፣ 2013**
**አዲስ አበባ**

# ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በኢትዮጵያ የእንግሊዝ ኤምባሲን ጎበኘ፡፡

የነእፓ ሊቀመንበር ዶ/ር አብዱልቃድር አደም እና የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት በአዲስ አበባ የእንግሊዝ ኤምባሲን በመጎብኘት በፓርቲው አጠቃላይ እንቅስቃሴ እና በ6ኛው ሀገራዊ ምርጫ ዙሪያ ውይይት አድርገዋል፡፡ የፓርቲው ኃላፊዎች በኤምባሲው የፖለቲካ ቡድን ውስጥ የsoft power ኦፊሰር ከሆኑት ሚስተር ሮበርት ኪ (Mr. Robert key) ጋር ባደረጉት ውይይት የነእፓን ርዕዮተ ዓለም፣ የፖለቲካ ፕሮግራም፣ የፓርቲውን እሴቶች፣ የትግል ስልቶች እንዲሁም ፓርቲው ከተመሰረተ ጀምሮ ያከናወናቸውን ዋና ዋና ስራዎች እና ያስመዘገባቸውን ስኬቶች በዝርዝር ያብራሩ ሲሆን፣ ነእፓ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ አዲስ የፖለቲካ አስተሳሰብ እና ባህል እንዲፈጠር አወንታዊ  ተጽኖ በማድረግ ላይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ዶ/ር አብዱልቃድር ኢትዮጵያ ካለችበት የቀውስ አዙሪት እንድትላቀቅ ብቸኛው አማራጭ **"ሚዛናዊ ፖለቲካ"** መሆኑን ገልጸው፣ እንደ ሀገር የተደቀኑብንን መሰናክሎች ለመሻገር በ**"አብሮ ማሸነፍ"** መርህ በተለይ በፖለቲካ ኃይሎች መካከል በትብብር እና በምክክር መስራት እንደሚያስፈልግ አመልክተዋል፡፡ 6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫን አስመልክቶ የምርጫው ሂደት ነጻ፣ ፍትሀዊ እና ሰላማዊ እንዲሆን፣ ዜጎች የሚፈልጉትን የፖለቲካ ፓርቲ በነጻነት መምረጥ እንዲችሉ እና ውጤቱም ተቀባይነት ያለው እንዲሆን ነእፓ የድርሻውን ለመወጣት እየሰራ መሆኑ ተመልክቷል፡፡

ነእፓ በምርጫ ሂደቱ በእጩዎች ምዝገባ፣ በመራጮች ምዝገባ እንዲሁም በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት በርካታ ችግሮች ያጋጠሙት መሆኑን እና ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ከብሄራዊ ምርጫ ቦርድ፣ ከኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት እንዲሁም ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በጋራ እየሰራ መሆኑ ተገልጿል፡፡ የውጭ መንግስታትን አስመልክቶ በኢትዮጵያ ሰላም እና ልማት እንዲሁም ለ6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ ስኬታማነት ዓለማቀፉ ማህበረሰብ አወንታዊ ሚና ሊጫወት እንደሚገባ የፓርቲው አመራሮች ገልጸዋል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ከዚህ ቀደም ከተለያዩ ሀገራት ኤምባሲዎች ጋር ውይይቶችን ማድረጉ የሚታወስ ሲሆን፣ ነእፓ በሚያደርጋቸው የውጭ ግንኙነቶች አለም አቀፉ ማህበረሰብ ኢትዮጵያን አስመልክቶ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረው፣ ኢትዮጵያ ከሀገራቱ ጋር ያላት ግንኙነት እንዲጠናከር፣ በሀገራችን  ላይ የሚደረጉ ጫናዎች እንዲቀንሱ ጥረት ያደርጋል፡፡

በኤምባሲው ግብዣ የተዘጋጀው ውይይት በቀጣይ ሌሎች የውይይት መድረኮችን ለማዘጋጀት በመስማማት ተጠናቋል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ግንቦት 26 2013**
**አዲስ አበባ**

# የነእፓ ከፍተኛ አመራሮች በኢትዮጵያ የጀርመን ኤምባሲን ጎበኙ፡፡

**በነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ሊቀመንበር በዶ/ር አብዱልቃድር አደም የሚመራ ቡድን በኢትዮጵያ የጀርመን አምባሳደር ጋር በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች፣ በ6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ፣ በፓርቲው አጠቃላይ እንቅስቃሴ እና ፖሊሲዎች ዙሪያ ውይይት አድርጓል፡፡ በውይይቱ ላይ ዶ/ር አብዱልቃድር በሀገራችን ከሶስት አመት በፊት ስለተጀመረው "የፖለቲካ ተሀድሶ" ትሩፋቶች እና ተግዳሮቶች ያብራሩ ሲሆን፣ ነእፓ የተጀመረው የለውጥ እንቅስቃሴ እንዲሰምር የበኩሉን አስተዋጾ በማድረግ ላይ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

በሀገራችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ የመጣው ግጭት አሳሳቢ ደረጃ መድረሱን የገለጹት የፓርቲው አመራሮች፣ ከሳምንታት በኃላ ሊካሄድ የታቀደው ሀገራዊ ምርጫ ለግጭቶች መባባስ ምክንያት ሊሆን ይችላል የሚል ከፍተኛ ስጋት እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡ ምርጫ 2013 በለውጡ ማግስት በተሰፋ ሲጠበቅ የነበረ መሆኑን የገለጹት የነእፓ ኃላፊዎች በአሁኑ ወቅት ምርጫው ለዜጎች እና ለፖለቲካ ማህበረሰቡ ከፍተኛ የስጋት ምንጭ መሆኑን አውስተዋል፡፡

ነእፓ በሀገራችን ያሉትን ታሪካዊ እና ወቅታዊ ግጭቶች ለመፍታት ብሄራዊ ውይይት እና እርቅ እንዲካሄድ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ መቆየቱና በተለያዩ ፖለቲካዎ እና የጸጥታ ችግሮች ሀገራዊ ውይይቱ ሳይካሄ ኢትዮጵያ ወደ ምርጫ መግባቷን ተመልክቷል፡፡ በኢትዮጵያ የተጀመረው የዴሞክራሲ ስርአት ጅማሮ ስኬታማነት ለአፍሪካ ቀንድ እና ለመላው አፍሪካ ተምሳሌት ሊሆን እንደሚችል የገለጹት የጀርመን አምባሳደር የተከበሩ ስቲፈን አር (Stephan Auer) ሀገራቸው ለኢትዮጵያ የምታደርገውን ድጋፎች አጠናክራ እንደምትቀጥል ገልጸዋል፡፡

በኢትዮጵያ የጀርመን ኤምባሲ ግብዣ በተካሄደው በዚሁ ውይይት ላይ የፓርቲው የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ አቶ ሲሳይ ነጋሽ እና የሊቀመንበሩ የማህበራዊ ጉዳዮች አማካሪ ወ/ሮ አዲስ መህመድ የተገኙ ሲሆን ቀጣይ ውይይቶችን ለማድረግ በመስማማት ውይይቱ ተጠናቋል፡፡ በውይይቱ ላይ በኢትዮጵያ የፈረንሳይ ኤምባሲ የፖለቲካ ጉዳዮች ኃላፊ ተገኝተዋል፡፡ ነእፓ በኢትዮጵያ ከሚገኙ የተለያዩ ሀገራት አምባሳደሮች ጋር የሁለትዮሽ ውይይት ሲያደርግ መቆየቱ የሚታወስ ሲሆን ይህንኑ አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

**"ጠንካራ ዲፕሎማሲ፣ ጠንካራ ሀገር"**

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ሚያዝያ 21 2013**
**አዲስ አበባ**

## <u>የነእፓ ሊቀመንበር ከአሜሪካ ኤምባሲ የፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊ ጋር ተወያዩ።።</u>

## ዶ/ር አብዱልቃድር አደም በኢትዮጵያ የአሜሪካ ኤምባሲ የፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊ ጋር በምርጫ እና ወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ተወያዩ።።

የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ሊቀመንበር ዶ/ር አብዱልቃድር አደም በኢትዮጵያ የአሜሪካ ኤምባሲ የፖለቲካ ጉዳይ ዘርፍ ኃላፊ ወ/ሮ ኢሎና ኮሌ ጋር በምርጫ እና ወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት አደረጉ።። በኤምባሲው ግብዥያ በተሰናደው ውይይት ላይ የነእፓ ሊቀመንበር የፓርቲውን ወቅታዊ ድርጅታዊ ሁኔታ፣ ርእዮተ ዓለም፣ ማህበራዊ መሰረት፣ ፓርቲው ለምርጫው ያለውን ዝግጁነት፣ ነእፓ ለወቅታዊ ሀገራዊ የፖለቲካ ምህዳር ያለውን እይታ በዝርዝር ያስረዱ ሲሆን፤ ፓርቲው በሚከተለው ሚዛናዊ እና አካታች የፖለቲካ ፕሮግራም/ፍልስፍና በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰፊ የህዝብ ተቀባይነት እንዲያገኝ እንዳስቻለው አብራረተዋል።።

ምርጫው በዜጎች ዘንድ በ"ተስፋ እና ስጋት" ውስጥ የሚጠበቅ መሆኑን የጠቀሱት ዶ/ር አብዱልቃድር ነእፓ ምርጫው ነጻ፣ ፍትሀዊ እና ሰላማዊ እንዲሆን የሚቻለውን ጥረት በማድረግ ላይ መሆኑን አስረድተዋል።። ነእፓ ምርጫው ሰላማዊ እና ውጤቱም ሀገራችንን ወደ ዴሞክራሲ የሚያሻግር ይሆን ዘንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች በተለይም ገዢው ፓርቲ እና መንግስት ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው ብሎ እንደሚያምን ዶ/ር አብዱልቃድር የገለጹ ሲሆን፣ ለምርጫው ስኬታማነት ዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ድጋፍ ሊያደርግ እንደሚገባ ገልጸዋል።።

ነእፓ ለምርጫው ከፍተኛ እጩ ካቀረቡ ፓርቲዎች አንዱ መሆኑን እና በምርጫው ጠንካራ ተፎካካሪ በመሆን ድህረ ምርጫ በሚቋቋመው መንግስት ጉልህ ሚና እንደሚኖረው ሊቀመንበሩ ገልጸው፣ ነእፓ የሚሳተፈበት ድህረ-ምርጫ የኢትዮጵያ መንግስት ለኢትዮጵያ እና አሜሪካ መንግስትታ ግንኙነት መጠናከር ከፍተኛ ትኩረት እንደሚሰጥ አረጋግጠዋል።።
ነእፓ ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ከሚገኙ የአሜሪካ ዲፕሎማቶች ጋር ውይይቶችን ማድረጉ ይታወሳል።።

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**መጋቢት 9 2013**
**አዲስ አበባ።።**

# በታሪካዊው የነጃሺ መስጂድ ላይ የደረሰውን ጥቃት ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በጽኑ ያወግዛል፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ በዓለም ከምትታወቅባቸው ታሪካዊ እና ሀይማኖታዊ ቅርሶች አንዱ የአልነጃሺ መስጊድ ይገኝበታል፡፡
ነጃሺ መስጂድ ለመላው ኢትዮጵያውያን ታላቅ መንፈሳዊ እና ብሄራዊ የኩራት ምንጭ ነው፣
ነጃሺ መስጊድ የኢትዮጵያውያን ብቻም ሳይሆን የመላው ዓለም ቅርስ እና ታሪክ ነው፣
ነጃሺ መስጊድ በአፍሪካ ብሎም በዓለም ከሚታወቁ እጅግ ጥንታዊና ታሪካዊ የእምነት ቦታዎች አንዱ ነው፣
ነጃሺ መስጊድ ኢትዮጵያውያን የምንኮራበት በሀይማኖት የመቻቻል ታሪክ ህያው ማሳያ ነው፣
ነጃሺ መስጊድ ለስደተኞች ክብር እና ከለላ በመስጠት ለዓለም ተምሳሌት የሆነው የታላቁ ንጉስ የነጃሺ መዘክር ነው፣

ይህ ትልቅ የሀገር እና የዓለም ቅርስ ጉዳት እንደደረሰበት እና በውስጡ የሚገኙ ጥንታዊ ሀብቶች መዘረፋቸው መላውን የሀገራችን ህዝቦች አሳዝኗል አስቆጥቷልም፡፡ ታሪካዊና ሀይማኖታዊ ቅርሶች እንዲከበሩ እና እንዲጠበቁ ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጠው ነእፓ በነጃሺ መስጂድ ላያ የደረሰውን ጥቃት በእጅጉ ያወግዛል፡፡ ይህ ኃላፊነት የጎደልው ድርጊት በማንም ይፈጸም በማን ከፍተኛ ወንጀል እና አሳፋሪ ድርጊት ነው፡፡ ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት በቅርሶች ላይ እና በእምነት ቦታዎች ላይ የሚደረግ ጥቃት በህግም በታሪክም የሚያስጠይቅ ወንጀል ነው፡፡ በነጃሺ መስጊዱ ላይ የደረሰው አደጋ ታሪካዊ ቅርሶች እና የአምልኮ ቦታዎች በጦርነት እና ግጭት ወቅቶች ጭምር ኢላማ እንዳይሆኑ የሚከለክሉ ዓለም አቅፍ ስምምነቶችንና አሰራሮችን የሚቃረን ተግባር ነው፡፡

የትግራይ ክልል ጊዚአዊ አስተዳድር እና የፌዴራል መንግስቱ በመስጊዱ ላይ የደረሰውን ጉዳት በተመለከት ዝርዝር ማብራሪያ በአፋጣኝ እንዲሰጡ እየጠየቅን፣ በተለያየ መንገድ በእምነት ቦታዎች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ለማስቆም የፌዴራል እና የክልል መስተዳድር አካላት ከፍተኛ ጥበቃ እንዲያደርጉ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ያሳስባል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ታህሳስ 24 2013**
**አዲስ አበባ**

# በሀገር መከላከያ ተቋማት ላይ የሚደረግን ጥቃት ነኢፓ ይቃወማል!!

## በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳይ ከነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የተሰጠ መግለጫ

በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ በሚገኙ የኢፌዴሪ መከላከያ ካምፖች እና ተቋማት ላይ የትግራይ ልዩ ኃይል እና ሚሊሻ ጥቃት መፈጸማቸውን የኢፌዴሪ መንግስት ዛሬ ማለዳ አስታውቋል። የኢትዮጲያ መከላከያ ሰራዊት የሀገርን ሰላም እና የህዝቦችን ደህንነት ከውስጥ እና ከውጭ ኃይላት ለመጠበቅና ለመከላከል ህገ መንግስታዊ ተልእኮ የተሰጠው ሀገራዊ ተቋም ሲሆን በተቋሙ ላይ የሚደረግ ማናቸውም ዓይነት ትንኮሳ ኢ-ህገ መንግስታዊ ከመሆኑም ባሻገር በሀገር አንድነት እና ሰላም ላይ የሚደረግ ጥቃት ተደርጎ ይወሰዳል።

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በሀገር መከላከያ ሰራዊት እና ተቋማት ላይ የሚደረግን ማናቸውም ዓይነት ጥቃት በጽኑ ይቃወማል። ደም እና ህይወቱን ገብሮ የሀገርን ሰላም ለመጠበቅ ሌት ከቀን በሚተጋው የሀገር መከላከያ ኃይል ላይ የተቃጣው ትንኮሳ አሳፋሪ እና አሳዛኝ ነው። በሀገራችን ከተጀመረው የሪፎርም እንቅስቃሴ ማግስት ጀምሮ በፌዴራል መንግስት እና በህወኃት መካከል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተካረረ የመጣው ልዩነት ወደ ግጭት እና ጦርነት ማምራቱ ለሀገራችን ህዝቦች አስደንጋጭ ዜና ነው፡፡ ሀገራችን ውስጥ ለዘመናት ከዘለቀው የጭቆናና የግፍ አገዛዝ ተላቀን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባት ከፍተኛ እንቅስቃሴ በሚደረግበት በአሁኑ ወቅት ግጭት መቀስቀሱ እጅግ አሳሳቢ ነው፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** የሀገራችን ነባር እና ወቅታዊ የፖለቲካ ስብራቶች ሊጠገኑ የሚችሉት በፖለቲካዊ መንገድ እንደሆነ ያምናል። በመሆኑም ፖለቲካዊ ፍላጎትን በኃይል ለመጫን የሚደረግን ህገ-ወጥ የኃይል እርምጃ አጥብቆ ይቃወማል። **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በትግራይ ክልል የተፈጠረው ግጭት በሰላማዊ ዜጎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ፣ ግጭቱ በአፋጣኝ ቆሞ ማናቸውም ዓይነት ልዩነቶች በድርድር የሚፈቱበት አማራጭ ጥቅም ላይ እንዲውል ያሳስባል።

ኃላፊነት በጎደላቸው ኃይሎች የተጫረው ይህ ግጭት በትግራይ እና በሌሎች የሀገራችን ህዝቦች መካከል ያለውን ወንድማዊ ግንኙነት እና አብሮነት እንዳያሻክር ተገቢው ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል። የተራዘመ ጦርነት እና ግጭት በድህነት አበሳ ውስጥ የሚኖሩትን የትግራይ እና መላው የሀገራችን ህዝቦች ለከፋ ችግር እና ሰቆቃ የሚዳርግ በመሆኑ ግጭቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመቋጨት ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል።

በተፈጥሮ ሀብቶቻችን የመጠቀም ህጋዊ እና ተፈጥሯዊ መብታችንን ለመግታት ከሚጥሩ የውጭ ኃይሎች ጋር እልህ አስጨራሽ ትግል በማድረግ ላይ ባለንበት በአሁኑ ወቅት፣ ውስጣዊ ቅራኔዎች ሀገራችንን ለውጭ ጠላት ይበልጥ ተጋላጭ የሚያደርግ በመሆኑ የተፈጠረው ግጭት በአጭር ጊዜ እንዲቋጭ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ያስታውቃል።

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ጥቅምት 25 2013**
**አዲስ አበባ**

# በሰላማዊ ዜጎች ላይ የሚደርሰው ጥቃት በአስቸኳይ ሊቆም ይገባል!!

ባለፉት ጥቂት ወራት ብቻ በተለያዩ የሀገራችን ክልሎች በርካታ ቁጥር ያላቸው ዜጎች ተገድለዋል፣ ለከፍተኛ የአካል ጉዳት ተዳርገዋል፣ ሀብት ንብረታቸው ወድሟል እንዲሁም ከቀያቸው ተፈናቅለዋል፡፡ በሰላማዊ ዜጎች ላይ የደረሱ ጥቃቶች በዋናነት ማንነትን መሰረት ያደረጉ መሆናቸው ወንጀሉን ይበልጥ ውስብስብ እና አደገኛ አድርጎታል፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣው በሰላማዊ ዜጎች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል።

በዜጎች ላይ የሚደርስ የትኛውም አይነት ጥቃት በተለይም ማንነትን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች የሀገራችንን ሰላም እና አንድነት፣ የዜጎችን አብሮነት ክፉኛ የሚፈታተኑ በመሆናቸው በአፋጣኝ ሊቆሙ ይገባል። በቤኒሻንጉል ጉሙዝ መተከል ዞን፣ በደቡብ ክልል በጉራ ፈርዳ ወረዳ እና በቅርቡ በምዕራብ ወለጋ ዞን ጉሊሶ ወረዳ በንጹሀን ዜጎች ላይ የደረሱ ጥቃቶች በሀገራችን ያለውን እጅግ አሳሳቢና በቀላሉ ተሰባሪ የደህንነት ሁኔታ በግልጽ ያመላክታል።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በዜጎች ህይወት እና ደህንነት ላይ የሚደርስን ማናቸውም ዓይነት ጥቃት በእጅጉ ያወግዛል። ጠባብ የፖለቲካ ፍላጎትን ለማሳካት በሰላማዊ ዜጎች ላይ የሚደረግ ጥቃት እጅግ የሚወገዝ ኢ-ሰብአዊ ድርጊት በመሆኑ ሁሉም ሰላም ወዳድ ኃይሎች በአንድነት ሊያወግዙት ይገባል። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በሀገራችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከተ የመጣውን በንጹሀን ዜጎች ላይ እየደረሰ ያለውን አሳዛኝ ጥቃት ለማስቆም፣ በሀገራችን አስተማማኝ ሰላም እና መረጋጋት ለማስፈን፣ ለግጭት እና ለዜጎች ሞት የሚዳርጉ ጥላቻ እና ቁርሾዎችን ለመቅረፍ አፋጣኝ ሁሉን አቀፍ እንቅስቃሴ መደረግ አለበት ብሎ ያምናል።

በንጹሀን ዜጎች ህይወት ላይ አደጋ በሚፈጽሙ ኃይላት ላይ የፌደራል እና የክልል መንግስታት በቂ እና አስተማማኝ እርምጃ አለመውሰዳቸው፣ በየጊዜው የሚደርሱ ጥቃቶች ምንነት እና መንስኤ እንዲሁም የድርጊቱን ፈጻሚዎች በፍጥነት በመለየት ለህዝብና ለፍትህ አለማቅረባቸው ጸረ-ሰላም ኃይላት በዜጎች ላይ የሚያደርስቱን ኢ-ሰብአዊ ጥቃት እንዲቀጥሉበት እድል ሰጥቷቸዋል።

በዜጎች ላይ የሚደርሱ ተደጋጋሚ ጥቃቶችን **"ያልታወቁ ቡድኖች በዜጎች ላይ ጥቃት ፈጸሙ"** የሚሉ መግለጫዎች እየሰጡ ማለፍ ለዜጎቸ ህይወት እና ደህንነት ደንታ ቢስነት ከመሆን በተጨማሪ ወንጀለኞችን የሚያበረታታ ተግባር ነው። በመሆኑም መንግስት ህግ እና ስርአትን በሚተላለፉ ኃይሎች ላይ ፈጣን እና ተገቢ እርምጃ በመውሰድ ከምንም በላይ የዜጎችን ህይወት፣ ንብረት፣ ሰላም እና ደህንነት ሊጠብቅ ይገባል። መንግስት ኃይል የመጠቀም ብቸኛ መብቱን በመጠቀም በጸረ ሰላም ኃይሎች ላይ አስተማሪ እርምጃ በመውሰድ የዜጎችን ህይወት እና ደህንነት የመጠበቅ የህግ፣ የሞራል እና የታሪክ ተጠያቂነት አለበት።

ነኢፓ ብሄራዊ ውይይት እና መግባባት እንዲፈጠር በተደጋጋሚ ሀሳብ ሲያቅርብ የቆይ መሆኑ የሚታወስ ሲሆን፣ በዜጎች ላይ እየደረሰ ያለውን አሰቃቂ ሞት እና ስቃይ ለማስቆም ዛሬም አፋጣኝ ብሄራዊ ውይይት እና መግባባት እንዲፈጠር ጥሪውን በድጋሜ ያቀርባል። በተለይ መንግስት እና የተፎካካሪ ፓርቲዎች በሀገራችን ላይ ያንጣበበውን የግጭትና የጦርነት አደጋ ከስር መሰረቱ ለመቅረፍ ተቀራርበው ሊሰሩ እና ዘላቂ መፍትሄ ሊያበጁ የሚገባባት ታሪካዊ ወቅት ላይ እንገኛለን።

በዜጎች መካከል ግጭት እንዲፈጠር እና እንዲባባስ የሚያደርጉ ምክንያቶችን ለማስቆም በተለይ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ አክቲቪስቶች እና የሚዲያ ተቋማት ከፍተኛ ኃላፊነት እና ተጠያቂነት እንዳለባቸው ነእፓ ያስገነዝባል። መላው የሀገራችን ህዝቦች፣ መንግስት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሀይማኖት ተቋማት፣ የሲቪክ ማህበራትና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በሰላማዊ ዜጎች ላይ የሚደርሱ ኢ-ሰብአዊ ጥቃቶች እንዲቆሙ የበኩላቸውን ጥረት እንዲያደርጉ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ጥሪውን ያቀርባል።

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ጥቅምት 23 2013**
**አዲስ አበባ።።**

# Ethiopians never exchange sovereignty for US Dollar: "Ethiopians' Life Matter"

**Freedom and Equality Party (FEP)** strongly condemns the statement given by the US president Donald Trump regarding the Grand Ethiopian Renaissance Dam (GERD). The naïve and reckless statement by the president shows his ignorance about Ethiopia, its patriotic people and Ethiopia's Geo-political role in the region and Africa. The remarks by the president is unfitting to a president administering a world super power like the US.

The statement by Trump is in contradiction to the long standing Ethio-American diplomatic relations which is based on mutual trust and respect. The remark is also tantamount to inciting war between Ethiopia and Egypt. Trump's statement is also against US's expected role as an observer in the tripartite negotiation between Ethiopia, Sudan and Egypt. The president's speech is part of his poor record on human rights in his domestic politics and failed diplomacy with Africa and rest of the world.

The president should know that GERD is a result of poor Ethiopians investing their hard-earned saving, expecting to get ride of the abject poverty that we are in and build a bright future. Ethiopian would stand hand in hand against any foreign intervention to intrude the completion and utilization of the dam, which is expected to ignite Ethiopia's economic development and end poverty. The people and government of Ethiopia will never compromise national sovereignty and freedom for foreign aid.

FEP calls upon Ethiopians & ended African Americans and all peace-loving people in the US to use their vote in US general election, to be held next week, to support world Freedom, Equality and Justice and to stop racism, hatred and irresponsible diplomacy. The president and the world should know that Ethiopians never compromise on their national dignity and never exchange sovereignty for US Dollar.

**Freedom and Equality Party (FEP)**
**26 October, 2020**
**Addis Ababa.**

# ወለድ አልባ የፋይናንስ ስርአት ለፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል እና ለዴሞክራሲያዊ አንድነት!!

የመጀመሪያው ሙሉ ለሙሉ ከወለድ ነጻ ባንክ ፍቃድ ማግኘቱ የሚደገፍ ተግባር ነው!!

የሀገራችን የፋይናንስ ሴክተር ካሉበት ድርብርብ ችግሮች አንዱ የተደራሽነት ውስንነት ነው፡፡ የሀገራችን የፋይናንስ ተቋማት አገልግሎቶቻቸው በዋናነት በወለድ ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው፣ በተለያየ ምክንያት በወለድ ስርአት መጠቀም ለማይፈልጉ ዜጎች ተደራሽ ሳይሆኑ ቀርተዋል፡፡ በዚህም ምክንያት በንግድና ኢንቨስትመንት ተሰማርተው ራሳቸውንና ሀገራቸውን መጥቀም የሚሹ በርካታ ወገኖች ህልማቸውን እውን ማድረግ ሳይችሉ ከመቅረታቸውም በላይ ሀገራችን የተሻለ እድገት ለማስመዝገብ የነበራትን ሰፊ እድል አጥታለች፡፡ በሀገራችን የተሟላ ከወለድ ነጻ የፋይናንስ ስርአት መስፋፋት፣

- ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ በኢኮኖሚው ውስጥ እንዲንቀሳቀስ፣ የቁጠባና የኢንቨስትመንት ምጣኔ ከፍ እንዲል ድርሻው የጎላ ነው፣
- የወለድ አልባ የፋይናንስ ተቋማት መስፋፋት ተጨማሪ የስራ እድል እንዲፈጠር በማድረግ የሀገራችን የስራ አጥነት ምጣኔ ዝቅ እንዲል ከፍተኛ አስተዋጾ ያደርጋሉ፣
- ከወለድ ነጻ የፋይናንስ ስርዓት መነልበት ተጨማሪ የውጭ የቀጥታ ኢንቨስትመንትን በመሳብ የሀገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት እንዲያድግ፣ የዋጋ ግሽበት እንዲቀንስና የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ እንዲኖር ያደርጋል፣
- የወለድ አልባ የፋይናንስ ስርአት ማደግ ከምንም በላይ በዜጎች መካከል ፍትሀዊ የገቢ እና የሀብት ክፍፍል እንዲፈጠር በማድረግ ሰላም እና መረጋጋት እንዲሁም ዴሞክራሲያዊ አንድነት እንዲጠናከር ፋይዳው የላቀ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር ጥቅምት 2፣ 2013 **የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ** ሙሉ ለሙሉ ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት ለመስጠት በምስረታ ላይ ካሉ ባንኮች አንዱ ለሆነው **የዘምዘም ባንክ** ፍቃድ መስጠቱ ከፍተኛ ሀገራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያለው እርምጃ ነው፡ :

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** (**ነእፓ**) በዜጎች መካከል ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፍትህ እንዲረጋገጥ አስተዋጾ የሚያደርጉ አማራጭ የፋይናንስ ስርዓቶች እንዲስፋፉ በፓርቲው ፕሮግራም ያከተተ ሲሆን ለተግባራዊነቱም ጠንክሮ ይሰራል፣ አካታች የፋይናንስ ተቋማት እንዲስፋፉና እንዲጎለብቱ የሚወሰዱ ፖሊሲዎችን ይደግፋል፡፡

**የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ** ሙሉ ለሙሉ ከወለድ ነጻ አገልግሎት ለመስጠት ለተቋቋሙ ባንኮች ፍቃድ መስጠት መጀመሩ እጅግ የሚያስመሰግን ተግባር ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ብሄራዊ ባንክ የጀመረውን ጥረት በማጠናከር ወለድ-አልባ ባንኮችና ሌሎች ከወለድ ነጻ የፋይናንስ ተቋማት ስራቸውን በቅልጥፍና የሚሰሩበት ምቹ የህግ ማእቀፍ ለመፍጠር ዝርዝር ደንቦችና መመሪያዎችን እንዲሁም የአሰራር ማንዋሎችን በማዘጋጀት የሀገራችንን የፋይናንስ ስርዓት ቀልጣፋና ተወዳዳሪ ለማድረግ የጀመረውን ጥረት አጠናክሮ እንዲቀጥል **ነእፓ** ጥሪውን ያቀርባል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ጥቅምት 3 2013**
**አዲስ አበባ፡፡**

# <u>የአንበጣ መንጋ በገበሬዎች ላይ በማድረስ ላይ ያለውን ጉዳት ለመቀነስ አስቸኳይ ሀገራዊ ንቅናቄ ያስፈልጋል!!</u>

## አደጋው በሺዎች የሚቆጠሩ ድሀ ገበሬዎችን ተስፋ አጨልሟል፡፡

ሰሞኑን በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የአንበጣ መንጋ በሰብል ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማድረሱ ታውቋል፡፡ በተለይ በሰሜን እና በሰሜን ምስራቅ የሀገራችን ክፍሎች የተከሰተው የአንበጣ መንጋ ከፊል የአማራ፣ የትግራይ እና የአፋር ክልል ገበሬዎችን እና አርብቶ አደሮችን እርሻ በከፍተኛ ደረጃ ያጠቃ ሲሆን፣ ሊሰበሰብ የደረሰ ሰብል ሙሉ ለሙሉ አውድሟል፡፡ የአንበጣ መንጋውን ለመከላከል የአካባቢው ህብረተሰብ፣ የክልል፣ የዞን እና የወረዳ ግብርና አካላት ባህላዊ እና ዘመናዊ (የኬሚካል ርጭት) መንገዶችን በመጠቀም መንጋውን ለመከላከል ከፍተኛ ርብርብ ቢያደርጉም ችግሩ ከአካባቢው ማህበረሰብ አቅም በላይ በመሆኑ መቋቋም አልተቻለም፡፡ በዚህም በሺዎች የሚቆጠሩ ገበሬዎች ማሳ ጉዳት ደርሶበታል፡፡ በአንበጣ መንጋ ከተጠቁ አካባቢዎች መካከል በአማራ ክልል የደቡብ እና ሰሜን ወሎ እንዲሁም የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞኖች ይገኙበታል፡፡

ምርታማነቱ እጅግ ዝቅተኛ በሆነ የእርሻ ስራ ኑሮው ከእጅ ወደ አፍ የሆነው የሀገራችን ገበሬ፣ በከፍተኛ ድካም ያፈራው ሰብል በአንበጣ መንጋ ሲወድም ለከፋ ርሀብ፣ ለስደት እና ለሞት ይዳረጋል፡፡ ችግሩ በገበሬው ላይ ብቻ ሳይወሰን በሀገር ደረጃ የምግብ ሰብሎች ዋጋ መናር እና አጠቃላይ የምግብ ዋስትና ቀውስ ያስከትላል፡፡ የሀገራችን ኢኮኖሚ ዋልታ በሆነው የእርሻ ዘርፍ የሚደርስ ጉዳት ከፍተኛ እና ውስብስብ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግሮችም ያስከትላል፡፡ በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች የተከሰተው የአንበጣ መንጋ ከፖለቲካዊ አለመረጋጋት፣ ኮቪድ 19 ወረርሽኝ፣ የጎርፍ መጥለቅለቅ ጋር ተደምሮ የዜጎችን በተለይም በመንጋው በተጠቁ አካባቢዎች የሚኖሩ ገበሬዎችን ተስፋ አጨልሟል፡፡

በመሆኑም እንደ ሀገር የገጠመንን ይህንን የአንበጣ ወረርሽን ለመከላከል ህብረተሰቡ፣ መንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በቅንጅት መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ዜጎች በዘርፈ ብዙ የሰው ሰራሽ እና ተፈጥሮ አደጋዎች ለከፋ ጉዳት በተዳረጉበት በዚህ ወቅት፣ በተለይም የፌዴራል መንግስት የልማት ፕሮጀክቶቹን ቅደም ተከተል ሊፈትሽ ይገባል፡፡ መንግስት እንደ ሀገር ያለንን ውስን ሀብት እና አቅም አንገብጋቢ ካልሆኑ ፕሮጀክቶች በማዞር በአንበጣ እና በጎርፍ ከፉኛ የተጎዱ የአርሶ አደር እና አርብቶ አደር አካባቢዎችን ለመታደግና መልሶ ለማቋቋም ሊጠቀምበት ይገባል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**መስከረም 30 2013**
**አዲስ አበባ**

# መንግስት ህግ የማስከበር ሀላፊነቱን ህግን አክብሮ ይወጣ!! የፍርድ ቤት ውሳኔ ይከበር!!

መንግስት ከተሰጠው ህገ መንግስታዊ ኃላፊነቶች አንዱ እና ዋነኛው የዜጎችን ሰላም እና ደህንነት ማስከበር ሲሆን፣ ይህንን ኃላፊነቱን በአግባቡ ይወጣ ዘንድ የተለያዩ የፍትህ እና የጸጥታ አካላት በተናጠል እና በጋራ ይሰራሉ፡፡ የፍትህ እና የጸጥታ አካላት የተጣለባቸውን ከፍተኛ ህገ መንግስታዊ ኃላፊነት ሲፈጽሙ ህግ እና ስርአትን ሊያከብሩ እና ሊያስከብሩ እንደሚገባ ይታመናል፡፡ የፍትህ አስከባሪ አካላት ከፖለቲካ ወገንተኝነትና ከመንግስት ጣልቃ ገብነት ነጻ ሆነው ስራቸውን ሊያካሂዱ፤ ተጠሪነታቸው እና ተጠያቂነታቸው ለሀገር እና ለህዝብ ሊሆን ይገባል፡፡

መንግስት ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ሰላም እና ጸጥታን ለማስከበር በሚል በተለያዩ አካባቢዎች በርካታ ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ስር ማዋሉ የሚታወስ ሲሆን ከተጠርጣሪዎች ውስጥ ከፍተኛ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ የተፎካካሪ ፓርቲ አመራሮች መካከል አንዳንዶቹ በፍርድ ቤት በዋስ እዲለቀቁ ቢወሰንም፣ ውሳኔው ተግባራዊ አለመደረጉ ዜጎች በሀገራቸው የፍትህ ስርአት ላይ ጥርጣሬ እንዲያድርባቸው አድርጓል፡፡ የተከሰተው ለፍርድ ቤት ውሳኔ ተገዥ ያለመሆን አሰራር የሀገራችን የፍርድ ስርአት ያለበትን ክፍተት በጉልህ ከማሳየቱም በተጨማሪ በፖለቲካ አመራሮች ላይ መንግስት “የህግ የበላይነትን” ለማስከበር በሚል እየወሰደ ያለውን እርምጃ በጥርጣሬ እንዲታይ አድርጓል፡፡

በህግ የበላይነት መከበር ከፍተኛ እምነት ያለው **የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** የፍርድ ቤት ውሳኔዎች ተፈጻሚ የማይሆንበትን አሰራር አጥብቆ ይቃወማል፡፡ ነጻ እና ገለልተኛ የፍርድ ስርአት አለመኖር ለሀገራችን ሰላም እና አንድነት፣ እንዲሁም በብዙ ውጣ ውረድ ውስጥ በማለፍ ላይ ለሚገኘው የለውጥ እንቅስቃሴ ከፍተኛ እንቅፋት ይሆናል፡፡ በመሆኑም በየትኛውም ደረጃ ያሉ የህግ ታራሚዎች በእስር ላይ በሚቆዩበት ወቅት ሰብአዊ መብቶቻቸው እንዲከበሩ እና መንግስት ህግና ስርአትን የማስከበር ኃላፊነቱን ህግን አክብሮ ሊፈጽም ይገባል፡፡

የፍርድ ቤት ውሳኔን በተለያዩ ምክንያቶች አለመፈጸም ወይም ማዘግየት የዜጎችን ሰብአዊ እና ዴሞክራሲዊ መብቶች የሚሸራርፍ፣ የሀገራችንን የፍትህ ስርአት የሚያዛባ እና ለውጡን የሚያሰናክል በመሆኑ በአስቸኳይ ሊታረም እንደሚገባ **የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ያሳስባል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**መስከረም 29 2013**
**አዲስ አበባ**

# በብሄራዊ መግባባት ዙሪያ ነእፓ ጥናታዊ ጽሁፍ አቀረበ።

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አስተባባሪነት በሀገራችን ብሄራዊ መግባባት በመፍጠር ሰላምና መረጋጋት እንዲሁም ዴሞክራሲያዊ ሽግግር እውን ለማድረግ በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የመጀመሪያ ዙር ውይይት ነሀሴ 16 2012 መካሄዱ ይታወሳል። የዚሁ መድረክ ሁለተኛ ዙር ውይይት ነሀሴ 30 2012 በአዲስ አበባ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን (ECA) ተካሂዷል። በውይይቱ ላይ በከፍተኛ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች አራት የተለያዩ ጽሁፎች የቀረቡ ሲሆን፣ የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ሊቀመንበር ዶ/ር አብዱልቃድ አደም "ብሄራዊ መግባባት በኢትዮጵያ፡ ዘላቂ ሰላም ፣ ሀገራዊ አንድነት እና ዴሞክራሲያዊ ሽግግር" በሚል ርእስ ጥናታዊ ጽሁፍ አቅርበዋል።

ዶ/ር አብዱልቃድር የብሄራዊ መግባባት ምንነት፣ አጠቃላይ ማዕቀፍ፣ አደረጃጀት፣ ዓለም አቀፍ ተሞክሮ እና ሌሎች ከብሄራዊ መግባባት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በዝርዝር ያቀረቡ ሲሆን ብሄራዊ መግባባትን አስመልክቶ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ግልጽ እና ተቀራራቢ አቋም እንዲኖራቸው ለማድረግ እንዲሁም ብሄራዊ መግባባትን አስመልክቱ የተሳሳቱ ግንዛቤዎችን ለማስተካካል ጥናታዊ ጽሁፉ ከፍተኛ ፋይዳ እንደነበረው በውይይቱ የተሳተፉ የፖለተካ ፓርቲዎች ገልጸዋል። የቀረበው ወረቀት በሀገራችን በቅርቡ ይጀመራል ተብሎ በሚጠበቀው ሁሉን አቀፍ የብሄራዊ መግባባት ሂደት ላይ ከፍተኛ አስተዋጾ እንደሚኖረው ይታመናል።

ነእፓ ቀደም ሲል በሀገራችን በብሄራዊ መግባባት ዙሪያ የመነሻ ጽሁፍ በማዘጋጀት ሀሳቡን ለመንግስት፣ ለፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ለሲቪክ ማህበራትና በኢትዮጵያ ለሚገኙ የውጪ ሀገር የዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ ማሰራጨቱ ይታወሳል። ነእፓ በሀገራችን ሰላም፣ መረጋጋትና አንድነት እንዲሰፍን፣ ቀጣዩ ምርጫ ነጻ ፍትሀዊ እና ቅቡል እንዲሆን ሁሉን አቀፍ የብሄራዊ መግባባት ሂደት በአፋጣኝ መካሄድ እንዳለበት በጽኑ ያምናል። ይህንኑ እውን ለማድረግ ፓርቲው የጀመረውን ጥረት ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን አጠናክሮ ይቀጥላል።

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ነሀሴ 30፣ 2012**
**አዲስ አበባ**

# የህዳሴ ግድብ የመጀመሪያ ዙር የውኃ ሙሊት መጠናቀቅ ብሄራዊ ስኬት ነው!!

የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ላለፉት ዘጠኝ አመታት መላው የሀገራችን ህዝቦች ለግድቡ ግንባታ ካላቸው ላይ ቆርሰው በገንዘባቸው፣ በጉልበታቸው እና በእውቀታቸው የሚችሉትን እያደረጉ የግንባታውን ሂደት በጉጉት ሲከታተሉ ቆይተዋል። ለግድቡ ከተደረገው ከፍተኛ ድጋፍ እና ጉጉት በተቃራኒ የግንባታው ሂደት በርካታ የቴክኒክ፣ የአስተዳደር እና ዲፕሎማሲያዊ ውጣ ውረዶች ኢጋጥመውታል። ታላቁ የህዳሴ ግድብ እነዚህን በርካታ ተግዳሮቶች አልፎ የመጀመሪያ ዙር የውሀ ሙሊት በተሳካ ሁኔታ ለማጠናቀቅ መቻሉ ለመላው የሀገራችን ህዝቦች እና ለኢትዮጵያ ወዳጆች ከፍተኛ ደስታ ፈጥሯል። ግድቡ ውሀ ተሞልቶ በግድቡ አናት ላይ ሲፈስ ማየት በጉጉት ስንጠብቀው የነበረ እጅግ አስደሳች ክስተት ነበር።

ሀገራችን በተፈጥሮ ሀብቷ በተለይም በወንዞቿ መጠቀም ሳትችል በርካታ ትውልድ በድህነት እና በጨለማ አልፏል። በተለይ ታላቁን የአባይ ወንዝ ለሀገራችን እድገት እና ለኢትዮጵያውያን ህይወት መለወጥ ጥቅም ላይ ለማዋል መላው የሀገራችን ህዝቦች ለረዥም ዘመናት ሲናፍቁ ኖረዋል። የታላቁ ህዳሴ ግድብ ለኢትዮጵያውያን የልማት እና የዳቦ ጥያቄ ነው። የዝናብ ጥገኛ የሆነው የሀገራችን ግብርና እንዲዘምን፣ ኢንዱስትሪ እንዲስፋፋ፣ ከተሞቻችን እንዲያበሩ፣ በገጠር የሚኖሩ ወገኖቻችን ሸክም እንዲቀንስ፣ በማገዶ ሸክም የጎበጠው የእናቶቻችን ወገብ እንዲያገግም ... ሀገራችንን ወደተሻለ የእድገት ምዕራፍ ለማሸጋገር የሚያስፈልገንን ኃይል ለማገኘት የታላቁ ህዳሴ ግድብ በትልቅ ተስፋ እና በጉጉት የሚጠበቅ ግዙፍ ሀገራዊ ፕሮጀክት ነው። የግድቡ የውሀ ሙሊት ከድህነት በአጭር ጊዜ መውጣት ይቻላል የሚለው እምነታችን ይበልጥ እንዲጠነክር ተስፋችን እንዲያብብ አድርጎታል።

ዛሬ ላይ የደረስንበት ስኬት የትላንት የጋራ ርብርብ ውጤት መሆኑ እሙን ነው፤ ከስኬት ሀዲድ ገባን እንጂ ጉዟችንን አላገባደድንም። ግድቡ ሙሉ ለሙሉ ተጠናቆ ጥቅም ላይ እስኪውል ብዙ ስራዎች ከፊታችን ይጠብቁናል። ይህንን ውጥን እውን ለማድረግ ከምንም በላይ ሰላምና መረጋጋት እጅግ አስፈላጊ ነው። ሰላማችንን ለመጠበቅ የፖለቲካ ልዩነቶቻችንን በድርድር እና በመግባባት ለመፍታት በከፍተኛ የኃላፊነት እና የተጠያቂነት ስሜት ጥረት ማድረግ ይገባል።

ለግድቡ ቀሪ ስራዎች ማጠናቀቂያ የሚያስፈልገውን ከፍተኛ ሀብት ማሰበሰብ ሌለው ትኩረት የሚሻ ስራ ነው። እንደ እስከ ዛሬው ሁሉ ድጋፍ በማድረግ እና ቦንድ በመግዛት ከፍተኛ ርብርብ ማድረግ ያስፈልጋል። የግድቡን የመጀመሪያ ዙር የውኃ ሙሌት በደስታ ስናከብር ለግድቡ እውን መሆን በሀሳብ፣ በአመራር፣ በገንዘብ፣ በሙያ፣ በጉልበት፣ አስተዋጾ ላደረጉ በሀገር ውስጥ እና በውጭ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ምስጋና በማቅረብ ነው።

በህዳሴ ግድብ ግንባታ ያሳየነውን የትብብር መንፈስ አጠናክረን በመቀጠል ዜጎች በነጻነት እና በእኩልነት የሚኖሩባት ከድህነት እና ኢ-ፍትሀዊነት ነጻ ሀገር ለመገንባት ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።
እንኳን ደስ ያለን።

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ሀምሌ 15፣ 2012**
**አዲስ አበባ**

# የሀገር መከላከያ ሰራዊትን ለማጠናከር እና ለማዘመን የሚሰራ ስራ የሚደገፍ ነው!!

የሀገርን ዳር ድንበር እና የዜጎችን ሰላም የመጠበቅ ህገ መንግስታዊ ኃላፊነት የተጣለበት የሀገር መከላከያ ሰራዊታችን ሀገር እና ህዝብ የጣሉበትን ታላቅ ኃላፊነት በከፍተኛ የሀገር ፍቅር ስሜት እና በላቀ የሙያ ስነምግባር ግዳጁን በመወጣት ላይ ይገኛል፡ ፡ ሰራዊታችን ከአባቶቻችን የወረስነውን አኩሪ የጀግንነት ታሪክ አስጠብቆ ሀገራችን በተለያዩ ጊዜያት ከውጪ እና ከውስጥ የተቃጡባትን አደጋዎች በአስተማማኝ ሁኔታ ሲመክት ቆይቷል፡፡

የመከላከያ ኃይላችን ከጊዜ ወደ ጊዜ አቅሙን በማጠንከር በአደረጃጀት፣ በቴክኖሎጂ፣ በስትራቴጂ፣ በወታደራዊ ስልት... ራሱን እያደሰ ዛሬ ላይ ደርሷል፡፡ በፍጥነት በሚያድረገው የመከላከያና የደህንነት ኢንዱስትሪ ውስጥ የሀገር መከላከያ ኃይላችን ብቃቱን ጠብቆ በማንኛውም ጊዜ ሉአላዊነታችንን የሚፈታተኑ አደጋዎችን ለመመከት ተከታታይ እና የተሟላ የአቅም ግንባታ ስራ መስራት ያስፈልጋል፡፡ይህንን እውን ለማድረግ የሀገራችን ኢኮኖሚ በሚፈቅደው ልክ በቂ ሀብት መመደብ የግድ ይላል፡ ፡

ከዚህ አንጻር በትላንትናው እለት ውይይት የተደረገበት የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት ማንባታ ስትራቴጂ ሰነድ ትልቅ ዋጋ የሚሰጠው እና የሚደገፍ እርምጃ ነው፡፡ የሀገራችን የመከላከያ ኃይል የሀገራችንን፣ የአካባቢያችንን እና የዓለምን ተጨባጭ ከግምት ውስጥ ያስገባ ቀጣይነት ያለው የአቅም ግንባታ እና ማሻሻያ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በውይይቱ ላይ ክቡር ጠቅላይ ሚንስትሩ እንደገለጹት ዋና ዓላማው የሀገሪቱን ህገ መንግስት ማስከበር የሆነ፣ ከአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ርእዮተዓለም እና ወገንተኝነት የራቀ፣ የሀገራችንን ህዝቦች ብዝሀነት ታሳቢ ያደረገ ጠንካራ እና ዘመናዊ የሀገር መከላከያ መገንባት ለሀገራችን ሁለንተናዊ እድገት እና ሰላም እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

ሰነዱ ውይይት የተደረገበት ወቅት ሀገራችን በተፈጥሮ ሀብቷ ላይ የመጠቀም ተፈጥሯዊ መብቷን ለማስከበር ህዝብ እና መንግስት ከፍተኛ ርብርብ በሚያደርጉበት ወቅት መሆኑ ልዩ ያደርገዋል፡፡ ነጻነት እና እኩልነት ፓርቲ ሀገራችን በየጊዜው የሚያጋጥሟትን የደህንነት ስጋቶች በአስተማማኝ ሁኔታ መመከት የሚችል የሀገር መከላከያ ኃይል ለመገንባት የሚደረገውን ማንኛውን እንቅስቃሴ ይደግፋል፣ ለተግባራዊነቱ የሚጠበቅበትን ለማበርከት ይሰራል፡፡

**የነጻነት እና እኩልነት ፓርቲ**
**ሰኔ 15፣ 2012**
**አዲስ አበባ**

# የሃይማኖት እኩልነት ለሀገር ሰላም እና እድገት የመሰረት ድንጋይ ነው!!

**የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤትንና የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስልን በአዋጅ ማቋቋም በህገ መንግስት የሰፈረውን የሀይማኖት እኩልነት ያረጋገጠ ውሳኔ ነው።**

ኢትዮጵያ የተለያየ ባህል እና ሀይማኖት ያላቸው ህዝቦች በሰላም እና በፍቅር የሚኖሩባት ሀገር መሆኗ ይታወቃል። ክርስትና እና ኢስላም በኢትዮጵያ ታሪክ እና ሀገረ መንግስት ግንባታ ከፍተኛ ሚና ነበራቸው። ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች እና ሙስሊሞች በወንድማማችነት እና በመከባበር ለትውልድ የሚተላለፍ አኩሪ ታሪክ ባለቤት ናቸው። ከዚህ የአብሮነት ታሪክ በተጻራሪ በተለያየ ዘመን በሀገራችን የነገሱ መሪዎች አንዱን ከፍ ሌላውን ዝቅ የማድረግ ፖሊሲ ይከተሉ እንደነበር ታሪክ የሚመሰክረው ሀቅ ሲሆን በዚህም ምክንያት የዜጎች የእምነት እና የአምልኮ ነጻነት የተገደበባቸው ኢጋጣሚዎች አልፈዋል።

የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የመደራጀት እና ህጋዊ እውቅና ያለው ሀገራዊ ተቋም የመፍጠር ዘመን ተሻጋሪ ህልም እውን ይሆን ዘንድ ተከታታይ ትውልዶች ለመንግስት ጥያቄ ሲያቀርቡ ቆይተዋል። የሙስሊሙ የእምነት አባቶች የመጅሊስ የህጋዊ እውቅና ጥያቄአቸውን ያለመታከት ለቀድሞ መንግስታት ሲያቀርቡ የቆዩ ቢሆንም ሰሚ ሳያገኝ ዛሬ ላይ ደርሰናል። ባለፉት ጥቂት አመታት የመንግስት የኃይማኖት ጣልቃ ገብነት እንዲቆም እና ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችን የሚወክል ጠንካራ ብሄራዊ ተቋም እንዲቋቋም ከፍተኛ እንቅስቃሴ ተካሂዷል። ዛሬ ላይ የጸደቀው የመጅሊስ ማቋቋሚያ አዋጅ ተከታታይ ትውልዶች የከፈሉት ከፍተኛ ዋጋ ፍሬ ነው።

በተመሳሳይ ህጋዊ ሰውነት እና እውቅና እንዲሰጣቸው ሲጠይቁ የኖሩ የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል አባል ኢትዮጵያዊያን ጥያቄአቸው በመንግስት ተቀባይነት እንዲያገኝ ለረዥም ዘመናት በትእግስት ቆይተው በዛሬው እለት ካውንስሉ በአዋጅ መቋቋሙ ታሪካዊ ነው። **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ (ነኢፓ)** ለመላው ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች እና ለኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል አባል ምእመናን፣ እንዲሁም በሀገራችን የኃይማኖት ነጻነት እና እኩልነት እንዲረጋገጥ ለታገሉ ኢትዮጵያውያን በሙሉ እንኳን ደስ አላችሁ ይላል።ትግላችሁ ፍሬ አፍርቷል እና ደስ ሊላችሁ ይገባል።

የዜጎችን የእኩልነት ጥያቄዎች ህጋዊ ምላሽ ሲያገኝ አንድነታችን ይጠነክራል፣ አብሮነታችን ይጎለብታል፣ ሰላማችን ይጠበቃል፣ የዜጎች የጋራ ጠላት ከሆነው ድህነት ለመላቀቅ እንደ ሀገር የምናደርገው ትግል በአጭር ጊዜ እንዲሳካ ዋስትና ይሠጣል። ሁለቱ የእምነት ተቋማት በአዋጅ የጸደቁበት የዛሬው እለት የእምነት እና የብሄር ልዩነቶቻችንን ተሻግረን የህዝቦች ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚከበርባት፣ ዜጎች **በነጻነት እና በእኩልነት** የሚኖሩባት ሰላማዊ ሀገር ለመገንባት በአዲስ መንፈስ የምንነሳበት ታሪካዊ እለት ነው።

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ሰኔ 4፣ 2012**
**አዲስ አበባ**

# “የዜጎች ሰብአዊ መብት የማይታለፍ ቀይ መስመር ነው”

የሀገራችን ኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት አያያዝ ታሪክ በዓለምአቀፍ ደረጃ እጅግ ዝቅተኛ መሆኑ ይታወቃል፡፡ የኢትዮጵያ መንግስታት በዜጎች ላይ እጅግ ዘግናኝ ኢ-ሰብአዊ ድርጊቶችን ፈጽመዋል- ከህግ ውጪ ግድያ፣ እስርና ግርፋት፣ ያለክስ ለተራዘመ ጊዜ ማቆየት በዜጎች ላይ ያለገደብ የሚፈጽሟቸው የተለመዱ ድርጊቶች ሆነው ዘመናት አልፈዋል፡፡ ዜጎች በፖለቲካ አመለካከታቸው፣ በብሄራቸው፣ በኃይማኖታቻው ወይም በሌላ ማንነታቸው ምክንያት ሰብአዊ መብቶቻቸው ተጥሶ እጅግ ለከፋ እና አሰቃቂ ግፍ ተዳርገዋል፡፡

በዜጎች ላይ በተፈጸሙ ኢ-ሰብአዊ እርምጃዎች አያሌ ወገኖቻችን ህይወታቸውን አጥተዋል፣ አካላቸው ጎድሏል፣ ሀብት ንብረታቸውን አጥተዋል፣ ሴቶች ክብራቸው ተደፍሯል፣ ቤተሰብ ተበትኗል፣ ህጻናት ያለ አሳዳጊ አረጋውያን ያለጧሪ ቀርተዋል፡ ፡ የሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አለመከበር ሀገራችንን ብዙ ዋጋ አስከፍሏታል- ሰብአዊ እና ፖለቲካዊ ቀውስ፣ አመጽ፣ የእርስ በርስ ጦርነት፣ የኢኮኖሚ ድቀት፣ ከብዙ በጥቂቱ ይገኙበታል፡፡ ባለፉት ሶስት አስርተ ዓመታት ሀገሪቱን ሲያስተዳድር የነበረው ስርአትም ከፍተኛ የሆነ የሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ረገጣ ሲያካሂድ ቆይቷል፡፡

መንግስታት በዜጎች ላይ የሚፈጽሙትን ግፍ እና ጭካኔ በመቃወም ዜጎች በሀገራችን የሰብአዊ መብቶች ሳይሸራረፉ እንዲከበሩ ለማድረግ ከሰላማዊ እና ፖለቲካዊ ትግል ነፍጥ አንስቶ እስከ መታገል የደረሰ እልህ አስጨራሽ ትግል አካሂደዋል፡፡ በውጤቱም ጸረ ዴሞክራሲ መሪዎች በህዝብ ትግል ተራ በተራ ከስልጣን ተወግደዋል፡፡ ከቀደመው የማይማሩ አምባገነን መሪዎች ፀረ-ዴሞክራሲ እና ፀረ ሰብአዊ መብት ፖሊሲዎቻቸውን እንደ ዱላ እየተቀባበሉ ዛሬ ላይ ደርሰናል፡፡

ከ2007 ጠቅላላ “ምርጫ” ማግስት በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ይበልጥ የተቀጣጠለው ህዝባዊ አመጽ መሰረታዊ ምክንያት የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች በህዝባችን ላይ የፈጸሟቸው ዘግናኝ እና ኢ-ሰብአዊ ድርጊቶች የቀሰቀሰው ህዝባዊ ቁጣ ነው፡፡ ግድያ እና እስር ያንገሸገሻቸው የሀገራችን ወጣቶች ከገዢው ፓርቲ የአፈና መዋቅር ጋር ፊት ለፊት ተጋፍጠው ገዢው ስርአት ማሻሻያ እንዲያደርግ አስገድደዋል፡፡ በውጤቱም በተለያዩ መስኮች አንፃራዊ ለውጦች የተገኙ ቢሆንም፤ የሰብአዊ መብት አያያዝን ጨምሮ ህዝብ ያነሳቸው የዴሞክራሲ፣ የመልካም አስተዳደር እና የፍትህ ጥያቄዎች አልተመለሱም፡፡

የሀገራችን የሰብአዊ መብት አያያዝ ያለበትን አስከፊ ደረጃ በተመለከተ የተለያዩ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች የሚያወጧቸው ሪፖርቶች አመላካች ሲሆኑ፣ አምነስቲ ኢንተርናሽናል በኢትዮጵያ ያለውን የሰብአዊ መብት አያያዝ አስመልክቶ በቅርቡ ይፋ ያደረገው ሪፖርት ለዚህ ሁነኛ ማሳያ ነው፡፡ አምነስቲ ባወጣው ሪፖርት ጥናቱ በተካሄደባቸው በአማራ ክልል የምዕራብ እና ማዕከላዊ ጎንደር ዞኖች እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምእራብ ጉጂ ዞኖች ግድያ፣ በዘፈቀደ ዜጎችን በቁጥጥር ሥር ማዋል፣ ጾታዊ ጥቃት፣ ድብደባና አካላዊ ጉዳት፣ ዜጎችን ከመኖሪያ አካባቢያቸው በኃይል ማስነሳት፣ የንብረት ውድመትና ሌሎች በደሎች መፈጸማቸውን አመልክቷል፡፡

አምነስቲ ተፈጸመ ያለውን የሰብአዊ መብት ጥሰት አስመልክቶ የሳተላይት እና የፎቶግራፍ ማስረጃዎችን ያቀረበ ሲሆን በተፈጸመው ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰት የፌዴራል እና የክልል የጸጥታ ኃሎች በቀጥታ ከመሳተፋቸው በተጨማሪ ጉዳቱን ለማስቆም እየቻሉ እርምጃ ከመውሰድ መቆጠባቸውን አመልክቷል።አምነስቲ ኢንተርናሽናል ጥናቱን ያካሄደበት ዘዴ (Methodology) እና ተያያዥ ውስንነቶችን አስመልክቶ በተለያዩ አካላት እየተነሱ ያሉ ትችቶች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ በሪፖርቱ የተካተቱ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ዜና የሀገራችንን አሁናዊ የሰብአዊ መብት አያያዝ በተመለከተ ትልቅ ጥያቄ የሚያጭር ነው፡
፡

**የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ (ነእፓ)** ባለፉት ጥቂት ቀናት የአምነስቲን ሪፖርት እንዲሁም የሀገራችንን አጠቃላይ የሰብአዊ መብት አያያዝ እና የወደፊት እጣ ፋንታ በተመለከተ በጥልቀት ሲመለከት ቆይቷል። **ነእፓ** በዜጎች ላይ በደረሰው ኢ-ሰብአዊ ድርጊት የተሰማውን ከፍተኛ ሀዘን ይገልጻል። ከምንም በላይ ለዜጎች ሰብአዊ እና ፖለቲካዊ መብቶች መከበር ልዩ ትኩረት የሚሰጠው **ነእፓ** ከህግ አግባብ ውጪ በመንግስትም ሆነ በሌሎች አካላት የሚፈጸምን እርምጃ በፅኑ ያወግዛል። በጥናቱ የተገለጸው የሰብአዊ መብት ጥሰት የሀገሪቱን ህገ መንግስት እና የዜጎችን ሰብአዊ መብት ለመጠበቅ የወጡ ህጎችን እንዲሁም ከሰብአዊ መብት ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለምአቀፍ ስምምነቶች በጉልህ የሚጻረር ነው። የሰብአዊ መብት ጥሰቶቹ የተፈጸሙበት ወቅት በሀገራችን ከሁለት ዓመት በፊት በተጀመረው የፖለቲካ ለውጥ ማግስት መሆኑ ይበልጥ አሳሳቢ እና አሳዛኝ ያደርገዋል።

አምነስቲ ኢንተርናሽናል እና ሌሎች ዓለምአቀፍ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች የሀገራችንን የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን አስመልክተው በተለያዩ ጊዜያት ያወጧቸውን ሪፖርቶች ታሳቢ በማድረግ፣ እንዲሁም በሀገራችን የሰብአዊ መብት ጥበቃ ያለበትን እጅግ ዝቅተኛ ደረጃ ከግምት ውስጥ በማስገባት **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** የሚከተሉትን የመፍትሄ ሀሳቦች ያቀርባል፣

1. መንግስት በለውጡ ማግስት ለህዝብ ከገባቸው ቃሎች ውስጥ አንዱ እና ዋነኛው የዜጎች ሰብአዊ መብቶች እንዲከበሩ ማድረግ መሆኑ ይታወሳል። በመሆኑም መንግስት እና ገዢው ፓርቲ ለህዝብ የገቡትን ቃል በመጠበቅ በየትኛውም የሀገራችን ክልል የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እንዳይፈጸሙ የማድረግ ህገ መንግስታዊ ግዴታቸውን ሊወጡ ይገባል፣
2. ኃይል የመጠቀም ብቸኛ መብት ያለው መንግስት እና መንግስት ብቻ ነው። በመሆኑም ከመንግስት ውጪ ያሉ ማንናቸውም ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች በዜጎች ላይ የኃይል እርምጃ የመውሰድ እድል ሊኖራቸው ፈጽሞ አይገባም። የመንግስት የጸጥታ አካላት ሰላምና መረጋጋትን ለማስጠበቅ የሚወስዱት እርምጃ ተመጣጣኝ እና ህግና ስርዓትን ለማስከበር የሚያስችል ብቻ ሊሆን ይገባል፤
3. በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ የጸጥታ ኃይሎች የሙያ ስነምግባር በሚጠይቀው መሰረት ኃላፊነታቸውን በገለልተኝነት እና በከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት ሊወጡ ይገባል። ሃላፊነት የሚጎድላቸው ጥቂት የጸጥታ ተቋማት አባላት የሚወስዷቸው እርምጃዎች ህዝብ በተቋማቱ ላይ ያለውን አመኔታ እንዲሸረሸር ስለሚያደርግ ሊታረም ይገባዋል፣

4. በአምነስቲ የቀረበው በኦሮሚያ እና በአማራ ክልሎች የተወሰኑ ዞኖች የተከሰቱት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እንዲሁም በዜጎች ላይ የደረሰው ጥቃት የሀገራችንን የሰብአዊ መብት አያያዝ በትንሹ የሚያሳይ ሲሆን ችግሩ በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች በስፋት እንደሚኖር ታውቆ ሁሉንም ክልሎች ያቀፈ ጥናት እንዲካሄድ፣

5. የፌዴራል እና የክልል መንግስታት አስፈጻሚ አካላት በሰብአዊ መብት ዙሪያ ጥናት ለሚያደርጉ ሀገራዊም ሆነ ዓለምአቀፍ ድርጅቶች በቂ እና ወቅታዊ መረጃ የመስጠት እና የመተባበር ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ተገንዝበው ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ፣

6. በሀገራችን የሰብአዊ መብት አያያዝ ታሪክ ከመሰረቱ ለመቀየር እና የዜጎች ሰብአዊ እና ፖለቲካዊ መብቶች ሙሉ ለሙሉ የሚከበሩባት ሀገር ለመፍጠር፣ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን እና የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ጉባኤን (ኢ.ሰ.መ.ጉ) ጨምሮ ሌሎች የመንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ሀገራዊ የሰብአዊ መብት ተቋማትን ለማጠናከር፣ ብሎም የአስፈጻሚ አካላትን በሰብአዊ መብት ዙሪያ ያላቸውን ግንዛቤ ለማዳበር እንደ ሀገር ሰፊ ስራ ሊሰራ ይገባል፣

7. ሰብአዊ መብትን የማስከበር ኃላፊነት የአንድ ወገን ብቻ አይደለም፤ መንግስት፣ የተፎካካሪ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ማህበራት፣ በጋራ እና በቅንጅት ሊሰሩ ይገባል። ይህንን እውን ለማድረግ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን ሚና በአግባቡ ሊወጡ ይገባል፣

8. በመጨረሻም በሀገራችን የሰብአዊ መብት ጥሰትን አስመልክቶ በተለያዩ አካላት የሚወጡ ጥናቶችን በተመለከተ አንዳንድ የመንግስት አካላትና የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጧቸው ሀሳቦች በሪፖርቶቹ ቅርጽ ላይ ከሚገባው በላይ ትኩረት በማድረግ መሬት ላይ ያለውን ሀቅ የዘነጉ ሆነው ይታያሉ።ይህ የተሳሳታ አተያይ አምነስቲ በቅርቡ ባወጣው ሪፖርትም ላይ ተስተውሏል። በመሆኑም በዜጎች ላይ የሚፈጸሙ ጥናቶች ላይ የሚቀርቡ መረጃዎችን በተመለከተ የሪፖርቶቹ የአሰራር ህፀፆችን ከመተቸት ባሻገር ከፖለቲካዊ ወገንተኝነት በጸዳ መልኩ በዜጎች ላይ የሚደርሱ ኢ-ሰብአዊ ጥቃቶችን ማውገዝ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል።

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ግንቦት፣ 2012**
**አዲስ አበባ**

# ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ሀገራዊ መግባባት (National Dialogue) ለማስጀመር የሚያስችል ሰነድ ይፋ አደረገ፡፡

የሀገራችን የፖለቲካ ታሪኮች የፈጠሯቸው ውስብስብ የፖለቲካ ችግሮች ጠባሳቸው ዛሬም ድረስ አልጠፉም፡፡ ልዩነቶችን በድርድር የመፍታት፣ የሀሳብ ብዝሀነትን የመቀበል፣ የመደማመጥ ባህላችን ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ድህነትን ጨምሮ ሌሎች ለነገ የማይባሉ ድርብርብ ችግሮችን ለመፍታት ተቀራርቦና ተባብሮ ለመስራት የሚያስችል የፖለቲካ ባህል የለንም፡፡ የብዙሀኑን ፍላጎት ያላገናዘበ የልሂቃን ፖለቲካ፣ ከመተማመን ይልቅ እርስ በርስ መጠራጠር፣ የራስን ሀሳብ አግዝፎና የሌሎችን አሳንሶ ማየት (Political Chauvinism) የፖለቲካችን መሰረታዊ መገለጫዎች ሆነዋል፡፡ የሚያስማሙን በርካታ ጉዳዮች እያሉ በሚለያዩን ጥቃቅን አጀንዳዎች ላይ ተጠምደናል፡፡ ቢያንስ ከሶስት ትውልድ በላይ ያስቆጠረው የፖለቲካ ባህላችን ብዙ ዋጋ አስከፍሎናል፡፡

ችግሮቹ በተቻለ ፍጥነት ካልተወገዱ በሀገራችን መጻኢ እድል ላይ ትልቅ ተግዳሮት ሆነው ይቆያሉ፡፡ እነዚህ የፖለቲካ ችግሮቻችን ሳይፈቱ ምርጫ ማካሄድ በሂደቱና በውጤቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይኖራቸዋል፡፡ ፈርጀ ብዙ የፖለቲካ ችግሮቻችንን ለመቅረፍ **ብሄራዊ መግባባት** /National Dialogue/ መፍጠር አንገብጋቢ ሀገራዊ አጀንዳ እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ ብሄራዊ መግባባት መፍጠር ምርጫ 2012ን ሰላማዊ፣ ነጻ እና ፍትሀዊ ከማድረግ ባሻገር የሀገራችንን ፖለቲካ በዘላቂነት ለማከም ቁልፍ ሚና እንደሚጫወት **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በጽኑ ያምናል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ይህንን ወሳኝ የፖለቲካ ስራ ለመስራት ሀሳብ አመንጭቶ እና ለውይይት መነሻ የሚሆን ሰነድ አዘጋጅቶ ለተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ መንግስታዊ እና መንግስዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የሚዲያ ተቋማት፣ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ በኢትዮጵያ ለሚገኙ የዲፕሎማቲክ ኮሚዩኒቲ አባላት እና ሌሎች አካላት ሀሳቡን አጋርቷል፡፡ **ነእፓ** በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በዝርዝር የአተገባበር ስልቶች ዙሪያ ለመነጋገር የውይይት መድረክ ያዘጋጃል፡፡

በሀገራችን ብሄራዊ መግባባት ከተፈጠረ ቀጣዩ ሀገራዊ ምርጫ ከዝግጅት እስከ ፍጻሜ ሰላማዊ፣ ውጤቱም ተአማኒ እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋጾ ይኖረዋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ያቀረበው የብሄራዊ መግባባት ሀሳብ ወደ ተግባር ይቀየር ዘንድ ከፖለቲካ ድርጅቶች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የበኩሉን ሚና እንደሚጫወት ያስታውቃል፡
:

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**መጋቢት 3፣ 2012**
**አዲስ አበባ**

# በታላቁ የህዳሴ ግድብ ውይይት ብሄራዊ ጥቅማችን ለድርድር ሊቀርብ አይገባም!!

ከአመታት በፊት ግንባታው የተጀመረው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ እጅግ ከፍተኛ የሀገር ሀብት ፈሶበት ዛሬ ድረስ ሊጠናቀቅ ካለመቻሉም በላይ በበርካታ አስተዳደራዊ፣ ቴክኒካዊ፣ ፖለቲካዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ምክንያቶች ስራው በመጓተት ላይ ይገኛል። ፕሮጀክቱ ካጋጠሙት የቴክኒክ ችግሮች ባሻገር ባለፉት ጥቂት ወራት የአሜሪካ መንግስት እና የዓለም ባንክ በታዛቢነት በሚገኙበት ከታችኛው ተፋሰስ ሀገራት ጋር የሚደረገውን ድርድር አስመልክቶ መንግስት ግልጽ፣ በቂ እና ወቅታዊ መረጃ ባለመስጠቱ የግድቡን የግንባታ ሂደት አስመልክቶ በዜጎች ላይ ከፍተኛ ሰጋት ተፈጥሯል።

በተለይ የግድቡን አሞላልና ሥራ በተመለከተ ጉዳዩ በቀጥታ የማይመለከታቸው የውጭ መንግስታት እና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች መሳተፋቸው ብዙዎች የድርድር ሂደቱን ፍትሀዊነት በጥርጣሬ እንዲመለከቱት አድርጓል። **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** መንግስት በግድቡ ዙሪያ በማካሄድ ላይ ያለው ድርድር ከሚያሰጋቸው የፖለቲካ ድርጅቶች አንዱ ነው። የሀገርን ብሄራዊ ጥቅም ማስጠበቅ ተቀዳሚ ኃላፊነቱ አድርጎ የሚያምነው **ነእፓ** በታላቁ የህዳሴ ግድብ የድርድር ሂደት ዙሪያ መንግስት ግልጽነት የተሞላበት አሰራር መከተል እንዳለበት በጽኑ ያምናል። ከፍተኛ መዋእለ ነዋይ የፈሰሰበት የታላቁ ህዳሴ ግድብ ካጋጠሙት ዘርፈ ብዙ ተግዳሮቶች በአጭር ግዜ ተላቆ መጠናቀቅ ይችል ዘንድ መንግስት እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በኃላፊነት እና በተጠያቂነት የድርሻቸውን እንዲወጡ ኃላፊነት አለባቸው።

**የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ያጋጠሙትን ተግዳሮቶች በተመለከተ ካለበት ሀገራዊ እና ታሪካዊ ኃላፊነት በመነሳት፣

- መንግስት ከታችኛው የተፋሰስ ሀገሮችም ሆነ ከማንኛውም ሶስተኛ ወገን ጋር በሚደረግ ድርድር የሀገራችንን ብሄራዊ ጥቅሞች ለማስጠበቅ ቅድሚያ ሰጥቶ እንዲሰራ፣
- በግድቡ ዙሪያ ከሚመለከታቸው ሀገራት እና ሌሎች የውጭ ሀገራትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በመካሄድ ላይ ያለውን ውይይት አስመልክቶ መንግስት ወቅታዊ እና በቂ መረጃ እንዲሰጥ፣
- ከግድቡ ግንባታ ጋር ተያይዞ ያሉ የቴክኒክ እና የፕሮጀክት አስተዳደር ችግሮች በአፋጣኝ ተቀርፈው፣ በተከለሰው የግዜ ሰሌዳ መሰረት ግድቡ ኃይል የማመንጨት ስራውን በተያዘለት ጊዜ እንዲጀምር መንግስት አስፈላጊውን እንዲያደርግ ያሳስባል።

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**የካቲት 19፣ 2012**
**አዲስ አበባ**

# ፓርቲ እና መንግስት ይለዩ!!

**ከነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የተሰጠ መግለጫ**

ባለፉት ሶስት አሰርተ አመታት በሀገራችን ከታዩ መሰረታዊ የፖለቲካ ችግሮች አንዱ የፓርቲ እና የመንግስት መቀላቀል የፈጠረው ውስብስብ ሂደት ነው፡፡ የመንግስት ስልጣንን ሙሉ ለሙሉ የተቆጣጠረው ገዥ ፓርቲ የመንግስትን መዋቅር እና ሀብት በመጠቀም በትረ ስልጣኑን ለማራዘም ኢ-ዴሞካራሲያዊ መንገዶችን ሲጠቀም ቆይቷል፡፡ በአንጻሩ የተፎካካሪ ፓርቲዎችን እንቅስቃሴ በመገደብ አመራሮቻቸውን እና አባላቱን በማሰርና በማዋከብ የሀገራችን የፖለቲካ ምህዳር እንዲጠብ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

በሀገራችን በተጀመረው የለውጥ ሂደት ከሚጠበቁ ውጤቶች አንዱ የፖለቲካ ምህዳሩን ማስፋት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች በነጻነት እና በእኩልነት የሚደራጁበትና ስራቸውን በነጻነት የሚያካሂዱበት ስርአት መፍጠር ነው፡፡ የፖለቲካ ሜዳው እና የጫወታው ህግ ሁሉንም የፖለቲካ ኃይሎች እኩል የሚያስተናግድ የፖለቲካ ስርአት ገዥው ፓርቲ እንደ አንድ ፓርቲ የሚታይና የገዥው ፓርቲ ድርጅታዊ እንቅስቃሴዎች ከመንግስት መዋቅር ሙሉ ለሙሉ ተለይተው የሚካሄዱበት ይሆናሉ፡፡ የገዥው ፓርቲ የሀብት ምንጭ እንደ ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ከአባላቱ እና ከደጋፊዎቹ ብቻ የሚሰበሰብ ሲሆን፣ ከመንግስት ካዝናም ይሁን፣ ማንኛውንም የመንግስት መዋቅር ተጠቅሞ ሀብት የመሰብሰብ መብት አይኖረውም፡፡

ይህ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ሁላችንም ስንጠብቀው የቆየነው የመንግስት እና የፓርቲ ልዩነት በትክክል እየተተገበረ ባለመሆኑ የለውጡን መንፈስ እና አዲሱን የምርጫ እና የፖለቲካ ፓርቲዎች  አዋጅ በእጅጉ የሚቃረን ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ብቻ ገዥው ፓርቲ ከባለሀብቶች ገንዘብ ለመሰብሰብ የተለያዩ አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶችን በመጠቀም ጥሪ ያካሄደ ሲሆን፣ የሰብሰባውን አጃንዳ ሳያውቁ ከተሰበሰቡ ባለሀብቶቹ ለገዥው ፓርቲ የገንዘብ መዋጮ እንዲያደርጉ ተጠይቀዋል፡፡ይህ አሰራር በተለያዩ ክልሎችም በስፋት እየተፈጸመ መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በተመሳሳይ በፌደራል እና በክልል መስሪያ ቤቶች የሚሰሩ የመንግስት ሰራተኞች የፓርቲ አባልነት መዋጮ በፔሮል ከደመወዛቸው ላይ የመቁረጥ አሰራር ዛሬም ድረስ እንዳልቆመ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በመሆኑም፤

1. ገዥው ፓርቲ ከባለሀብቶች የሚሰበስበውን ድጋፍ ከመንግስት መዋቅር ውጪ በፓርቲው ድርጅታዊ መዋቅር ብቻ እንዲያካሂድ፣ ፓርቲው ለሀብት ማሰባሰብ ለባለሀብቶች የሚያደርገውን ጥሪ ከመንግስት መዋቅር ውጪ ግልጽ በሆነ መንገድ በፓርቲው ስም እንዲያከናውን፣ ለፓርቲው ሀብት ማሰባሰብ ስራ ላይ የሚሰማሩ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት የመንግስት ስልጣናቸውን ተጠቅመው ጫና ከማሳደር እንዲቆጠቡ እና የተሰጣቸውን መንግስታዊ ኃላፊነት ለመላው ህዝብ ያለአድልዎ እንዲሰጡ፣
2. ገዥው ፓርቲ በፌደራል መንግስት እና ክልል መስተዳድር ውስጥ ከሚሰሩ አባላቱ የሚሰበስበው የአባልነት መዋጮ ከመንግስት መዋቅር ውጪ በራሱ በፓርቲው ድርጅታዊ መዋቅር እና ጽ/ቤት እንዲሰበሰብ፣
3. ገዥው ፓርቲ የመንግስት መዋቅርን በመጠቀም የሚያካሂዳቸው ማናቸውም አይነት የሀብት ማሰባሰብ ስራዎች አዋጁን የሚጻረር እና የፖለቲካ ሜዳውን ለገዢው ፓርቲ የሚያሰፋ እና ለሌሎች ተፎካካሪ ፓርቲዎች የሚያጠብ በመሆኑ በአፋጣኝ እንዲቆም፣

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ጥሪውን እያቀረበ፣ የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ እና የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አዋጁን በማስከበር ገዥው ፓርቲ ድርጅታዊ መዋቅሩን ከመንግስት መዋቅር ለይቶ እንዲሰራ አስፈላጊውን ያደርጉ ዘንድ ያሳስባል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**
**ጥር 2012**
**አዲስ አበባ**